# ማ ው ጫ

ገፅ


ከአንባብያን....................................................................2

የዝግጅት ክፍሉ ማስታወሻ..............................4

ፖለቲካ

- እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን አስፈላጊነት፣ ይዘትና ፋይዳ............................................................6
- የወጣቶችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እናረጋግጥ !!...........38
- በሶሻል ሚዲያ ምህዳሩ ተሳትፏችንን በማሳደግ ግንባር ቀደም ሚናችንን እንወጣ !! ............................76


## አዲስ ራዕይ

በየሁለት ወሩ፣ በአማርኛ ቋንቋ እየተዘጋጀች በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ዓለም አቀፋዊና ድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ማብራሪያና ትንታኔ ይዛ የምትቀርብ የኢህአዴግ የትንታኔ መፅሄት ነች፡፡


11ኛ ዓመት ቅፅ 5 መስከረም- ጥቅምት 2009

አዘጋጅ፡- የኢህአዴግ የህዝብና የውጭ ግንኙነት ዘርፍ

አሳታሚ፡- ኢህአዴግ

አድራሻ፡- ስልክ 011-123-43-03

የመ.ሳ.ቁጥር፡-80007

ፋክስ፡- 011-122-12-34 /124-34-72

ኢ.ሜይል- addisreay. mag @ gmail.com

ድህረ ገፅ- WWW.eprdf.org.et/publication

## "ዋናው መስመሩ ነው"

የሚሄድበትን ቦታና ወደዛ የሚያደርሰውን ትክክለኛ መንገድ የለየ ተጓዥ ያሰበበት ቦታ ሳይደርስ አይቀርም፡፡ኢህአዴግ ከጅምሩ ትክክለኛውን የህዝብ ጥያቄ፣ችግር እና ሀገራዊ ደህንነት ሁኔታ በመለየት መልስ ሊሰጥ የሚችል ትክክለኛውን መስመር በመፍጠር ታግሎ በማታገል ለመበታተን እያቃሰተች የነበረችን ሀገር አንገትዋን ቀና እንድታደረግ አድርጓል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተአምር የተባለለት ለውጥም አምጥቷል፡፡በተጨማሪም ከውልደቱ ጀምሮ ለድርጅቱ፣ለአባላቱና ለህዝቡ ስጋት የሆኑ የተለያዩ ችግሮች በየጊዜው ሲያጋጥሙት ነበር፡፡ አስፈላጊውን አቅጣጫ በመቀየስም እየፈታ መጥቷል፡፡አሁንም ኪራይ ሰብሳቢነት ወቅታዊ ሀገራዊ ስጋት የፈጠረ ችግር ሆኗል፡፡ኢህአዴግ አሁንም እንደልማዱ ሙሉ ሐላፊነቱን ወስዶ ሁሉንም ህዝብ ሊያታግል የሚችል የመፍትሄ አቅጣጫ በመለየት ትግሉን አቀጣጥሎታል፡፡ ትግሉ እንዴት መመራት እንዳለበትም መጋቢት-ሚያዝያ ቅፅ 5 ቁጥር 4 በወጣችው አዲስ ራዕይ መፅሄት ላይ ተብራርቷል ጥሩ ግንዛቤም ተፈጥሯል፡፡ ስለሆነም መስመሩን ይዘን እኛም እንታገላለን ችግሩም አዳዲስ ብልህ ጀግና መሪዎችን ፈጥሮልን አነቃቅቶን ያልፋል ስለሆነም የጠራ መስመር ካለ የማይታለፍ ተግዳሮት የለም ዋናው መስመሩ ነው እያልኩ አዲስ ራዕይ መፅሄትን የመስመሩ ኮምፓስ ናትና ለአዘጋጆችዋ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ይትባርክ ኋ/ሚካኤል
ከዲላ ዩንቨርስቲ

## አዲስ ራዕይ የድርጅታችን የቀኝ እጅ

ውድ የአዲስ ራዕይ መጽሄት አዘጋጆች መስከረም - ጥቅምት ቅጽ 5 ቁጥር 2/2008 አዲስ ራዕይ መጽሄታችሁ ላይ የድርጅቱ ወቅታዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ የወደፊቱ የድርጅቱ አቅጣጫ በሚመለከት እና የኪራይ ሰብሳቢነት በሀገራችን ለረጅም ጊዜ የበላይነት መያዙን በተለይ በከተማ አካባቢ ኪራይ ሰብሳቢነት ከምንጩ ለማድረቅ ቃል የተገባበት መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡ ነገር ግን እንደ እኔ ግምት በከተማ አካባቢ ኪራይ ሰብሳቢነት፣ የመልካም አስተዳደር ችግር ማዳከም የሚቻለው እና ልማታዊነት የበላይነት እንዲይዝ ለማድረግ ከተፈለገ በተለይ ሥራ መሠራት ያለበት በከተማ አስተዳደር ሥር ከሚገኙ መስሪያ ቤቶች እስከ ቀበሌ ድረስ ብቃት ያለው አመራር የማፍራት ስራ ላይ ትኩረት ቢሰጠው ኪራይ ሰብሳቢነት ማዳከም እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ህብረተሰባችን በአብዛኛው ቀጥታ ግንኙነት የሚያደርገው ከላይ በገለፅኩት መስሪያ ቤቶች በመሆኑ ነው እላለሁ፡፡

ነጋሽ ቀቻ
ወልቂጤ ጉራጌ ዞን

# ኪራይ ሰብሳቢነትና የወቅቱ ትግል

ውድ አዲስ ራዕይ አዘጋጆች ቅፅ 5 ቁጥር 4 2008 ዓ/ም ካነበብኩት “የተሃድሶ መስመራችን የፀረ ኪራይ ሰብሳቢነት ትግሉና የወቅቱ ሁኔታ” በሚል ርዕስ የተሰጠው ትንታኔ አርክቶኛል፡፡ በፀረ ኪራይ ሰብሳቢነት ትግል በአመራሩ በአባሉና በህዝቡ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎን ያለ ምንም ማጋነን አስቀምጧል፡፡ ይህንን ነባራዊ ሃቅ ኢህአዴግ በተሃድሶ መስመራችን ኪራይ ሰብሳቢነት የስርአቱ  አደጋ መሆኑን አበክሮ ገና በጧቱ የገለፀ ሲሆን አሁን ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ኪራይ ሰብሳቢነት ያስከተለውን ጉዳት በዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን ይህንን ችግር ከስር መሰረቱ ካልተወገደ በህዝቦች መራራ ትግልና መስዋእትነት የተገኘ ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ ልማትና ፍትህ እንዳይቀለበስ የተቀመጠውን ወቅታዊ የትግል አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ በየደረጃው የምንገኝ የድርጅቱ አባላትና አመራሮች ምልአተ ህዝቡን ባሳተፈ መልኩ ከፍተኛ ርብርብ ልናደርግ ይገባል እላለሁ፡፡

ካሳ ተሾመ
ሰሜን ወሎ ቆቦ ከተማ

# እንኳን አደረሰን

ድርጅታችን ኢህአዴግ ከ1993 ዓ/ም የተሃድሶ ንቅናቄን በማቀጣጠል ላለፉት 15 ዓመታት በአገራችን ባስመዘገበው ሁለንተናዊ ለውጥ ከነበርንበት የድህነት አረንቋ በመላቀቅ አለምን ያስደመመ ስኬት ልናስመዘግብ ችለናል፡፡ድርጅታችን ኢህአዴግ ገና ከማለዳው በማያሻማ መልኩ በግልፅ አመላክቶ እንዳስቀመጠው ባስመዘገብነው ተከታታይና ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት በሽግግር ላይ ያለ ማህበረሰብ መፍጠር ተችሏል፡፡ ይህ ታላቅ ድል ሞጋች የሆነ ማህበረሰብ እንዲፈጠር በማድረግ በየደረጃው የሚገኘውን የድርጅታችንን አመራር በማያቋርጥ የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ በተግባር በማስገባት እንዲፈተን በማድረግ ከተለያዩ ብልሽቶች የሚድንበት ነባራዊ ሁኔታ ተፈጥሯል።ይህንን መልካም እድል በአግባቡ በመጠቀም ይበልጥ ተጠናክረን የምንወጣበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ ድርጅታችን ሲለውና ሲመኘው የነበረው ነባራዊ ሁኔታ በመፈጠሩ እንኳን ለዚህ ለትግል ምቹ የሆነ ነባራዊ ሁኔታ አደረሰን እያልኩ በጥልቀት በመታደስ የጀመርነውን የህዳሴ ጉዞ አጠናክረን በማስቀጠል በየደረጃው የምንገኝ የድርጅታችን አባላትና አመራሮች ለተሃድሶው ስኬት የበኩላችንን ሚና ለመወጣት ዝግጁ ልንሆንይገባል፡፡

መለሰ ገበየሁ
ፍኖተ ሰላም

# የዝግጅት ክፍሉ ማስታወሻ

## በጥልቀት በመታደስ ሀገራዊ ሕዳሴያችንን እናረጋግጣለን!!

ኢህአዴግ መቼም ቢሆን ለሚያጋጥሙት ችግሮች ውጫዊ ምክንያት ከመስጠት ይልቅ ወደ ውስጥ በመመልከት ራሱን በማረም ላይ የሚያተኩር ህዝባዊ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅታችን የሚያጋጥሙትን ፈተናዎች በብቃት በመተንተንና ሁነኛ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በመንደፍ ህዝቡን ባሳተፈ መልኩ በመተግበር ሀገራችን በቀጣይ የምትደርስበትን የዕድገት ደረጃና በየምዕራፉ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ጭምር ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተንትኖ አማራጭ መፍትሄዎቻቸው በመጠቆም ቀድሞ የሚዘጋጅ የለውጥ ኃይል ነው፡፡ ኢህአዴግና የግንባሩ አባል ፓርቲዎች ገና ከምስረታቸው ጀምሮ ፈታኝና ውስብስብ ሁኔታዎችን በድል የመወጣት ብቻ ሳይሆን ተግዳሮቶችንም ወደ መልካም እድልነት በመቀየር ከአንድ ፈታኝ ምዕራፍ ወደ ሌላኛው ከፍተኛ የስኬት ምዕራፍ እየተሸጋገሩ የመጡ ናቸው፡፡ ኢህአዴግ እንደ ግንባር ከተመሰረተ ወዲህም ያጋጠሙትን ችግሮች ራሱን ማዕከል አድርጎ ከነምንጫቸው በጥልቀት ሲፈትሽ፣ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ሲያስቀምጥና መላ ህዝቡን ከጎኑ በማሰለፍም ለመታረም ሲተጋና በዚህም የሀገራችንን ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት እያረጋገጠ መጥቷል፡፡ በ2008ዓ.ም ማገባደጃ የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የኢህአዴግ ምክር ቤት ባስቀመጡት አቅጣጫ መሰረት በግንባሩና በአባል ፓርቲዎች በሚገኙ ሁሉም መዋቅሮች እየተካሄደ ያለው ዳግም በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄም የዚሁ የድርጅታችን ነባር መሰረታዊ ባህሪ ውጤትና መገለጫ አካል ነው፡፡

በቅርቡ በአንዳንድ የኦሮሚያ እና የአማራ ክልል አካባቢዎች ለተከሰቱት ወቅታዊ ችግሮችም ሆነ ከዛ በፊት በነበሩት ተከታታይ አመታት ህዝባችንን እያስመረሩ ያሉና ለልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን ፈተና የሆኑ ችግሮች ዋነኛ መንስዔ የድርጅትንና የመንግስትን ስልጣን ለህብረተሰባዊ ለውጥ ከማዋል ይልቅ ለግል ጥቅም ማበልፀጊያ የማዋል ዝንባሌ በውስጣችን ስር እየሰደደ መሆኑ እንደሆነ ኢህአዴግ ለይቷል፡፡ ይህ ችግር አሁኑኑ የማያዳግም መፍትሄ ካልተሰጠው በስተቀር የጀመርነው የሕዳሴ ጉዞ የሚቀለበስበት እድል ዝግ እንደማይሆንም ኢህአዴግ ገምግሟል፡፡ ለዚህም ነው የፀረ ኪራይ ሰብሳቢነት ትግሉ በውስጣችን፣ ከውስጣችን ደግሞ ከበላይ አመራሩ ጀምሮ እንዲቀጣጠል በማድረግ ሁሉም የድርጅታችን መዋቅር እራሱን በጥልቀት እየፈተሸ የሚታደስበት አቅጣጫ የተቀመጠው፡፡

የአሁኑ አዲስ ራዕይ እትማችን ዋነኛ የትኩረት ማዕከል የሆነውም ይሄው ወቅታዊ የሀገራችንና የድርጅታችን ሁኔታ ነው፡፡ የዚህ እትም አብይ አጀንዳ የሆነውና "እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን አስፈላጊነት፣ ይዘትና ፋይዳ" በሚል የቀረበው ፅሁፍ በመታደስ ንቅናቄያችን ላይ ጥልቅ ትንታኔ ያዘለና በተሃድሶው ማግስት የሚኖረንን መዳረሻ ያስቀመጠ ነው፡፡ ሀገራችን የምትገኝበት አጠቃላይ ሁኔታ በዝርዝር የሚተነትነው ይህ ፅሁፍ ዳግም ለመታደስ ግድ ያሉንን ምክንያቶች ከስር መሰረታቸው ያብራራል፡፡ በመሆኑም ዳግም ተሃድሷችንን ስናካሂድ የምንመራበት አቅጣጫ ሆኖ የሚያገለግል ፍኖተ ካርታ (Road Map) መሆኑን ታሳቢ በማድረግ መላ አባላትና አመራሩ በጥልቀት እንዲወያዩበት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ሁለተኛው ፅሁፍ የወጣቶችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንፃር እስካሁን የተጓዝንበትን ርቀትና በአሁኑ ወቅት ያላሚላናቸው የወጣቶች ፍላጎቶች ላይ አትኩሮ የተዘጋጀ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ወጣቶች አብዛኛውን የሀገራችንን የህብረተሰብ ክፍል የሚይዙ ናቸው፡፡ ይህ ተስፋና ስጋት የሚታይበት አገራዊ ወቅታዊ ሁኔታ በተለይ ለወጣቶች የፈጠረው እድልና ያስከተለው ተግዳሮት እንዲሁም ወደፊት የምንጓዝበት አቅጣጫ ምን መምሰል እንዳለበት በዝርዝር ያብራራል፡፡ ችግሮችን በመሻገርና እድሎችን አሟጦ በመጠቀም ረገድ ከወጣቶች የሚጠበቀው ሃላፊነት የፅሁፉ ማጠንጠኛ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ፅሁፍም ለወጣቶች መድረኮች ማወያያ ሰነድ ሆኖ ከማገልገል ባለፈ አባላት በየአደረጃጀቶቻቸው ለሚያደርጉት ውይይት መነሻ ሆኖ እንዲያገለግል ታሳቢ ተደርጓል፡፡

ሶሻል ሚዲያ አሁን ባለንበት አለማዊ ሁኔታ በፈጣን ለውጥ ውስጥ ያለና የተፅዕኖ አድማሱን በማስፋት ላይ የሚገኝ አዲስ የሚዲያ ስርዓት ሆኗል፡፡ ድርጅታችን ኢህአዴግ ከተለምዶ መገናኛ ብዙሃን ጎን ለጎን በዚህ የሚዲያ አይነትም በብቃትና በንቃት ተሳታፊ መሆን እንዳለበት አምኖ ከ2007ዓ.ም ጀምሮ በምህዳሩ ውስጥ ተዋናይ ለመሆን የሚያስችሉት እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ እናም በሶስተኛው ፅሑፍ ላይ ሶሻል ሚዲያው ለፖለቲካ ስራችን የሚኖረው ፋይዳ ለማመላከት ጥረት ተደርጓል፡፡ በሶሻል ሚዲያ ምህዳሩ የልማታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የበላይነት ሊኖረው የሚችለው የድርጅታችን አባላትና ደጋፊዎች በተለይም ምሁራን አባላትና ደጋፊዎች በሶሻል ሚዲያው በሚያደርጉት የተቀናጀና የነቃ ተሳትፎ ነውና ፅሁፉ አባላትን በዚሁ መልኩ በሚያነቃቃ ሁኔታ ተዘጋጅቷል፡፡ ሶሻል ሚዲያው የሚሰጣቸውን መልካም እድሎች አሟጦ ለመጠቀም እንዲሁም ደግሞ የሚያስከትላቸውን አሉታዊ ተፅዕኖዎችን መቀነስ እንዲቻል አባላት በተለይም ምሁራን አባላት ድርጅታዊ ስነ ምግባርን በተላበሰና የልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብን ልዕልና በሚያረጋግጥ መልኩ በምህዳሩ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ እንዳለባቸው በመገንዘብም ሁሉም አደረጃጀቶች ከፍተኛ ርብርብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

መልካም ንባብ !!

# እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን አስፈላጊነት፣ ይዘትና ፋይዳ

## 1. መግቢያ

በ2008 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ የተሰማው እንደገና በጥልቀት የመታደስ ድርጅታዊ ውሳኔ በርግጥም በአስቸጋሪነቱ ለየት ያለ ባህሪ ይዞ የተጠናቀቀው ያሳለፍነው ዓመት ብሩህ ማጠቃለያ ነበር፡፡ በተለይ ደግሞ የከፋ ግጭትና ሁከት በተቀሰቀሰባቸው የክረምቱ ወራት፣ በብዙዎች ዘንድ "ወዴት እያመራን ነው?" የሚል ምላሽ የሌለው የሚመስል ጥያቄ ከግራም ከቀኝም ይቀርብ እንደነበር ላስተዋለ ሁሉ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ውሳኔያችን ዓመቱን በአዎንታዊ ቅኝት ያጠናቀቅንበት ነበር፡፡ በተጨማሪም አዲሱን ዓመት በታላቅ የለውጥ መንፈስ፣ ወኔና ዝግጅት እንድንጀምረው ዕድል የከፈተልን ነበር፡፡ ከዚህ አኳያ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ውሳኔያችን ወቅታዊና ነብስ አድን ነው ማለት ይቻላል፡፡

እንደገና በጥልቀት የመታደስ ውሳኔያችንን ፋይዳ በትክክል ለመገንዘብ የሚቻለው ግን አስፈላጊ ያደረጉትን ምክንያቶች ጥቂት ወደኋላ መለስ ብሎ ከመመልከት በመጀመር ነው፡፡ የአዲሱ የመታደስ ንቅናቄ መሰረታዊ መንስዔዎች እንዲሁም ይዘትና ባህሪ ምን እንደሆነ በውል በመገንዘብ ንቅናቄውን በተቀመጠለት አቅጣጫ አስኪዶ ተፈላጊውን ውጤት ለማምጣት ይቻል ዘንድ ከመጀመሪያው ተሃድሶ በመጀመርና አንዳንድ መሰረታዊ ጥያቄዎችን በማንሳት ጉዳዩን መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡ ከዚህ በመነሳት በዛሬው የአዲስ ራዕይ ዕትም እንደገና በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴያችንን አነሳስና ይዘት በተመለከተ አጠር ያለ ማብራሪያ ነክ ፅሁፍ ይዘን ቀርበናል፡፡

# 2. እንደገና በጥልቀት መታደስ ለምን አስፈለገን?

እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄ ለማካሄድ ከመዘጋጀታችን ጋር ተያይዞ በቀዳሚነት የሚነሳው ጥያቄ፣ “ከዚህ ቀደም የተጀመረውና እስካሁን የቆየው የተሃድሶ እንቅስቃሴ ምን ስለሆነ ነው እንደ አዲስ በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄ አስፈላጊ ሆኖ የመጣው?” የሚል መሆኑ አይቀርም፡፡ በርግጥም ለአስራ አምስት ዓመታት በተሃድሶ ላለፈ ድርጅትና መንግስት በመጀመሪያው ተሃድሶ ላይ ምን ሳንካ ቢያጋጥም ነው ሌላ የመታደስ እንቅስቃሴ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው? የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ መሰረታዊ ጥያቄ በመነሳት ሌሎች ተከታይ ጥያቄዎችን እያቀረቡ ጉዳዩን በጥልቀት መመርመር ለተሟላ ግንዛቤ ያግዛል፡፡ ግንዛቤያችን በጠራ የሁኔታዎች ግምገማ ላይ ተመስርቶ ሲገነባ ደግሞ በጉዳዮቹ ላይ ጥራት ያለው ብቻ ሳይሆን ለቀጣይ ስራና ትግል የሚያግዝ ዕውቀት መያዝ ይቻላልና ከሁሉ በማስቀደም አገራችን በምትገኝበት ተጨባጭ የዕድገት ደረጃ ላይና በወቅታዊ መገለጫዎቹ ዙሪያ የጋራ ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል፡፡

## 2.1 ሁሌም በእድገት ጎዳና መራመድን የግድ የምትል አገር መገንባታችን እንደ ምክንያት

በማንኛውም አገር ያለ ህብረተሰብ ከትንሽ ወደ ትልቅ፣ ከቀላል ወደ ውስብስብ እያደገ የሚጓዝ እንደመሆኑ አገራችንም በዚህ የማይቀር የህብረተሰብ የጉዞ አቅጣጫ ማለፏ የግድ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከደረሰችበት የዕድገት ደረጃና ከገባችበት መድረክ ለሚመነጩ መልካም ዕድሎችና ተግዳሮቶች የምትጋለጥ አገር መሆኗ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ይህን በመሰለው ሁኔታ ከአመራር የሚጠበቅ ኃላፊነት መልካም ዕድሎቹን በአግባቡ በመጠቀም፣ ፈተናዎቹን ደግሞ በጥበብና በፅናት በማለፍ፣ አለፍ ሲል ደግሞ ተግዳሮቶችን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም አገራችን በማያቋርጥ የዕድገት ሂደት እንድታልፍና ህዝቦቿን በሙሉ እየጠቀመች እንድትጓዝ ማድረግ ይሆናል፡፡ ከዚህ ውጭ ሌላ ዕድል፣ ሌላ መንገድ የለም፡፡

የዛሬዋን ኢትዮጵያ መነሻ በማድረግ እንደገና በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴውን አስፈላጊነት ለመረዳት የሚቻለው ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የመጣውን ለውጥ መነሻ አድርጎ ሂደቱን በመመልከት ነው፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ እንዲህ እንደዛሬው መለወጥ ከመጀመሯ በፊት ለብዙ ዘመናት በአስቸጋሪ ምዕራፍ ውስጥ ለማለፍ የተገደደች አገር ነበረች፡፡ በአገራችን ታሪክ የማያባራ የርስ በርስ ጦርነት ከተካሄደበት ከዘመነ መሳፍንት ጀምሮ የነበረው ታሪኳ እንደሚያሳየው እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ የሚዘገንን ዕልቂት ያስከተሉ ጦርነቶችን አስተናግዳለች፡፡ ይህም በአንድ በኩል በእርስ በርስ ጦርነቱ የተነሳ፣ በሌላ በኩል ደግሞ መንግስታቱ ስልጣናቸውን ለግል ብልፅግና መጠቀሚያ አድርገው ህዝቡን ለፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዳይበቃ በማድረጋቸው የተፈጠረ ነው፡፡ ጦርነቱም ሆነ ድህነትና ኋላቀርነቱ ታዲያ አገሪቱን ወደ መበታተን አፋፍ አስጠግቷት ነበር፡፡

አገራችን የብዙ ህዝቦች እናት ሆና እያለ ብዝሃነትን በአግባቡ የሚያስተናግድ ስርዓት ስላልነበራት በሁሉም ማዕዘኖች ለቅሬታዎች መበራከት፣ ለአመፅ መቀስቀስና መበራከት ለም አፈር ተፈጥሮ ነበር፡፡ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተረግጠው ዜጎች ለስቃይ በተዳረጉባቸው በእነዚያ ዘመናት ወደ ውድቀት አፋፍ ተጠግታ ከዛሬ ነገ ትበታተናለች ተብሎ የተሰጋላት አገር እስከ መሆን ደርሳ ነበር፡፡ በድርቅና ረሃብ፣ በጦርነትና ጭፍጨፋ ሚሊዮኖች እንደ ቅጠል የሚረግፉባት፣ ስደትና መፈናቀል የበዛባት አገር ለመሆን ተገዳም ነበር፡፡

ይህ ሁኔታ እስከ ግንቦት 1983 ዓ.ም. ከቀጠለ በኋላ ያ የታሪክ ምዕራፍ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከደርግ ውድቀት ጋር አብሮ ተዘጋ፡፡ ኢትዮጵያ ከአፈና አገዛዝ ወደ ዴሞክራሲ፣ ከከፊል ፊውዳልና ከፊል ካፒታሊስታዊ ስርዓት ወደ ታዳጊ የገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት ተሸጋገረች፡፡ ደርግ በሶቭየት ህብረት ሞዴል የገነባው የዕዝ ኢኮኖሚ ካለብዙ ምስቅልቅል ደረጃ በደረጃ እንዲናድ ከተደረገ በኋላ አገራችን ታዳጊ የገበያ ስርዓት አቅጣጫን በመከተል ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በአዲስ ፈለግ ስትጓዝ ቆይታለች፡፡

ያለፍንባቸው ሃያ አምስት ዓመታት በእርግጥም በሁሉም የህይወት መስኮች የህገራችን የማሽቆልቆል ምዕራፍ የተዘጋባቸው አዲስና የማያቋርጥ

የእድገት ምዕራፍ የተከፈተባቸው ነበሩ፡፡ በእነዚህ ዓመታት ለዘመናት ከኖርንባቸውና ከተጓዝንባቸው አቅጣጫዎች የተለዩ አዳዲስ መንገዶች ተከትለናል፡፡ በቅድሚያ አገራችን ከምንም ነገር በላይ በዴሞክራሲ እጦት የምትሰቃይ አገር እንደሆነች በመገንዘብ የተሟላ ዴሞክራሲን ለማስፈን ጥረት ተደርጓል፡፡ መጀመሪያ በሽግግሩ ወቅት ቻርተር የጀመረው የዴሞክራሲ ለውጥ ሂደት፣ በህገ-መንግስቱ ተሟልቶና ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ በህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ተዘጋጅቶ የቀረበውና ሁሉንም አማራጭ ድንጋጌዎች ለህዝብ ውይይት ያቀረበው ረቂቅ ህገ-መንግስት በ1986 ዓ.ም እስከ አስራ ስምንት ሚሊዮን የሚደርሱ ዜጎች ከመከሩበት በኋላ በህዝብ በተመረጡ ተወካዮች እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡

በዚህ ዴሞክራሲያዊ አኳኋን የፀደቀው ህገ-መንግስታችን በይዘቱም ቢሆን ዴሞክራሲያዊና የተዋጣለት ነበር፡፡ማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት አሟልቶ ሊይዛቸው የሚገባ ዴሞክራሲያዊ ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡ በተጨማሪም ህገ-መንግስታችን በሌሎች ህገ-መንግስቶች ተፈልገው የማይገኙ ተጨማሪ ዴሞክራሲያዊ አንቀፆችን ይዞ የተቀረፀ ከመሆኑም በላይ በተግባርም በኢትዮጵያ የሚገነባውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚገዛና የሚመራ የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ ይገኛል፡፡ የዜጎችና የማህበረሰቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አሟልቶ በመጓዝ የተቀረፀው ህገ-መንግስታችን እነሆ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲገነባ ያስቻለን ቁልፍ የለውጥ መሣሪያችን ለመሆን በቅቷል፡፡ በዚህ ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት ከሌሎች መሰል አገሮች በተለየ ሁኔታና ደረጃ መንግስታዊ ስልጣን የህዝብ መገልገያ መሣሪያ መሆን እንዳለበትና በዚሁ በመመራት የሚገነባው ስርዓትም ይህን ያለማወላወል ለማረጋገጥ የሚያስችል ማዕቀፎችን ይዞ እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡

ህገ-መንግስታችን የአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አቅጣጫ የህዝብና የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በሚያስችሉ መሰረታዊ መርሆች እንዲመራ አድርጓል፡፡ በዚህም ባህሪው በአገራችን የህዝብን ተጠቃሚነት የሚያሰፋ በተለይ ደግሞ በድህነትና በጉስቁልና የሚኖሩ ህዝቦችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከምንም ነገር በላይ ትኩረት እንዲሰጥ ያደረገ ዴሞክራሲያዊና ተራማጅ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ለመገንባትም እጅግ

የተመቸ ሁኔታ የፈጠረ ነበር፡፡ በዚህ ላይ ድርጅታችን አገር የመለወጥና ህዝባችንን ተጠቃሚ የማድረግ ራዕይ ይዞ የመሰረተውና የመራው መንግስት በተከተላቸው ትክክለኛ የፖሊሲ አቅጣጫዎች አገራችን ከደርግ ውድቀት በኋላ በነበሩት በመጀመሪያዎቹ አስር ዓመታት በአማካይ የ5.5 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት እያስመዘገበች እንድትጓዝ ለማድረግ ችለናል፡፡ ይህ የዕድገት ምጣኔ በወቅቱ መላው አፍሪካ በአማካይ ሲያድግበት ከነበረው የ3 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት ጋር ሲነፃፀር ከሞላ ጎደል እጥፍ ነበር፡፡ ስለሆነም ድርጅታችን የመሪነት ሚናውን በአገር ደረጃ ባረጋገጠባቸው በመጀመሪያዎቹ አስር ዓመታት በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የማሽቆልቆል ምዕራፍ በአስተማማኝ አኳኋን እንዲዘጋ ማድረግ ጀመረ፡፡ ልማት፣ ዴሞክራሲና ሰላም የማይነጣጥሉ አገራዊ ግቦች እንዲሆኑ ያደረገው ድርጅታችን፣ በእነዚህ ዓመታት በእርግጥም ኢትዮጵያ በአዲስ የዕድገት አቅጣጫ እንድትረማመድ አደረገ፡፡

ይህም ሆኖ በእነዚህ ዓመታት ድርጅታችንንና መገንባት የጀመረውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚፈታተኑ ልዩ ልዩ ዝንባሌዎች አልታዩም ማለት አልነበረም፡፡ ይልቁንም የህዝብ መብትና ጥቅም እንዲከበር አልሞ የተነሳውን ድርጅታችንን የየራሳቸው የክብደት ደረጃ የነበራቸው ልዩ ልዩ ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎች ገጥመውታል፡፡ ከእነዚህ ፈተናዎች አንዱ ለለውጥ የተነሳውን ድርጅትና መንግስት ወደ አንድ ተራ አፍሪካዊ ዘራፊ መንግስት ሊቀይር የሚችል የጥገኝነት አስተሳሰብና እንቅስቃሴ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የኤርትራ መንግስት ያካሄደብን ወረራ ነበር፡፡

ወረራው ውጭያዊ በመሆኑ ከባድ መስዋዕትነት በመክፈል ሊቀለበስ ይቻልና ይገባው የነበረ ሲሆን ከዚህ በላይ ከባድ ሆኖ የተገኘው ችግር ከስርዓቱ ዝቅጠት ጋር ተያይዞ የተነሳውና ድርጅታችንን ለማፍረስ ተቃርቦ የነበረው አደጋ ነበር፡፡ ድርጅታችንን በዚህ ወቅት የገጠመው የጥገኛ ዝቅጠት አደጋ መሰረታዊ ምንጩ ከአመራራችን ንዑስ ባለሃብትነት ጋር ተያይዞ ይህ ኃይል ቀስ በቀስ ስልጣኑን ካለአግባብ ለመጠቀምና ለመበልፀግ እንደ መሣሪያ መጠቀም በመጀመሩ ነበር፡፡ አመራራችን ከንዑስ ባለሃብት መደባዊ ተፈጥሮው በመነሳት ሲታይ፣ በአንድ በኩል ትግሉ በተለይ የአርሶ አደሩ ትግል የተጠናከረ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ አብዮታዊ የአመራር ሚና የሚጫወት ይሆናል፡፡ ከዚህ ለየት ባለና አርሶ አደሩ በተቀዛቀዘ ሁኔታ

በሚያልፍበት ጊዜ ደግሞ በያዘው ስልጣን ራሱንና የቅርብ ወዳጆቹን እየጠቀመና እየተጠቃቀመ በመጓዝ ወደግል ብልፅግና ሊሸጋገር የሚችል ነው፡፡

ይህ ዝንባሌ በንድፈ ሃሳብ የሚታወቅ ከመሆኑ በተጨማሪ በአገራችን ሁኔታ በተጨባጭ መከሰት የጀመረው ገና ወደ ስልጣን በመጣን ማግስት ነበር፡፡ በሁሉም ክልሎችና ብሄራዊ ድርጅቶች የመንግስት ስልጣን የያዙ ግለሰቦች ቀስ በቀስ በስልጣን የመጠቀም አዝማሚያቸው እየጠነከረ መሄድ ጀመረ፡፡ ይህም ድርጅታችን የአርሶ አደሩ ጥያቄዎች የነበሩትን የዴሞክራሲና የብሄር እኩልነት፣ ራስን በራስ የማስተዳደርና የምርት ነፃ ተጠቃሚነት መብቶችን በማረጋገጡ የአርሶ አደሩ ትግል ስለተቀዛቀዘ አመች ሁኔታ ስለተፈጠረለት የታየ ዝንባሌ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትርና የድርጅታችን ምክትል ሊቀ መንበር የነበረው አቶ ታምራት ላይኔ ከፈፀመው ከባድ የሙስና ቅሌት ጀምሮ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት የታዩት ራስን ወደ አዲስ ገዥ መደብነት የማሸጋገር አዝማሚያዎች ይህን በግልፅ የሚያመላክቱ ነበሩ፡፡

ከዚህ በመነሳት ሲታይ እንደ እኛ በአገራዊ የለውጥ ሂደት ውስጥ ከሚያጋጥሙት ፈተናዎች አንዱና መሰረታዊው የመንግስትን ስልጣን አላግባብ ለመጠቀምና በዚህም እየታገዙ ለመበልፀግ ማሰብና መንቀሳቀስ መሆኑ የማያጠያይቅ ሆኗል፡፡ ይህ ዝንባሌ እስከ ተወሰነ የእድገት ደረጃ አብሮ የሚቆይና በማንኛውም ሁኔታ ቸል ሳይባል ሊታገሉትና ሊቆጣጠሩት የሚገባ ዝንባሌ ነው፡፡ ይህ ዝንባሌ አርሶ አደሩ የነበሩት ጥያቄዎች ሁሉ ተመልሰውለት በሰላም አርሶ መብላት በሚፈልግበት ሁኔታና ወቅት ይበልጥ የተመቸ ሁኔታ እንደሚፈጠርለት ግንዛቤ ተይዞ ተገቢው ጥንቃቄና ትግል ካልተደረገበት በስተቀር ስርዓቱን ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑ የማያጠያይቅ ነው፡፡ በ1993 እና በ1994 ዓ.ም. የተካሄደው ድርጅታዊ ተሃድሶ ዋነኛ መነሻዎችም እነዚህ ነበሩ፡፡

ተሃድሶው እስከ ተወሰነ የታሪክ ምዕራፍ በተለይ ደግሞ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ የተሟላ ልዕልና እስኪይዝ ድረስ ባለው የለውጥ ምዕራፍ፣ የመንግስት ስልጣን በማያቋርጥ ደረጃ ከታለመለት ዓላማ ውጭ የግል ብልፅግና መሣሪያ ሊሆን የሚችልበት ዕድል እንዳለ፣

ከዚህም አልፎ ይህ ዝንባሌ ከስርዓቱ ጋር በማይነጠል ሁኔታ አብሮ የሚኖርና ቀጣይ ትግል የሚጠይቅ እንደሆነ አሰመረበት፡፡ በአንፃሩ ይህን ችግር ለመቋቋም አስፈላጊ የሆነው የህዝብ ትግል ደግሞ እንደሁኔታው ሊኖርም ላይኖርም፣ሊቀዛቀዝም ላይቀዛቀዝም እንደሚችል ተሰመረበት፡፡ ይህ የህዝብ ትግል በሌለበት ጊዜ ሁሉ የመንግስት ስልጣንን ካለአግባብ የመጠቀም ዝንባሌ ከመኖሩ አልፎ፣ የበላይነት ሊይዝ ይችላል፡፡ ስለሆነም በመፍትሄ ደረጃ የህዝቡን ትግል በቀጣይነት ማረጋገጥ እንደሚገባ፣ ለዚህም ሲባል በህብረተሰባችን ውስጥ ዴሞክራሲና ልማትን ማስፋፋትና የህዝብን ተጠቃሚነት እያረጋገጡና እያሰፉ መሄድ እንደሚገባ በግልፅ ተቀመጠ፡፡ ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት በአገራችን የጥገኛ ዝቅጠት አደጋን ለመመከት የሚያስችል እንቅስቃሴ የጀመርነው ከዚህ በመነሳት ነው፡፡

ይህ እንቅስቃሴ የተሃድሶ መስመሩን በመንግስታዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ መልክ በመቅረፅና ወደ ህዝቡ በማስረፅ አሃዱ ብሎ ተጀመረ፡፡ በመቀጠልም ፖሊሲና ስትራቴጂዎቹን በዓመታዊ ዕቅድ መልክ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ ሽግግር ተደረገ፡፡ እነሆ ላለፉት አስራ አምስት ዓመታት በዚህ የተሃድሶ አቅጣጫ እየተመራን በመንቀሳቀስ አገራችን በተሟላ የለውጥ ምህዋር ውስጥ እንድትገባ ለማድረግ ቻልን፡፡ በእነዚህ ዓመታት ኢኮኖሚያዊ ዕድገታችን ከመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት በተሻለ የዕድገት ምጣኔ እንዲራመድ አደረግን፡፡ በዚህ የተነሳም መላው አፍሪካ በአማካይ ከ6 በመቶ ባልበለጠ ዓመታዊ ዕድገት ሲራመድ፣ አገራችን ግን ባለ ሁለት አሃዝ ዕድገት እያስመዘገበች ልትቀጥል ቻለች፡፡ በዚህ ዕድገት ብዙሃኑ የአገራችን ህዝቦች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ባደረግነው ርብርብ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ዜጎቻችን ቁጥር ከ54 በመቶ ወደ ሃያ ሁለት በመቶ እንዲወርድ ለማድረግና በከተማም በገጠርም ልማት ተስፋፍቶ የህዝብ ተጠቃሚነት እንዲጨምር ለማድረግ ተቻለ፡፡ በማህበራዊ ልማት መስክ ትምህርትና ጤና ተስፋፉ፡፡ የመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ተጠናከረ፡፡ እነዚህ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ውጤቶች ዴሞክራሲያችንን ይበልጥ የሚያጎለብቱና የሚያጠናክሩ ከመሆን አልፈው ራሱን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታችንን ደግሞ ለዚሁ ተብለው በሚወሰዱ ርምጃዎች አጠናከርን፡፡ በዚህ የተነሳ አገራችን ኢትዮጵያ ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በሁሉም መስኮች በቀጣይነት እያደገች ስትጓዝ የቆየች አገር ልትሆን በቃች፡፡

ድሎቻችን ትልልቅና መሰረታዊ ነበሩ፡፡ ለውጡ በሁሉም የህይወት መስኮች የተካሄደና በእርግጥም አገራችንን ከማሽቆልቆል በማላቀቅ ራሱን ወደ ቻለ አዲስ የሽግግር ምዕራፍ ያስገባ ነበር፡፡ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት አኛ ኢህአዴጎች ለዘመናት በማሽቆልቆል ሂደት ውስጥ ለማለፍ የተገደደችውን አገራችንን ከአንድ የዕድገት ምዕራፍ ወደ ሌላ እያሸጋገርን እጅግ የሚያስጎመጅ የዕድገት ተስፋ ያላት አገር ለመሆን አብቅተናታል፡፡ ኢትዮጵያ ዛሬ ከፍተኛ ብዛት ባለው ህዝቧና እጅግ በጣም ፈጣን ዕድገት በሚያሳያው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቷ እንዲሁም ሰላምና መረጋጋት የሰፈነባት አገር ልትሆን በመብቃቷ በእርግጥም ማንንም የምታማልል አገር ልትሆን ችላለች፡፡ ይህ የመጀመሪያው ተሃድሷችን አገራዊ ውጤት ነው፡፡

ኢትዮጵያንም ሆነ ተሃድሷችንን ከዚህ ስኬት ውጪ ለመረዳትም ሆነ ለመግለፅ መሞከር ቢያንስ አንድ ግዙፍ እውነታን መካድ የሚሆነው በዚህ የተነሳ ነው፡፡ እናም በአጠቃላይ በሃያ አምስት ዓመታት፣ በተለይም ደግሞ ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት ለዘመናት የተኛችውን አገር ቀስቅሰን ይህን የሚያስጎመጅ ሁኔታ የፈጠርነው ኢህአዴጎች ከስኬት አኳያ ቀና ብለን እንድንራመድ የሚያደርግ ታሪክ እንዳለን ሊሰመርበት የሚገባ ነው፡፡ ይህን ስኬት ከማንኛውም ዓይነት ክፉ ነገር ጠብቀን ልናስቀጥለው ይገባናል፡፡ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄን አስፈላጊ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱና ዋናውም በአገራችን መመዝገብ የጀመሩትን መልካም ውጤቶች አጠናክሮ የማስቀጠል አስፈላጊነት እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

ነገር ግን ይህ ሁኔታ አንድ መገለጫ ወይም የሳንቲሙ አንድ ገፅታ ብቻ ነው፡፡ ከስኬቶቹ ትይዩ እንደገና የመታደስ ንቅናቄን የግድ የሚሉ ሌሎች ጉዳዮችም አሉ፡፡ የመታደስ ጥያቄ ሁሌም ከእኛ ጋር መኖር ያለበት፣ ወይም ተሃድሶ በቋሚነት የምንመራበት መርህ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ መሆኑ ባይካድም፣ በዚህ ወቅት እንደገና መታደስን የሚጠይቁ ሌሎች ሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ደግሞ አሉ፡፡ አንደኛው ምክንያት የመጀመሪያውን የተሃድሶ መስመር ተግባራዊ በማድረጋችን የተፈጠሩ አዳዲስ አገራዊ እውነታዎች መኖራቸውና እነዚህን በአግባቡ ማስተናገድ አለመቻላችን እንደገና በጥልቀት መታደስን የግድ የሚል መሆኑ ነው፡፡ ህብረተሰባችን በጣም ታዳጊና ዳይናሚክ ህብረተሰብ ነው፡፡ ይህ ህብረተሰብ

ከአንድ የዕድገት ምዕራፍ ወደ ሌላ የዕድገት ምዕራፍ ያለማቋረጥ እየተሸጋገረ ሲጓዝ ከመቆየቱ በተጨማሪ አንዳንዶቹ ለውጦች በራሳቸው እንደገና ያደገ ነገር ይዘን እንድንቀርብ የግድ የሚሉ ሆነዋል፡፡ ለምሳሌ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂያችንን ተግባራዊ ከማድረጋችን ጋር ተያይዞ በገጠር ብዙ ለውጦች በመምጣት ላይ ናቸው፡፡ ከአርሶ አደሩ ምርታማነት መጨመር ጋር ተያይዞ ለተጨማሪ የስራ ስምሪት ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው የህዝብ ፍልሰት በጣም ጨምሯል፡፡ በተለይ ደግሞ ወጣቶች ከገጠር እየለቀቁ በአቅራቢያቸው ወደሚገኙ ትንንሽ ማዕከላትና ከተሞች በሰፊው እየፈለሱ ይገኛሉ፡፡ ይህ የዕድገት ውጤት ቢሆንም በህብረተሰብ ደረጃ እጅግ በጣም ሰፊና ሙሉ አካባቢውን የሚመለከት አዳዲስ ጥያቄ ያስከተለ ሆኗል፡፡ የወጣቶችን የመልማትና የተጠቃሚነት ጉዳዮችን በፍጥነት፣ በስፋትና በአስተማማኝ ደረጃ መመለስ የግድ የሚል ሆኗል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ ከመስፋፋቱ ጋር ተያይዞ ህብረተሰባችን ሰፊ የተማረ የሰው ኃይል የሚገኝበትና ይህም እንደገና ለአዳዲስ ጥያቄዎች መቀስቀስ በር የከፈተ ሆኗል፡፡ ባለፉት በርካታ ዓመታት በሁሉም መስኮች የተከናወነውን ስራና የህዝቡን ንቃት በከፍተኛ ደረጃ አሳድጎታል፡፡ ህዝቡ ከልማት አኳያ ፈጣን ዕድገት ምን ማለት እንደሆነና ምን እንደሚመስል ብቻ ሣይሆን፣ ከዚሁ በማይነጠል መልኩ ዕውን መሆን ያለበት ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ምን እንደሆነ ለመገንዘብ ችሏል፡፡ ከዚህም አልፎ መሰረተ ሰፊ ዴሞክራሲ እንዲሁም የህዝብ ተሳትፎ ምን ማለት እንደሆነና ምን እንደሚመስልም ተገንዝቧል፡፡ መንግስትን የመቆጣጠር ሚናውም ሆነ ፍላጎቱና ጥቅሙ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማድረግ ከእርሱ ስለሚጠበቀው ሚና ተገንዝቧል፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነት ምን ማለት እንደሆነና በህዝብ ጥቅሞች ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ምን እንደሆነ ተገንዝቦ ይህንኑ ለማስወገድ በንቃት የሚታገል ህብረተሰብ ሆኗል፡፡

ከዕድገታችን ጋር ተያይዘው የመጡት እነዚህ ሁሉ አዳዲስ እውነታዎች የምንመራው ህብረተሰብ እንደተለወጠ ማሳየት ብቻ ሳይሆን ከድርጅትና ከመንግስት በኩል የሚጠበቀው አመራር ከፍተኛ ብቃት ያሟላ መሆን እንዳለበት የግድ የሚሉ ሆነዋል፡፡ በዚህ የተነሳ አመራራችን በየጊዜው እየታደሰ፣ አገራዊው ፈጣን ዕድገት የሚጠይቀውን ብቃት

በቀጣይነት እያሟላ የሚሄድ መሆኑን ማረጋገጥ ቁልፍ ሆኗል፡፡ ስለሆነም በየጊዜው የምንገባበት አዲስና ያደገ መድረክ ድርጅታችንና አዲሱ ስርዓት ያለማቋረጥ እንዲታደሱ የሚጠይቅና እንደገና በጥልቀት የመታደስን አስፈላጊነት አግዝፎ የከሰተ ሊሆን ችሏል፡፡

እነዚህ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችንን አስፈላጊ ያደረጉ መሰረታዊ ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው ሌላ ዋነኛ ምክንያትም አለ፡፡ ይኸውም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችንን የሚፈታተን እየሆነ የመጣው የመንግስት ስልጣንን የግል ጥቅም ማስከበሪያና የኑሮ መሰረት የማድረግ ዝንባሌ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ላለፉት በርካታ ዓመታት አገራችን ዓለምን ያስደነቀ ፈጣን ዕድገት እንድታመጣና ፍትሃዊ የህዝብ ተጠቃሚነት እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ ያስቻለን አንዱ መሰረታዊ ምክንያት የመንግስት ስልጣንን ለበጎ ዓላማ ልንጠቀምበት መቻላችን ነበር፡፡ ይሁንና እኛን በመሰሉ ብዙ ያልበለፀጉ አገሮች ድህነትና ኋላቀርነት እንዲንሰራፋ ካደረጉት መሰረታዊ ምክንያቶች አንዱ የመንግስት ስልጣንን ለዝርፊያና ራስን ለመጥቀም የማዋል አስተሳሰብና ተግባር ነው፡፡ ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል በሚል ቅኝት የሚመሩት ያልበለፀጉ አገራት መንግስታት፣ በእጃቸው የገባውን ስልጣን የግል ጥቅም ማረጋገጫ መሣሪያ አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡ ስልጣን ላይ ከወጡባት ዕለት ጀምሮ ብቻ ሳይሆን፣ ለስልጣን በሚፎካከሩበት ጊዜ ሁሉ ዋነኛ ግብ አድርገው የሚያራምዱት ይህንኑ አስነዋሪ ዘርፎ የመጠቀም አስተሳሰብ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ የመንግስትን ስልጣን አዲስ እሴት በመፍጠር የህብረተሰብን የጋራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና ለማስፋት እንዲያገለግል ከማድረግ ይልቅ፣ የተፈጠረችውን ሃብት እየተቀራመቱ ኪሳቸውን ማድለብ ይቀናቸዋል፡፡ ስልጣንን የዝርፊያ መሣሪያ በማድረግ ህብረተሰባቸው ጉልበት፣ መሬትና ሌላም ፀጋ እያለው አዲስ ሃብት እንዳይፈጥር እግር ከወርች አስረው ይይዙታል፡፡ በዝርፊያ ያገኙትን ሃብት በመጠቀም ስልጣናቸውን ለማሰንበት የሚያስችል የአፈና ተቋም እየገነቡ ተመልሰው የዝርፊያ ተግባራቸውን ያጠናክራሉ፡፡

ይህን የመሰለው የመንግስት ስልጣንን የግል ጥቅም ማረጋገጫ መሣሪያ የማድረግ አስተሳሰብና ተግባር ህብረተሰብን ለድህነት እንጂ

ለብልፅግና እንደማያበቃ የተገነዘበው ድርጅታችን፣ ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በተለይ ደግሞ ከተሃድሶ ዓመታት በኋላ መንግስታዊ ስልጣንን በነጣቂ መንግስታት ፈለግ ሳይሆን በራሱ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ቅኝት ለመገንባትና ለመጠቀም ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ ያለፉት ዓመታት ያሳዩን ፈጣንና ህዝብ የሚጠቀምበት እድገት የዚህ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ቅኝት ውጤት ነበር፡፡ ይህ መሰረታዊ አቅጣጫ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን መንግስታዊ ስልጣንን የግል ብልፅግና ማረጋገጫ የማድረግ አዝማሚያ እየተጠናከረ ሲሄድ ቆይቷል፡፡ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስታችን ራሱን ከኪራይ ሰብሳቢ አዝማሚያዎች የመጠበቅና ነፃ የማድረግ ግዴታውን መወጣት ላይ ያሳየው ቸልተኝነት፣ ኪራይ ሰብሳቢነት በመንግስትም ሆነ ከመንግስት ውጪ ባሉ ኃይሎች ከልክ በላይ የገዘፈና ስርዓቱን የሚፈታተን አደጋ እየሆነ እንዲሄድ በር ከፍቷል፡፡ መንግስት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተገነባ በመጣው አገራዊ አቅም በመታገዝ መሰረተ ሰፊ የሆኑ ልማታዊ ተግባራትን የሚያከናውን ግዙፍ ተቋም መሆኑን ተከትሎ በኮንትራት  አስተዳደር፣ በግዥ፣ በግብር አሰባሰብና በመሬት ዕደላና አጠቃቀም ዙሪያ ለከፋ ሙስና የሚጋለጥበት ሁኔታ እየሰፋ ሊሄድ ችሏል፡፡ ይህ ሁኔታ በውስጣችን የመንግስት ስልጣን ለመያዝ ወይም በአንዳች ተዓምር ለመንግስታዊ ኃላፊነት መብቃት ከተቻለ ከፍ ላለ ጥቅም መብቃት ይቻላል የሚል አመለካከት እንዲሰፋም በር ከፍቶ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ወደ መንግስት ስልጣን ለመውጣት የሚደረገውን ሩጫ እንዲባባስ አደረገው፡፡ እንደምንም ተሳክቶለት የመንግስት ስልጣን ላይ ሊቀመጥ የቻለ ሰው በቀላሉ ከሚገኙ ጥቅማ ጥቅሞች ጀምሮ በአጭር ጊዜ ሰፊ ሃብት ለማግኘት የሚችልበት አጋጣሚ እንደሚያሰፋ የተገነዘቡ ሁሉ በዚህ ዕድል ለመጠቀም ዓይናቸውን የማያሹበት ሁኔታም ተፈጠረ፡፡

መንግስታዊ ስልጣንን መቋደስ ለዚህ ዓይነቱ ዕድል እንደሚያበቃ ግልፅ በሆነበት በዚህ ዘመን ዋናው የስልጣን መንገድ የሚፈጠረው በድርጅታችን እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ድርጅታችን በህዝብ ተመርጦ ስልጣን ላይ የወጣ እንደመሆኑ መጠን መንግስታዊ የኃላፊነት ቦታዎችን የሚያስይዘውም እርሱ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በቆየው ልማዳዊ አሰራር የድርጅት ማዕከላዊ ኮሚቴው የተሻለ ብቃት ባላቸው ሰዎች የተሞላ እንደሚሆን ታሳቢ በማድረግ

የመንግስት ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት እንዲያዙ ይደረግ ነበር፡፡ ይህ አሰራር ካላንዳች ለውጥ መቀጠሉን ተከትሎ ደግሞ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ወደ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ የገቡ ሰዎች ሁሉ ብቃት ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም በሹመኝነት ትልልቅ ቦታዎች እንዲይዙ ተደረገ፡፡ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነትና ሚኒስቴርነት ወይም የቢሮ ኃላፊነት የማይነጣጥሉ ተደርገው ተወሰዱ፡፡

በዚህ የተነሳ የመንግስት ሹመኛ መሆን የፈለጉ እንደምንም አንገታቸውን ወደ ፓርቲ አመራርነት ለማስገባት መረባረብ ጀመሩ፡፡ ድርጅታችንም የስልጣን ብቻ ሳይሆን ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ማረጋገጫ መሣሪያ ወደ መሆን አምርቶ የድርጅታችን የአመራር ጥራት ለአደጋ መጋለጥ ጀመረ፡፡ አድርባዮችና የስልጣን ጥመኞች ወደ ፓርቲው የኃላፊነት ቦታዎች በመግባት በቀላሉ ወደ መንግስት ስልጣን የሚሸጋገሩበት ሁኔታ እየሰፋ በመሄዱም ይዘነው የተነሳነው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት የመገንባት ተልዕኮ ለአደጋ መጋለጥ ጀመረ፡፡

አንድ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ይህን ለመሰለ የኪራይ ሰብሳቢነት አዝማሚያ በመጋለጡ ምክንያት ተልዕኮውን ለመፈፀም እየተቸገረ መሄድ ሲጀምር፣ ያነገባቸው መሰረታዊ ግቦች መደነቃቀፍ የሚያጋጥማቸው መሆኑ አያከራክርም፡፡ መንግስት አገር የመለወጫና የህዝብ ጥቅም ማረጋገጫ ከመሆን ይልቅ የግል ጥቅም ማስጠበቂያና የኑሮ መሰረት መሆን ሲጀምር የዕድገት ፍጥነት መቀነስና ከዚሁ በማይነጠል መልኩ ደግሞ በህዝብ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ዙሪያ ተመሳሳይ ችግር መከሰት ይጀምራል፡፡ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እየተዳከመ፣ የህዝብ ጉዳትና ቅሬታ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ይህ በአገራችን ደረጃ ምናልባታዊ ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ መታየት የጀመረ ዝንባሌ መሆኑ በዚህ የተነሳ ነው፡፡ በአገራችን እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄን አስፈላጊ ካደረጉት ጉዳዮች ሌላው መሰረታዊ ምክንያት ይህ ነው፡፡

እንደገና በጥልቀት መታደሱ አስፈላጊ የሆነው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስቱን ብቻ ሣይሆን ድርጅታችንንም ጭምር ይህን ከመሰለው አደጋ ለመጠበቅና በአገራችን የተጀመረው የህዳሴ ጉዞ በታለመለት አቅጣጫ ተጉዞ ተፈላጊው የእድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ እንዲችል ነው፡፡

ከላይ ከቀረበው ማብራሪያ በመነሳት እንደገና በጥልቀት የመታደስ አገራዊ ንቅናቄን የግድ ያሉት ሶስት ዋነኛ ምክንያቶች እንደሆኑ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው በሃያ አምስት ዓመታት ሂደት በተለይ ደግሞ በአስራ አምስቱ የተሃድሶ ዓመታት ጉዟችን ያስመዘገብናቸውን መልካም ውጤቶች የማስጠበቅና የማስፋት አስፈላጊነት ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ከዕድገታችን ጋር ተያይዘው የተነሱ አዳዲስ የህዝብ ጥያቄዎችና ፍላጎቶችን በዳበረ አስተሳሰብ በመመለስ የህዝብን ፍላጎት የማርካትና አዳዲስ ጥያቄዎች እንዲነሱ የማድረግ አስፈላጊነት ነው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስቱና ድርጅታችን በመንግስት ስልጣን አተያይና አጠቃቀም ዙሪያ ካጋጠማቸው አደጋና ድክመት በማላቀቅ ለተልእኳቸው የማብቃት አስፈላጊነት ነው፡፡ እነዚህ ሶስት ምክንያቶች መሰረታዊና ትክክለኛ ብቻ ሣይሆኑ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን በዚህ ጊዜና መልክ እንዲካሄድ የሚያደርጉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በወቅቱ ያጋጠመን የፖለቲካ ቀውስ አንድ በአንድ ሲመረመር እንደገና በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴን የግድ የሚል ሁኔታ እንዳለ ለማረጋገጥ አይከብድም፡፡

## 2.2 ወቅታዊ ሁኔታው እንደገና በጥልቀት መታደስን አስፈላጊ ማድረጉ እንደ ምክንያት

በቅርቡ ሰፋ ያሉ የአገራችንን አካባቢዎች የሸፈነ ፖለቲካዊ ቀውስ እንደተከሰተ ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ ቀውሱ ሰፊ የህዝብ ቁጥር ባላቸው የአገራችን ክልሎች በርከት ባሉ ከተሞችና አንዳንድ ገጠሮች የተቀሰቀሰ ነበር፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች በአብዛኛው ወጣቶች የተሳተፉበት ግጭት አዘል ፖለቲካዊ መነሳሳት የታየ ሲሆን፣ ለዚህ ሁኔታ መፈጠር መሰረታዊ ምክንያቶች ደግሞ ከላይ የተዘረዘሩት ነበሩ፡፡ ምንም እንኳ በእነዚህ ግጭቶች ዙሪያ የተከሰተውን ቀውስ መነሻ በማድረግ በተለይ ፅንፈኛ የዲያስፖራ ኃይሎች የራሳቸው የስራ ውጤት እንደሆነ በማስመሰል ሲያቀርቡ የከረሙ ቢሆንም፣ ችግሩ በዋነኛነት ከስርዓታችን ድክመቶች ጋር የተያያዘና የዚሁ መገለጫ መሆኑን መጠነኛ ጥልቀት

ያለው ትንታኔ በማካሄድ ለማረጋገጥ አያስቸግርም፡፡ለዚህ ይበጅ ዘንድ ግን የቀውሱን አንዳንድ መገለጫዎች አጠር አድርጎ ማስቀመጥና እነዚህን ከመሰረታዊ ጉዳዮች በመነሳት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

### 2.2.1 በመሰረታዊ ድክመቶች ምክንያት የተቀሰቀሰ ወቅታዊ ቀውስ

በቅርቡ የተከሰቱት ቀውሶች የልማትና መልካም አስተዳደር ጉዳይ የአገራዊ ህልውና ጉዳይ ነው ብለን ከዓመታት በፊት ያስቀመጥነው ድምዳሜ ምን ያህል ትክክለኛ እንደነበር የሚያሳይ ነው፡፡ ከሁሉ በፊት ወቅታዊ ሁከትና መነሳሳት በታየባቸው አካባቢዎች ሁሉ ችግሩ አንድም ከልማት ስራ መጓተትና ከመልካም አስተዳደር እጦት የተነሳ በተፈጠረ አሊያም ምላሽ ለሚፈልጉ አዳዲስ የህዝብ ጥያቄዎች ተገቢ ፈጣን ምላሽ መስጠት ባለመቻሉ ከተፈጠረው ተስፋ መቁረጥ ጋር የተያያዙ እንደሆኑ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ ጎላ ያለ ቀውስ በታየባቸው አካባቢዎች ያለው ሁኔታ በቅርበት ሲታይ ላለፉት ጥቂት ዓመታት በቂ የልማት እንቅስቃሴ እንዳልተካሄደ ወይም ተጀምሮ የነበረ እንቅስቃሴ እንደተቋረጠ ለመመልከት ይቻላል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች በገጠር ትርጉም ያለው የልማት ስራ አለመካሄዱን አካባቢዎቹን በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ስራዎች፣ የግብርና ምርታማነትን የማሳደግ እንቅስቃሴዎች አንድም ተጀምረው ተቋርጠዋል፤ አሊያም ከጅምሩ በአጥጋቢ ሁኔታ ሳይካሄዱ ቀርተዋል፡፡ በዚህ የተነሳ በእነዚህ አካባቢዎች ተስፋ የሚሰጥና ህዝባችን ነገን በሙሉ መተማመን አሻግሮ እንዲጠብቅ የሚያደርግ ሁኔታ ሳይፈጠር ቀርቷል፡፡ ይልቁንም የተስፋ መቁረጥ አዝማሚያ እንዲከሰት አድርጓል፡፡

በእነዚህ አካባቢዎች ሌላው የታየው ችግር ለወጣቶች በተለይ ደግሞ ከገጠር ወደ ከተማ ለሚፈልሰውና ቁጥሩ እየጨመረ ለሚሄደው ወጣት የሚሆን የስራና የተጠቃሚነት ዕድል በበቂ ደረጃ አለመፈጠሩ ነው፡፡ የተሻለ ልማት በታየባቸውም ሆነ ባልታየባቸው አካባቢዎች ከገጠር ወደ ከተማ የሚካሄድን ፍልሰት የሚያበረታቱ በርካታ ምክንያቶች ተፈጥረዋል፡፡ የአርሶ አደር ምርታማነት በጨመረባቸው ገጠሮች በእርሻ ማሳዎች ላይ ትርፍና አላስፈላጊ ጉልበት መፈጠር ጀምሯል፡፡

በሌላ በኩል የከተሞች ዕድገትና የማማለል ሁኔታ እየጨመረ መምጣቱና ትምህርትም መስፋፋቱ ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሰውን ወጣት ቁጥር አሳድጎታል፡፡ ይህ ወጣት በአብዛኛው ወደ ትንንሽ የገጠር ከተሞች የሚፈልስ ሲሆን በእነዚህ ከተሞች ደግሞ በቂ የስራ ዕድልና የተጠቃሚነት ሁኔታ አልተፈጠረም፡፡ ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሰው ወጣት ቁጥር ብዙ በመሆኑ የተነሳ መንግስት አስቀድሞ በጀመራቸውና በከፈታቸው የስራ ዕድሎች ተገቢውን እርካታ መፍጠር ሳይችል ቆይቷል፡፡ አልፎ አልፎ እንደሚጋነን ከግምት ውስጥ ገብቶ ከስራ ፈጠራ አኳያ የተሰራው ስራ ትንሽ እንዳልሆነ ቢታመንም ለችግሩ የሚመጥን ባህሪና ደረጃ እንደሌለው ለመገንዘብ ግን አያዳግትም፡፡ ይህም በመሆኑ ወጣቱ ስለወደፊት ዕድሉ ግልፅነትና መተማመን የጎደለው ሆኗል፡፡ ይህ ጥያቄዎቹ በአግባቡ ያልተመለሱለት ወጣት ለተስፋ መቁረጥ የተጋለጠበትና ከዚህም በመነሳት ወደ አፍራሽ እንቅስቃሴ የገባበት ሁኔታ ሰፍቶ ታይቷል፡፡ ይህ ወቅታዊ ሁኔታ ጅምሩን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚያጠናክር፣ አዳዲስ ተግዳሮቶችን የሚፈታና የድርጅትና የመንግስትን ድክመቶች የሚያርም እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄ እንዲካሄድ ግድ የሚል ሆኗል የተባለው ከዚህ በመነሳት ነው፡፡

### 2.2.2 አፍራሽ አመለካከቶች ጎልተው የወጡበት ወቅታዊ ቀውስ

ወቅታዊ ሁኔታው በጉልህ እንዲታዩ ካደረጋቸው ችግሮች ሌላው በአገራችን መለስተኛ ቀውስ በተፈጠረበት አጋጣሚ ሁሉ የማይቀሩት የተለያዩ አፍራሽ አመለካከቶች ገዝፈው መከሰታቸውና በዚያው ልክ ደግሞ በአገርና በህዝብ ላይ ጉዳት ያደረሱ መሆናቸው ነው፡፡ በቅርቡ የተቀሰቀሰው ቀውስ ከመምጣቱ በፊት ለበርካታ ዓመታት አፍራሽ አመለካከቶች እየተዳከሙ እንደመጡ ይታወቃል፡፡ ልማታዊ ሂደቱ እየተጠናከረ፣ የህዝቦች ተጠቃሚነት እየጨመረና ተስፋችን እየለመለመ በሄደባቸው ጊዜዎች ሁሉ በህብረተሰባችን ውስጥ በዋነኛነት ሚዛናዊ አስተሳሰብ እያደገና ስር እየሰደደ የሚሄድበት እንደነበር ታይቷል፡፡ ህዝብን በጥላቻና መቃቃር ፖለቲካ እየበከሉ ለማነሳሳት ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ አፍራሽ ኃይሎች ሁሉ

ውጥናቸው አልሳካ ብሎ ለተስፋ መቁረጥ የተጋለጡበት ሁኔታም ጎልቶ ታይቷል፡፡ አገራችን የብዙ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሃይማኖቶች አገር መሆኗ ታውቆና ተቀባይነት አግኝቶ በፍቅርና በሰላም መኖር እየዳበረ ሲሄድም ቆይቷል፡፡ በአራቱም የአገሪቷ ማዕዘናት ለሩብ ምዕተ ዓመት የዘለቀ አስተማማኝ ሰላም የተፈጠረው ከምንም ነገር በላይ ህዝባችን ከአፍራሽ ኃይሎች የአመለካከት ተፅዕኖ እየተላቀቀ ስለሄደና ሚዛናዊ አስተሳሰቡ እየዳበረ ስለነበር ነው፡፡ በዚህ የተነሳ በአዲሲቱ ኢትዮጵያ መቻቻልና መከባበር እንጂ መናናቅና መበላለጥ ሰፊ ቦታ አልነበረውም፡፡ በማንነት ላይ የተመሰረተ ግጭትና መቃቃርም አልፎ አልፎ ከሚታዩ በጣም መለስተኛ ችግሮች በዘለለ ሰፊ ቦታ አልነበረውም፤ ዛሬም የለውም፡፡ በእነዚህ ዓመታት ትምክህትና ጠባብነት መሰረታቸው እየተናደና እየጠበበ በአንፃሩ ደግሞ ልማታዊ ዴሞክራሲና ዴሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት እየተስፋፉ ሲሄዱ ቆይተዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ለሃይማኖት አክራሪነት፣ ፅንፈኝነት እንዲሁም ለአሸባሪነት የሚሆን ለም አፈር እየታጣ፣ ፅንፈኝነትን ለማዛመት የተደረጉ ሙከራዎች ሁሉ እየከሸፉ አገራችን በርግጥም የዘላቂ ሰላም ባለቤት ሆኖ ቆይታለች፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንዳንድ የአገራችን አካባቢዎች የተከሰቱ ቀውሶችን ተከትሎ አፍራሽ የፖለቲካ ዝንባሌዎች እንደገና ሲያቆጠቁጡ መመልከት ጀምረናል፡፡ በዴሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት ምትክ በመናናቅና በጥላቻ ላይ የተመሰረተ አስተሳሰብ ቀላል በማይባል ደረጃ ጉዳት ሲያደርስ ተመልክተናል፡፡ በማንነት ላይ የተመሰረተ እኩልነት በሰፈነባት አገራችን በማንነት ላይ የተመሰረተ የጥላቻ ዘመቻ ቀላል በማይባል ደረጃ መስፋፋቱን ታዝበናል፡፡ ይህን ተከትሎ ለዓመታት የጥላቻና የአፍራሽ ፖለቲካዊ ዘመቻ መሀንዲሶች ሆነው የቆዩት ፅንፈኞች ይህንኑ ዘመቻቸውን በከፋ መልክ ለማስኬድና ህዝብን ከህዝብ ጋር ለማጋጨት እንዲሞክሩ የተመቸ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል፡፡

ይህን የመሰለው ለፅንፈኝነትና አፍራሽ ፖለቲካ የተመቸ ሁኔታ የተፈጠረው በሌላ ሳይሆን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ጉዟችን ካጋጠመው መደነቃቀፍ ጋር ተያይዞ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ የስርዓታችን ፈተና በሆነው የመንግስት ስልጣን ላይ የተሳሳተ አተያይና አጠቃቀም የተነሳ ጅምሩ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ጉዞ እንቅፋት ሲገጥመው ከተፈጠረው ተስፋ

መቁረጥና ግራ መጋባት ጋር ተያይዞ የመጣ ችግር ነው፡፡ ፅንፈኛውና አፍራሹ ኃይል የራሱ የስራ ውጤት ባልሆነው ይልቁንም የራሳችን ድክመት በፈጠረለት ምቹ አጋጣሚ የተነሳ ለጊዜው በድል አድራጊነት ስሜት ሲቦርቅ ቢታይም በዋነኛነት ይህ ኃይል የራሱ ባልሆነ ድል በመስከር ላይ ያለ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ያም ሆነ ይህ የራሳችን ድክመቶች መበራከት ለጊዜውም ቢሆን በፅንፈኛና አፍራሽ የፖለቲካ አስተሳሰቦች እንድንወረር ማድረጉ በራሱ እንደገና በጥልቀት የመታደስን አስፈላጊነት የግድ የሚል ሁኔታ ላይ እንደምንገኝ ያስገነዝባል፡፡

## 2.2.3 የህዝብና የአባላት የመታደስ ፍላጎት የቀሰቀሰው ንቅናቄ

ከእነዚህ ምክንያቶች ባሻገርና በላይ በጥልቀት የመታደሱን ንቅናቄ አስፈላጊ ያደረገው ሌላው ምክንያት ህዝብና አባላት በከፍተኛ ደረጃ የፈለጉትና የጠየቁት የመታደስ ጥያቄ መሆኑ ነው፡፡ ለማንም ግልፅ እንደሚሆነው መላ የአገራችን ህዝቦችና የድርጅት አባላት ባለፉት ጥቂት ዓመታት ድርጅታችን እንደገና በመታደስ መልክ በሚካሄድ እንቅስቃሴ ችግሮቹን እንዲፈታ ተከታታይ ጥያቄዎች አቅርበዋል፤ ግፊትም አድርገዋል፡፡ በድርጅታችን ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመንግስት ስልጣን አተያይና አጠቃቀም ዙሪያ በተከሰተው ድክመት ምክንያት ጅምሩ ልማት ሲስተጓጎል የመጀመሪያ ሰለባ የሚሆኑት ህዝቡና አባላት ናቸው፡፡ በተሃድሶ መስመራችን ትግበራ ከድህነት የመላቀቅ ተስፋቸው የለመለመው መላ የአገራችን ህዝቦች ማንኛውም ስህተት ሲፈፀም በሚፈጠር መስተጓጎል ተጠቃሚነታቸው ለአደጋ እንደሚጋለጥ ይገነዘባሉ፡፡ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ መርሃችን ከዕለት ተዕለት ገቢያቸው እየጨመረና የኑሮ ደረጃቸው እየተሻሻለ የመጡት የአገራችን ህዝቦች በዚህ መስክ በሚፈፀም ማንኛውም ስህተት ተጎጂ መሆናቸውን ለመገንዘብ የተለየ ብቃት አያስፈልጋቸውም፡፡ ችግሩ በራሳቸውና በአካባቢያቸው ከፍተኛ በሆነ መንገድ ሲደርስ ይመለከታሉና በዚህ ረገድ ብዙም ጊዜ ሳይፈጅባቸው ድክመቶቻችንን ይገነዘባሉ፡፡ ትላንት ስራ አጥ የነበሩና የተሻለ የስራ እድል ያገኙ ብቻ ሳይሆኑ ከዛሬ ነገ ያልፍልናል ብለው የሚጠብቁ ስራ አጥ ወጣቶችም ጅምሩ ልማታዊ ጉዞ ለአደጋ ሲጋለጥ

የጉዳቱ ሰለባዎች መሆናቸው እንደማይቀር መረዳታቸውና ድክመቱ በፍጥነት እንዲታረም መፈለጋቸው አይቀሬ ነበር፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች የተነሳ ባለፉት ዓመታት በልማትና በመልካም አስተዳደር ችግሮች ዙሪያ ፈጣን የማስተካከያ ርምጃዎችን እንድንወስድ ከመላው የአገራችን ህዝቦችና ከአባላት የማያቋርጥ ጥያቄ ሲቀርብ ቆይቷል፡፡ መድረክ በተከፈተላቸው ቁጥር የፖለቲካ አመራሩ ብቻ ሳይሆን ሲቪል ሰርቪሱም በተገቢው ደረጃ እየደገፋቸው እንዳልሆነ የሚያነሱና የሚሞግቱን ህዝብና አባላት ነበሩ፡፡

ከእነዚህ የህዝብና የአባላት ፍላጎቶች በመነሳት ድርጅታችንን የማደስ እንቅስቃሴ ቀደም ሲል መጀመርና ተጠናክሮ መቀጠል ይገባው ነበር፡፡ ይህም ሆኖ በውስጣችን በተለይ ደግሞ በአመራር ደረጃ ለመንግስታዊ ስልጣን የነበረው አተያይና አጠቃቀም ፈር እየሳተ መሄዱን ተከትሎ ለዚህ የህዝብና የአባላት ጥያቄ በቂና ትክክለኛ ምላሽ መስጠት ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ይልቁንም አመራሩ ባለፉት በርካታ ዓመታት በተመዘገቡ ስኬቶች ተሸፍኖ ድክመቶችን ለማረም የግድ ይል የነበረውን ሁኔታ ያለመቀበል አዝማሚያውን እያጠናከረ ሲሄድ ቆይቷል፡፡ በዚህ የተነሳ ከህዝብና ከአባላት በኩል የተነሱ ልዩ ልዩ የመታደስ ጥያቄዎች ተገቢና አፋጣኝ ምላሽ ሳይሰጣቸው ቆይተዋል፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ ሁኔታውን ለማስተካከል የሚደረገው እንቅስቃሴ ግብታዊና ከህገ መንግስታዊ የችግር አፈታት ስርዓት ባፈነገጠ አቅጣጫ እየሆነ እንዲሄድ ምቹ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደጋጋሚ የተመለከትናቸው ኃይልን የተመረኮዙ የችግር አፈታት ጥረቶች እየተበራከቱ የመጡት በዚህ የተነሳ ነው፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅታችን የመጀመሪያው ተሃድሶ በተቀሰቀሰበት ወቅት በግልፅ እንዳስቀመጠው በአገራችን የመንግስትና የድርጅታችንን የመበላሸት ዕድል ለመቀነስና በወሳኝነት ለማስወገድ የሚቻለው ለልማታዊ ዴሞክራሲ ፀንቶ የሚታገል ህዝብና አባል ሲኖር ነው፡፡ ባለፉት የተሃድሶ ዓመታት ህዝቡ ልዩ ልዩ የልማትና ዴሞክራሲ ትሩፋቶች እንዲቋደስ ብቻ ሳይሆን፣ እነዚህን ለማስገኘት በሚካሄደው ትግል ንቁ ተዋናይ እንዲሆን የተደረገው ጥረትም በዚህ ቅኝት የተጀመረና የተገፋበት ነበር፡፡ እነሆ ይህ አቅጣጫ በተሳካ ሁኔታ ተፈፅሞ በአሁኑ ጊዜ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ደረጃ ለመብቱና ጥቅሙ የሚታገል ህብረተሰብ

ተፈጥሯል፡፡ የመንግስትና የድርጅት ጤንነት ለመንግስትና ለድርጅት ከፍተኛ አመራር ብቻ የማይተው፣ ይልቁንም በህዝቡ ወሳኝ ሚና ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት ለማረጋገጥ የተካሄደው ትግል ፍሬ አፍርቶ ለዛሬው እንደገና በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ እንድንበቃ ያደረገን ታጋይ ህዝብና አባል ተፈጥሯል፡፡ ድርጅታችንና ልማታዊ መንግስታችን እንደገና በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ እንዲያነሱ ምክንያት የሆናቸው መሰረታዊ ጉዳይ ከዚህ የፈለቀ ሊሆን የቻለውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ከፍ ሲል በተገለፁት መሰረታዊና ወቅታዊ ምክንያቶች የተነሳ ድርጅታችን እንደገና በጥልቀት የመታደስ ሃሳብ እንደያዘ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በጥልቀት የመታደሱ ሃሳብ አንዳንዶች እንደሚሉት ምንም ዓይነት ነባራዊ ተፈላጊነት የሌለው ወይም ያልነበረው እንዳልሆነ ለመገንዘብም ይቻላል፡፡ ንቅናቄው አስፈላጊ የሆነባቸው በርካታ ምክንያቶች ከመኖራቸውም በላይ እነዚህ መሰረታዊና ወቅታዊ ምክንያቶች በድምር በጥልቀት የመታደስን ጉዳይ አስፈላጊና ሊሳካ የሚችል እንዲሆን አድርገውታል፡፡ ፈረንጆች "ጊዜው የደረሰን ሐሳብ ተግባራዊ ከመሆን በፍፁም ማስቀረት አይቻልም" እንደሚሉት፣ በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን የወቅቱ ግዴታ ሆኖ መጥቷል፡፡ ከዚህ በመነሳት የንቅናቄውን ዋና ዋና ባህሪያትና ግቦች ባጭር ባጭሩ መመልከትና ይህን ወቅቱ የደረሰ ሃሳብ በፅናትና በዲስፕሊን ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

## 3. እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን ባህሪያት፣ ግቦችና አፈፃፀም

መሰረታዊና ወቅታዊ ሆኖ የመጣው እንደገና በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴያችን ሊሳካ የሚችለው ከምንም ነገር በፊት የንቅናቄውን ባህሪያት በትክክል በመገንዘብ፣ እንዲሁም ግቦቹንና መሰረታዊ የአፈፃፀም አቅጣጫዎቹን አሟልቶ በመጨበጥ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ስለንቅናቄው ቀጥለው የተዘረዘሩትን መሰረታዊ ጉዳዮች በውል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## 3.1 ተራማጅና የድርጅታችንን አብዮታዊና ዴሞክራሲያዊ ባህሪ የሚያጎለብት ንቅናቄ

እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን ከስረ መሰረቱ ተራማጅ ባህሪ ያለው ንቅናቄ ነው፡፡ አንድ ንቅናቄ ወይም የንቅናቄ ሃሳብ ተራማጅ መሆን አለመሆኑ የሚወሰነው ከምንም ነገር በፊት ከህብረተሰብ ህግጋት ጋር የተጣጣመ ሲሆን ነው፡፡ ከህብረተሰብ ህግጋት ጋር የማይጣጣም ማንኛውም ሃሳብ ወይም ተግባራዊ እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት ሳይጓዝ መክሸፉ አይቀሬ ነው፡፡ በአንፃሩ በህብረተሰብ ህግጋት ተገዝቶና እነዚህን አክብሮ የሚጓዝ ማንኛውም ሃሳብ ወይም ተግባራዊ እንቅስቃሴ የመክሸፍ ዕድሉ ዝቅተኛ፣ የመሳካት ዕድሉ ደግሞ እጅግ ከፍተኛ ይሆናል፡፡

ከዋና ዋናዎቹ የህብረተሰብ ህግጋት ከሚባሉት መካከል አንዱ ህብረተሰብ በማያቋርጥ ሁኔታ ወደፊት ማደግና መሻሻል ያለበት መሆኑ ነው፡፡ ይህ የማንኛውም ህብረተሰብ ፍላጎት ወይም ቋሚ ህግ ነው፡፡ የህብረተሰብን የማደግ ፍላጎት በመፃረር የሚራመድ ማንኛውም ሃሳብ ሆነ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሳይውል ሳያድር ከህዝብ ጋር መጋጨትን ያስከትላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ህብረተሰብ በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚኖርና የሚቀጥል መሆኑ የህብረተሰብ ቋሚ ህግ ነው፡፡ ይህ ህግ በማንኛውም አጋጣሚ የህብረተሰብን ተነቃናቂነት የሚያቆም ዝንባሌ ሁሉ ከህብረተሰብ ፍላጎት የማይነሳና የሚጋጭ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ማንኛውም የህብረተሰቡን እንቅስቃሴ የሚገድብ ወይም የሚገታ ልዩ ሃሳብ ተራማጅ ተብሎ የማይወሰደው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

በተጨማሪም ማንኛውም ህብረተሰብ በልዩ ልዩ ተቃራኒ ፍላጎቶች የተዋቀረና ወደፊት የመራመድም ሆነ ወደኋላ የመመለስ እድሉም በዚህ ህብረተሰባዊ ቅራኔ የሚወሰን የመሆኑ ህግ አለ፡፡ በህብረተሰብ ውስጥ በዋነኛነት በአላፊና ጠፊ ማህበረሰቦችና በወደፊቱማህበረሰቦች/Futuristic/ መካከል ያለውን ጨምሮ የተለያዩ ቅራኔዎች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ መካከል ዋናው በትልልቆቹ መደቦች ወይም የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለው ቅራኔ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ቅራኔዎች በምኞት ማስወገድም ሆነ ማጥፋት እንደማይቻል በመገንዘብ ቅራኔዎቹን ለጋራ ትንሳኤ በሚበጅ መልኩ በትክክል መፍታት የህብረተሰብ ህግ ግድ የሚለው ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የአንድን ሃሳብ ወይም ተግባራዊ ንቅናቄ መሳካት ወይም መክሸፍ

የሚወስነው እነዚህን የህብረተሰብ ህጎች የማክበር ወይም የመፃረር ይዘቱ ይሆናል፡፡ በህብረተሰብ ውስጥ የሚራመዱ ማናቸውም ሃሳቦች ጤናማ ወይም ችግር ያለባቸው እንደሆኑና እንዳልሆኑ ለመመልከት የሚሻ ማንኛውም ሰው በእነዚህና እነዚህን በመሳሰሉ የህብረተሰብ ህጎች ተገዝቶ የሚራመድ ሊሆን ይገባዋል፡፡ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችንን ተራማጅ ባህሪ ከእነዚህ መስፈርቶች እየተነሱ በመለካት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ንቅናቄያችን ከሁሉ በፊት ከህብረተሰባችን የዕድገት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ እንጂ የሚቃረን አይደለም፡፡ ተሃድሷችንን አስፈላጊ ያደረጉ ሁኔታዎችን በሙሉ መነሻ ስናደርግ የተጀመረውን ፈጣንና ህዝብ የሚጠቀምበትን ዕድገት ማስቀጠል፣ ዴሞክራሲና ሰላማችንን ማጠናከር የግድ የሚል ሁኔታ ላይ እንደምንገኝ አመላክተውናል፡፡ ባለፉት በርካታ ዓመታት ያስመዘገብናቸውን ስኬቶች የማጎልበትና የማስቀጠል አስፈላጊነት የህብረተሰብን ዕድገት ከማስቀጠል ፍላጎት የሚነሳ ነው፡፡ በህብረተሰባችን ውስጥ አዳዲስ ታዳጊ ጥያቄዎች መከሰታቸውም ሆነ ለእነዚህ ቀና ምላሽ የመስጠት ጉዳይ ህብረተሰብን ወደፊት የማራመድ ባህሪ ያለው ነው፡፡ ድክመቶቻችንን በተለይ ደግሞ በመንግስት ስልጣን ዙሪያ መታየት የጀመረውን ስህተት የማረም አስፈላጊነትም ቢሆን ይህ ቁልፍ የትግል መሣሪያ ለአገር ግንባታና የህዝብ ተጠቃሚነት እንዲውል በማድረግ ዕድገትን የማስቀጠል ባህሪ ያለው ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን በእርግጥም ተራማጅ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ዳግም የመታደስ ንቅናቄያችን የህብረተሰባችንን ተነቃናቂነትና በዚህም ውስጥ የብዙሃኑን ህዝብ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ህግጋትን የማክበር ባህሪ የተላበሰም ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ድክመቶቻችን የህብረተሰባችንን ወደፊት የመራመድ ሂደት መግታት ጀምረው ነበር፡፡ የአገልግሎት አሰጣጣችን ፈጣንና ቀልጣፋ ከመሆን ይልቅ ከተገልጋዩ ፍላጎት እኩል ያለመራመድ ችግሮች፣ ከውስጥም ከውጭም የሚታየውን የኪራይ ሰብሳቢነት አዝማሚያ በውል ከመታገል ይልቅ የመማረክ ችግሮች፣ መልካም አስተዳደርን በማስፈን የህዝብን ልማታዊ ቅልጥፍና ከማሻሻል ይልቅ ጥረቱን የማምከን ችግሮች ሁሉ ተዳምረው የህብረተሰባችንን ተናቃናቂነት ገድበውት ቆይተዋል፡፡ ይህ ለብዙ

ዓይነት ችግሮች እንድንዳረግና የማታ ማታ ደግሞ ተደጋጋሚ ግጭቶችና አለመረጋጋት የሰፈነበት ህብረተሰብ ወደመሆን እንድናመራ አድርጎን ቆይቷል፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ የህብረተሰባችን የተነቃናቂነት ደረጃ እየቀነሰ፣ መለምለም ጀምሮ የነበረውም ተስፋ እየጠወለገ መሄድ ጀምሮ ነበር፡፡ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን በእነዚህ ድክመቶች ላይ ያተኮረ መሆኑ የህብረተሰባችንን ተነቃናቂ ባህሪ የሚያዳክሙ ችግሮችን በመቅረፍ ዕድገታችንና ተነቃናቂነታችን ከበፊቱ በላቀ ደረጃ እንዲቀጥል ያስችላል፡፡ በዚህ ባህሪውም የህብረተሰብን የተነቃናቂነት ህግ የሚያከብር ተራማጅ እንቅስቃሴ ነው፡፡

እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን ሌላው ተራማጅ ባህሪ ዕድገታችን ላይ የተመሰረተና ውድቀታችን የሚወሰነው ህብረተሰብን ወደፊት የሚገፋውን ትክክለኛ ቅራኔ በመለየት ይህንኑ በሣይንሳዊና ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ እንድንፈታ የሚያደርገን ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የትኛውም ህብረተሰብ ለልዩ ልዩ ዓይነት ቅራኔዎች የተጋለጠ ነው፡፡ በህብረተሰብ ውስጥ የምናገኘው አንዳንዱ ቅራኔ መሰረታዊ ሌላው ደግሞ ኢ-መሰረታዊ ቅራኔ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አንዳንዱ ቅራኔ ውስጣዊ ሌላው ደግሞ ውጫዊ ቅራኔ ነው፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ ቅራኔዎች በህብረተሰብ ውስጥ የተለያየ ሚና የሚጫወቱ ሲሆን መሰረታዊና ውስጣዊ ቅራኔዎች የየትኛውንም ህብረተሰብ ህልውና ይወስናሉ፡፡ በአንፃሩ ኢ-መሰረታዊና ውጫዊ ቅራኔዎች ደግሞ የማንኛውንም ህብረተሰብ ህልውና የሚወስኑ አይደሉም፡፡ ይህም ሆኖ የኋለኞቹ ቅራኔዎች በህብረተሰብ ህልውና ላይ እንደ ሁኔታው ከቀላል እስከ ከባድ ተፅዕኖ የሚያሳርፉ ይሆናሉ፡፡ስለሆነም ማንኛውም ተራማጅ ባህሪ ያለው አስተሳሰብ በመሰረታዊና ውስጣዊ ቅራኔዎች ላይ በመመስረት እነዚህን በትክክለኛ አቅጣጫ የመመለስ ዕድልን ያጎናፅፋል፡፡ በአኳያው በህብረተሰብ ደረጃ የሚታዩ ቅራኔዎችን በትክክል ያለመረዳትና ያለመያዝ ችግር ህብረተሰብን ለዕድገት በማያበቃውና ህልውናውን በማይወስኑ ጉዳዮች ላይ እንዲሽከረከር በማድረግ መሰረታዊና ውስጣዊ ቅራኔዎች በአግባቡ እንዳይፈቱ ያደርጋል፡፡

እንደገና በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴያችን በዚህ መስፈርት ሲለካ መሰረታዊና ውስጣዊ ቅራኔዎችን በትክክል በመለየትና ፋይዳቸውን

በመገንዘብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ለምሳሌ በቅርቡ የተከሰቱትን ግጭቶች ለመፍታት በተደረገው እንቅስቃሴ ድርጅታችን የሁሉም ችግሮች ምንጭ ውጫዊ ሳይሆን ውስጣዊ ሁኔታችን ነው በማለት በግልፅ የቅራኔውን ምንጭ አስቀምጦታል፡፡ ዕድገታችንን ከኪራይ ሰብሳቢ ዝንባሌ ተፅዕኖ ነፃ በማድረግ የተጀመረውን ሂደት አጠናክሮ የማስቀጠል ፍላጎት መሰረታዊና ውስጣዊ ነው፡፡ ከስኬታችን ጋር ተያይዘው የመጡ አዳዲስ የህብረተሰብ ጥያቄዎችም ውስጣዊ ናቸው፡፡ በድክመቶቻችን የተነሳ የሚታየው የህዝብ ቅሬታም መሰረታዊና ውስጣዊ ጉዳይ ነው፡፡ በአንፃሩ ከፅንፈኛ ተቃዋሚ ኃይሎች እስከ ዓለም አቀፍ የቀለም አብዮተኞች ድረስ ያሉ ኃይሎች ቀላል የማይባል አሉታዊ ሚና የሚጫወቱ እንደሆኑ ባያጠያይቅም፣ በዋነኛነት የችግሩ ምንጮች እንዳልሆኑና የህብረተሰባችንን ዕድል እንደማይወስኑ ተቀምጧል፡፡ በዚህ የተነሳ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን በህብረተሰባችን መሰረታዊና ውስጣዊ ቅራኔዎች ላይ የተገነባና እነዚህንም ሳይንሳዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል ባህሪ የተላበሰ ነው፡፡ ስለሆነም ደግሞ እንደገና የመታደስ ንቅናቄያችን በእርግጥም ተራማጅ ባህሪ ያለው ነው፡፡

የንቅናቄው ተራማጅ ባህሪ የሚገለፅበት ሌላው ጉዳይ የብዙሃኑን ህዝባችንን መብትና ጥቅሞች ማዕከል ያደረገ ንቅናቄ መሆኑ ነው፡፡ በህብረተሰብ ውስጥ የሚካሄዱ ችግሮች ተራማጅነት ወይም ኋታችነት ከሚለካባቸው መስፈርቶች አንዱና ዋናው የብዙሃኑን መብትና ጥቅም ለማስከበር ያለው ፋይዳ ነው፡፡ ማንኛውም የብዙሃኑን መብትና ጥቅም ታሳቢ በማድረግ የሚቀረፅና ተግባራዊ የሚደረግ ሃሳብ ተራማጅ ነው፡፡ በአንፃሩ በብዙሃኑ መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስ አስተሳሰብና ተግባር ደግሞ በማንኛውም መስፈርት ቢለካ ኋታች እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን ከዚህ አኳያ ሲመዘን እጅግ ተራማጅ ባህሪ የተላበሰ ነው፡፡ መነሻና መድረሻው የህዝባችን መብትና ጥቅም ነው፡፡ ድርጅታችን ሁሌም እንደሚያደርገው የትግሉ አልፋና ኦሜጋ የህዝብ መብትንና ጥቅምን ማክበርና ማስፋት ነው፡፡ ትጥቅ ትግሉ የተካሄደውና ከባድ መስዋዕት በመክፈል የተሳካው ለህዝብ መብትና ጥቅም መከበር ነው፡፡ ከሽግግሩ ወቅት ጀምሮ እስከ መጀመሪያው ተሃድሶ የተካሄዱት ትግሎችና ጥረቶች

ሁሉ ማዕከላቸው የህዝብ መብትና ጥቅምን ማስከበርና ማስፋት ነበር፡፡ ዛሬም እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን ጉዳይ ሲነሳ ከዚሁ የህዝብ መብትና ፍላጎት በመጀመር ነው፡፡ የመንግስት ስልጣንን ለህዝብ መገልገያ የማድረግ ሃሳባችን ችግር እንደገጠመው በመገንዘብ፣ ይህን ለማስተካከል መካሄድ የጀመረው እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ግቦቹ ህዝባዊ መብትና ጥቅምን ማስከበር ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ስለሆነም ተራማጅና የህብረተሰብን ችግር በትክክለኛው አቅጣጫ የመፍታት ባህሪ ያለው ንቅናቄ ነው፡፡

### 3.2 ድርጅታችንን ለማደስ ቅድሚያ የሚሰጥና ይህንኑ የማሳካት ችሎታ ያለው ንቅናቄ

እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን የመጀመሪያውን ተሃድሶ ስኬቶች በመጠበቅና ያጋጠሙንን ድክመቶች በማረም ላይ የተመሰረተ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዋነኛነት የሚያተኩረው ድርጅታችንን እንደገና በማደስ ላይ ይሆናል፡፡ በዚህ ባህሪው ስርዓታችን በጀመረው መልካም መንገድ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ድክመቶቻችንን በአስተማማኝ ደረጃ እንዲታረሙ ያደርጋል፡፡ በተሃድሶ መስመራችን በውል እንደተቀመጠው በአገራችን የሚካሄደው ለውጥ በዋነኛነት ሶስት የለውጥ አቅሞች በከፍተኛ ትስስር የሚያከናውኑት ነው፡፡ እነዚህ ኃይሎች የለውጥ ሃሳቦች ያመነጨው ድርጅታችን፣ ይህንኑ ሃሳብ ህጋዊ ባህሪ አላብሶ የሚያስፈፅመው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስታችንና የለውጡን ሃሳብ በተሳካ ሁኔታ የሚፈፅመው ህዝባችን ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሶስት ወሳኝ የለውጥ አቅሞች መካከል ትልቁ የመሪነት ሚና በድርጅታችን ትከሻ ላይ ያረፈ ሲሆን ድርጅታችን ይህን የለውጥ ሃሳብ እያመነጨ መላውን መንግስታዊ አስፈፃሚ ኃይልና ህዝባችንን በዚህ የለውጥ ሃሳብ ዙሪያ በማረባረብ የማሳካት ግንባር ቀደም ሚና ይጫወታል፡፡

ይህ በራሳችን አጭር የለውጥ ጉዞ የታየ ሲሆን፣ ድርጅታችን ለአደጋ በተጋለጠ ቁጥር ለጊዜውም ቢሆን የለውጥ ሃሳባችን በተፈላጊው ደረጃ ተግባራዊ ሳይሆን እንደሚቀር ታይቷል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በመንግስት ስልጣን አተያየና አጠቃቀም ዙሪያ የተከሰተው ድክመት ድርጅታችንን በዚህ የተሳሳተ ዝንባሌ እንዲለከፍ በማድረጉ የተነሳ

ተልዕኮዎችን በብቃት መፈፀም ተስኖት ቆይቷል፡፡ ይህን ከግንዛቤ በማስገባት እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን የድርጅታችንን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ባህሪ የመጠበቅና የማጎልበት ባህሪ እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ ድርጅታችን የመንግስት ስልጣንን የሚፈልገው ግለሰቦችን ለመጥቀምና የህዝብን መብትና ጥቅም ለመርገጥ ሳይሆን ህብረተሰባዊ ለውጥን ለማምጣትና በዚህም ለውጥ ብዙሃኑን ህዝብ ለመጥቀም ሲል ብቻ እንደሆነ ተሰምሮበታል፡፡ ከዚህም አልፎ ማንኛውም ድርጅታችንን የስልጣን መወጣጫ ለማድረግ የሚካሄድ እንቅስቃሴ በጥብቅ ሊመከትና ለጎራ መደበላለቅ የዳረገን ብልሹ የስልጣን አተያይ እንዲስተካከል መደረግ እንዳለበት የንቅናቄው ግብ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ ድርጅታችንን የስልጣን መወጣጫ ለማድረግ የሚካሄድ ማናቸውም እንቅስቃሴ ፈፅሞ ተቀባይነት የሌለውና በትግል ሊታረም የሚገባው ተደርጎ የተወሰደውም በዚህ የተነሳ ነው፡፡

የድርጅታችንን ተራማጅና ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ባህሪ መልሶ በመገንባት ላይ የሚያተኩረው እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን በአንድ በኩል ከዚህ ቀደም ያዳበርናቸውን ጥራት ያላቸውን የትግል መስመሮች የማስረፅና በውጤታማነት ተግባራዊ የማድረግ ባህሪ አለው፡፡ ቀደም ሲል ታላቁ መሪያችን ጓድ መለስ ዜናዊ በጥልቅ ጥናታዊ ምርምር የደገፋቸውና ድርጅታችንም አዳብሮ ተግባራዊ ሲያደርጋቸው የቆዩ የትግል መስመሮቻችን በጥገኝነት ምክንያት ይደርስባቸው ከነበረው አሉታዊ ተፅዕኖ ተላቀው በላቀ ውጤታማነት ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ ሆኖ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል በመስመራችን ትግበራ የተፈጠሩ አዳዲስ ሁኔታዎችና ምላሽ የሚፈልጉ ጥያቄዎች ደግሞ ይገኛሉ፡፡

ስለሆነም እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን በአንድ መኩል መስመራችንን በጥልቀት እየተገነዘብን ተግባር ላይ በማዋል በሌላ በኩል ደግሞ ከራሳችንና ከሌሎች ልምድ በመነሳት ይህንኑ እያበለፀግን ሁሌም በሚያድግ ቅኝት ህብረተሰባችንን መምራት ይሆናል፡፡ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን ሁለተኛ ባህሪ ድርጅታችንን ከልዩ ልዩ ባዕድ ዝንባሌዎች በመጠበቅና በመከላከል እንዲሁም ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመራችንን በጥልቀት በመገንዘብና በማስተካከል ላይ የተመሰረተ ባህሪ የተላበሰው ከዚህ በመነሳት ነው፡

የድርጅታችንን አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ባህሪ የማጎልበት ተልዕኮ ይዞ የሚካሄደው እንደገና የመታደስ እንቅስቃሴ እዛው ሳለም ሌሎች ተጨማሪ ለውጦችን ለማስመዝገብ የሚያልም ነው፡፡ በዚህ ረገድ ቀዳሚ ተደርጎ የሚወሰደው የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲን የማስፋት ጉዳይ ይሆናል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠው ደግሞ ተቋማዊ አሰራርንና አደረጃጀቶችን ማጠናከር ይሆናል፡፡

ድርጅታችን ያነገባቸውን ትክክለኛ ዓላማዎች ለማሳካት ከምንም በላይ የሚተማመነው በአባላቱና በህዝቡ ነው፡፡ አባላትና ህዝብ የድርጅታችንን ዴሞክራሲያዊ ዓላማ አንግበው በመንቀሳቀስ ለተፈፃሚነቱ ካልተረባረቡ በስተቀር ተፈላጊው ውጤት እንደማይገኝ አያጠራጥርም፡፡ በሌላ በኩል አባላትና ህዝብ በሙሉ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ሊረባረቡ የሚችሉት ደግሞ በተሟላ የውስጠ ድርጅት ትግል ታግዘው ሲንቀሳቀሱና በከፍተኛ የራስ መተማመን ሲረባረቡ ነው፡፡ ድርጅታችን ከዚህ መሰረታዊ እምነት በመነሳት በውስጡም ዴሞክራሲን እያሰፈነ ተጉዟል፡፡ በእኛና በፀረ-ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች መካከል ከሚታዩት መሰረታዊ ልዩነቶች አንዱ በዴሞክራሲ ጥያቄ ረገድ ያለን ልዩነት የሆነበት ምክንያትም ይኸው ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ኪራይ ሰብሳቢነት በራሳችን ድክመትም ሆነ በሌላ ምክንያት መስፋፋት ሲጀምር ዴሞክራሲያችን ለአደጋ እንደሚጋለጥ ታይቷል፡፡ የኪራይ ሰብሳቢነት የበላይነት ባለበት ሁኔታ ፀረ-ዴሞክራሲ በእኛ ውስጥ ብቻ ሳይታጠር እስከ ህብረተሰቡ ድረስ ዘልቆ ይስፋፋል፡፡ በዚህ የተነሳ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየገነገነ የመጣው ኪራይ ሰብሳቢነት ውስጣዊ ዴሞክራሲያችንን በመጫን መላወሻ ምህዳሩን ሲያጠበው ቆይቷል፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነትን የሚጠሉና አምርረው የሚፋለሙ ታጋዮችን ለልዩ ልዩ ዓይነት ጥቃቶች ከማጋለጥ ጀምሮ አድርባይነትና ቸልተኝነትን ሲያበረታታ ቆይቷል፡፡ ይህም እንደገና የድርጅታችንን ራሱን በራሱ የማረም ችሎታ እያዳከመ ለችግሩ መባባስ የበኩሉን አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡

ይህን መነሻ በማድረግ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲን የማዳበር ተልእኮ እንዲሸከም ተደርጓል፡፡ ማንኛውም ዓይነት ትክክለኛ ይሁን የተሳሳተ ሃሳብ ካለምንም ፍርሃት በነፃነት የሚገለፅበትና የሚደመጥበት ሁኔታ ሊጠናከር እንደሚገባው፣ በተለይ ደግሞ ፀረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ይዘት ያላቸው ሃሳቦች ፈፅሞ እንዳይደፈቁ የማድረግ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ ሃሳቦችን የመግታት ዝንባሌ ምንም ዓይነት ሽፋን

ይኑረው ፀረ-ዴሞክራሲና ለኪራይ ሰብሳቢነት ብቻ የሚያመች እንደሆነ በመገንዘብ፣ ማንኛውም ሰው ከዚህ ዓይነቱ ዝንባሌ እንዲላቀቅ ልዩ ትግል ሊደረግ እንደሚገባውና ከዚሁ በማይነጠል መልኩ እያንዳንዱ ታጋይ ራሱን ችሎ አቋምና ኃላፊነት ሊወስድ እንደሚገባው፣ ስለዚህም ደግሞ ራሱን ከማንኛውም ዓይነት የጥገኝነት መረብና ቡድን ነፃ ማድረግ እንዳለበት ተሰምሮበታል፡፡

እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን የድርጅታችንን አብዮታዊና ዴሞክራሲያዊ ባህሪ ለማጠናከር ያስቀመጠው ሌላው አቅጣጫ የዴሞክራሲ ተቋሞቻችንን ማጠናከርና ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የየራሳቸው ተልዕኮ እንደተጠበቀ ሆኖ ከድርጅት አኳያ የቁጥጥርና ኦዲት እንዲሁም የኢንስፔክሽን ተቋሞቻችን እንዲጠናከሩና ሌሎች እንደ አመራር ት/ቤቶች፣ የልሳን ዝግጅት ክፍሎችና የምርምር ተቋማት የመሳሰሉት አቅም መገንቢያ ተቋሞቻችንም በአጭር ጊዜ ተፈላጊው የጥራትና ጥንካሬ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ እንደሚገባ ታምኖበታል፡፡

## 3.3 ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስትን የማጠናከር ባህሪ ያለው የመታደስ ንቅናቄ

አገራችን የተያያዘችውን የለውጥ ሂደት ለማሳካት ጠንካራ መንግስት እንደሚያስፈልጋት እሙን ነው፡፡ ባለፉት በርካታ ዓመታት በአገራችን ውጤታማ መንግስት ለመገንባት የተካሄደው ትግልም ከዚህ መሰረታዊ ጉዳይ የተነሳ ነበር፡፡ ለማንም ግልፅ እንደሚሆነው እንደ እኛ በመሰሉ ያልበለፀጉ አገሮች ምን ዓይነት መንግስት ሊኖር ይገባዋል የሚለው ጉዳይ ከፍተኛ ክርክር የሚካሄድበት ነው፡፡ በአንድ በኩል በዓለማችን የበላይነት ይዞ የቆየው ኒዮ-ሊበራል አስተሳሰብ ባልበለፀጉ አገሮች መገንባት ያለበት መንግስት ትንሽና ደካማ መሆን አለበት ይላል፡፡ ኒዮ-ሊበራሊዝም ሁሉም ችግሮች በገበያውና በባለሃብቱ ሊፈቱ ስለሚችሉ የመንግስት ኢኮኖሚያዊ ጣልቃ ገብነት ሊኖር አይገባም ይላል፡፡ ህግ በማስከበር ተግባር ላይ ብቻ የተወሰነ፣ አንዳችም ልማታዊ ሚና የማይጫወት መንግስት መኖር አለበት እስከ ማለት ይደርሳል፡፡ መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ ሲገባ ሙስናና አድሎ መፈፀሙ ስለማይቀር ከኢኮኖሚው ላይ እጁን ማንሳት አለበት ይላል፡፡ እናምያልበለፀጉ አገሮች ደካማና ምንም መስራት የማይችል

መንግስት ሊኖራቸው ይገባል እስከማለትም ይደርሳል፡፡ የሚቆጣጠራቸው ጠንካራ ልማታዊ መንግስት ያጋጠማቸው ጥገኞች ደግሞ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የልማታዊ መንግስቱን አቅም ለማዳከም ይሰራሉ፡፡ በኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ የተበከሉ ኃይሎች መንግስት የእነሱ ተቀጥላና ተገዢ እንዲሆንና ስልጣንን በእጃቸው እስኪያዙ ድረስ በዚሁ ስልጣን ታግዘው ማንኛውንም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግበስበስ ይሰራሉ፡፡

የመንግስት ስልጣንን ከእነዚህ ለየት በሚል ቅኝት የሚመለከተውና የሚጠቀምበት ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ብቻ ነው፡፡ በዚህ ኃይል አስተሳሰብ መሰረት የገበያ ስርዓት በራሱና በባለ ሃብቱ ሚና ብቻ ከችግር ነፃ ወይም እንከን የሌለበት ተደርጎ አይወሰድም፡፡ ይልቁንም ስርዓቱ በተፈጥሮው ለጥቂቶች የማድላት ባህሪ ያለውና ራሱን በራሱ ለማረም የሚቸገር ስርዓት ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ገበያው በጣም ብዙ ጉድለቶች ያሉበት፣ ስለዚህም ደግሞ በጥብቅ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ሁሌም እየተስተካከለ ሊሄድ የሚችልና የሚገባው ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ለምሳሌ የገበያ ስርዓት ሁሉም ነገር በገንዘብ ሊሸጥ ይገባዋል በሚል አስተሳሰብ የተዋቀረ በመሆኑ በዚህ ስርዓት ትምህርትም ሆነ ቴክኖሎጂ በዋናነት የሚቀርበው መክፈል ለሚችሉ ብቻ ይሆናል፡፡ ማንኛውም መሰረተ ልማት የሚገነባው በአዋጭነት መርህ በመሆኑ የለማ ገበያ በሌላቸውና አትራፊ ባልሆኑ አካባቢዎች ሁሉ የመሰረተ ልማት አገልግሎትን ለማስፋፋት አይተጋም፡፡ በሰለጠኑ አገሮች በጥቂት ከተሞችና በብዙ ገጠሮች መካከል የሚታየው የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ልዩነት ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ስለሆነም ልማታዊ መንግስታት ይህን የገበያ ስርዓት ተፈጥሮአዊ የሚዛን መዛባት /Inherent Imbalance/ በመንግስት የተመረጠ ጣልቃ ገብነት ማረምና ማስተካከል ተገቢ ይሆናል ብሎ ያምናል፡፡ የገበያ ስርዓት መብትና ጥቅማቸውን የማያስከብርላቸው ወገኖች ብዙሃኑና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ስለሆኑ የእነሱን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍላጎት መነሻ የሚያደርግ ጣልቃ ገብነት በጥብቅ ይታመንበታል፡፡ ይህም ሆኖ መንግስት ጣልቃ ይግባ ሲባል ራሱ መንግስት ማለት ምንም እንከን የማይታይበት ተቋም ነው በማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም በመንግስት በኩልም ቀላል የማይባል ጉድለት እንደሚኖር ታሳቢ ሊደረግ ይገባዋል፡፡ የመንግስት ስልጣንን የግል መጠቀሚያ የማድረግ

ዝንባሌ ለዚህ እንደ አንድ ማረጋገጫ ሊቀርብ ይችላል፡፡ መንግስት በሙስናና አድሎ ተበክሎ ልማታዊ ተልዕኮውን መፈፀም ተስኖት ፀረ-ዕድገት ሚና እንዳይጫወት ለማድረግ የሚቻለው ይህን ጉድለት ተቀብሎ ለማስተካከል በሚደረግ ያልተቆጠበ ጥረት ብቻ ነው፡፡

በአገራችን ከዚህ መሰረታዊ ግንዛቤ በመነሳት ጠንካራ ልማታዊ መንግስት የመገንባት ተልዕኮ ተሸክመን ስንቀሳቀስ ቆይተናል፡፡ ከገጠር እስከ ከተማ ጠንካራና ግዙፍ መንግስት ገንብተናል፡፡ የኒዮ-ሊበራል ኃይሎች ተቃውሞ ሳይለየን አገራዊ ለውጡን የሚያቅድና የሚያስፈፅም ጠንካራ መንግስት ፈጥረናል፡፡ በዚህ መንግስት እየተመራን ላለፉት በርካታ ዓመታት አገራችንን ከማሽቆልቆል አውጥተን በዕድገት ጎዳና አረማምደናል፡፡ ሚሊዮኖችን ከድህነት በማላቀቅ ለተሻለ የኑሮ ደረጃ አብቅተናል፡፡ እነዚህ የልማታዊ መንግስታችን ትሩፋቶች እንደተጠበቁ ሆነው በሂደት ልማታዊ መንግስታችን ለልዩ ልዩ አደጋዎች መጋለጥ እንደጀመረም ተመልክተናል፡፡ በህብረተሰብ ውስጥ ያለው የኪራይ ሰብሳቢነት አዝማሚያ መንግስትን ጭምር እየበከለ በልማታዊ ተልዕኳችን አፈፃፀም ላይ ጫና ሲያሳርፍ ቆይቷል፡፡

ከዚህ በመነሳት እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችን አንድ መሰረታዊ ባህሪ የመንግስትን ጤንነት የመጠበቅና ለውጤታማ የተልዕኮ አፈፃፀም እንዲበቃ ማድረግ መሆኑ ተሰምሮበታል፡፡ መንግስት በየትኛውም እርከን ላይ ከሚታዩ የኪራይ ሰብሳቢነት አዝማሚያዎች ተጠብቆ እንዲጠናከርና ዕድገታችን በሚጠይቀው ልክ ጣልቃ እየገባ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ተልዕኮዎችን የሚፈፅም እንዲሆን ተሰምሮበታል፡፡ በመንግስት ስልጣን አጠቃቀም ረገድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተሳሳተ ከባድ ተፅዕኖ የመጣው ከራሱ ከድርጅታችን እንደሆነ በመገንዘብ የመንግስት ውጤታማ የተልዕኮና የእቅድ አፈፃፀም ከምንም ነገር በላይ ክብደት እንዲሰጠው ተደርጓል፡፡ የፓርቲ ከፍተኛ አመራር ኃላፊነት በመንግስት ስልጣን ላይ ለመቀመጥና ለመቆየት ብቸኛውም ሆነ ዋናው መስፈርት መሆን እንደሌለበት ተሰምሮበታል፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት አገራዊ ለውጡን የማቀድና የማስፈፀም ብቃት እንዲኖረው በማድረግ ከድርጅታችን ውስጥም ሆነ ከውጭ ብቁ ሰዎች እየተለዩ በአስፈፃሚው የኃላፊነት ቦታ ላይ እንዲመደቡ መደረግ

እንደሚገባው ታምኖበታል፡፡ በዚህም በሁሉም ደረጃዎች የሚካሄደውን ምደባና መልሶ ማደራጀት ተከትሎ ሰፋፊ የአቅም ግንባታ ስራዎች መካሄድ እንዳለባቸው ተቀምጧል፡፡ የመንግስትን የስራ አፈፃፀም ለማጠናከር የሚያግዙና የተጀመረውን ልማታዊ ሂደት የሚያጠናክሩ አቅጣጫዎች ተተልመው ወደ ትግበራ ሽግግር ይደረጋል፡፡ በዚህ ረገድ መንግስትን ለኪራይ ሰብሳቢነት ይበልጥ የሚያጋልጡ ተለይተው እነዚህን በጥብቅ ለማስተካከልና ከኪራይ ሰብሳቢነት ለማፅዳት በሚያስችል ቅኝት ሂደቱን ለመምራት ጥረት ይደረጋል፡፡ በተለይ ደግሞ የኮንትራት አስተዳደርን፣ የመንግስት ግዥ አፈፃፀምን፣ እንዲሁም የግብር አሰባሰብና የመሬት ዕደላን ለሚያከናውኑ ተቋማት ልዩ ትኩረት በመስጠት የማስተካከል እንቅስቃሴ ይካሄዳል፡፡

መንግስት ልማታዊ ተልዕኮውን በአግባቡ ይፈፅም ዘንድ አገራዊና ክልላዊ የዴሞክራሲ ተቋሞቻችን እንዲጠናከሩ መደረግ እንዳለበት ታምኖበታል፡፡ በአገራችን ኪራይ ሰብሳቢነትን ለማዳከምና በቁጥጥር ስር ለማስገባት መካሄድ ያለበት ትግል ተቋማዊ መንገድ ይዞ ጭምር መካሄድ እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ከዚህ ትግል ውጭ ኪራይ ሰብሳቢነትን ማዳከምም ሆነ ማሸነፍ አይቻልም፡፡ ስለሆነም ለዚህ ትግል ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ አስተዋፆ የሚያደርጉ ተቋማት ሁሉ እንዲጠናከሩና ተልዕኳቸውን በአግባቡ እንዲፈፅሙ ይደረጋል፡፡ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌደሬሽን ምክር ቤቶች፣ የዕንባ ጠባቂና የሰብዓዊ መብት ኮሚሽኖች፣ የአቃቢ ህግና የፀረ-ሙስና ተቋማት፣ ፍርድ ቤቶች፣ ሚዲያና መሰል ተቋማት እንዲጠናከሩና ኪራይ ሰብሳቢነት የሚፈጥራቸውን ችግሮች በጥብቅ እንዲታገሉ መደረግ እንዳለበት ተቀምጧል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት የስራ አፈፃፀም ሂደታችን ምን እንደሚመስልና በየደረጃው የሚገኙ አስፈፃሚ አካላት የስራ አመራርና ስነ-ምግባራዊ ደረጃ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ የሚከታተሉና የሚያጣሩ የኢንስፔክሽን ተቋማት እንዲኖሩና እንዲጠናከሩ መደረግ እንዳለበት ተወስኗል፡፡ ከእነዚህ መሰረታዊ አቅጣጫዎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው እንደገና በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴያችን የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስታችንን ባህሪ፣ ተልዕኮና የመፈፀም ብቃት የሚያጠናክሩ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

## 3.4 ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለላቀ አፈፃፀም የሚያበቃ የመታደስ ንቅናቄ

አገራችን በተሃድሶ አቅጣጫ እየተመራች ዘርፈ ብዙ ለውጦች ካመጣችና የዳበረ የአፈፃፀም ልምድ ካካበተች በኋላ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የሚያመጣ ዕቅድ በማዘጋጀት የመጀመሪያውን አምስት ዓመት በስኬት አጠናቃለች፡፡ ከዚህ ስኬት በመነሳት ሁለተኛውን የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አዘጋጅታ ወደ ትግበራም ተሸጋግራለች፡፡ ይህም ሆኖ ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ዕትዕ) ተግባራዊ ማድረግ በጀመርንበት ዓመት የአፈፃፀማችንን ውጤታማነት ገደብ ያሳረፉበት ሁለት ምክንያቶች አጋጥመውናል፡፡ የመጀመሪያው ከፊል አቅማችንን የግድ ማረባረብ እንዲኖርብን ያደረገው የድርቅ አደጋ ነው፡፡ ሁለተኛው አደጋ ደግሞ ሰፋ ያለ ቦታን የሸፈነና ዓመቱን በሙሉ ያልተላቀቀን ግጭትና ያለመረጋጋት ነበር፡፡ ሁለቱም ፈፅመው ያልታሰቡና ያልተዘጋጀንባቸው ስለሆኑ በድርጅታዊና በመንግስታዊ አመራራችን ላይ ተጨማሪ ከባድ ሸክም የጫኑ ነበሩ፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈፃፃም የሚያጓትት ተፅዕኖ ያደረጉ ነበሩ፡፡ ስለሆነም ሁለተኛው የዕትዕ የታሰበውን ያህል ለውጥ እንዲያመጣ ከተፈለገ በቀሪዎቹ አራት ዓመታት ከፍተኛ ርብርብ ማድረግይገባናል፡፡ ይህ ደግሞ ከያዝነው ዓመት በመጀመር መፈፀም ያለበት ተግባር ነው፡፡

በዚህ መሰረት መላ ድርጅታዊና መንግስታዊ አቅማችንን የባከነውን ጊዜ በሚያካክስ ቅኝትና ተነሳሽነት ለማረባረብ መዘጋጀት ይገባናል፡፡ አገራችን የዜጎቿን ህይወት ያለማቋረጥ ለማሻሻል የምትችለው ያላትን ተፈጥሯዊ ፀጋ በማልማትና በመጠቀም ብቻ ነው፡፡ ይህም በገጠር የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን መሬት ከህዝቡ ጉልበት ጋር አዋህዶ በማልማት እውን የሚሆን ነው፡፡ በከተሞችም ለወጣቶችና ሴቶች የሚሆኑ የሃብትና ስራ ፈጠራ ዕድሎችን በማስፋት የሚፈፀም ነው፡፡ ስለሆነም በዕቅዳችን ተዘርዝረው የተቀመጡ ተግባራትን ከየአካባቢያችን ሁኔታ ጋር በማዛመድ በልዩ ርብርብ ማስፈፀምና የላቀ ውጤት ማስመዝገብ ይገባናል፡፡ ይህን ከፀረ-ጥገኝነት ትግላችን ጋር አዋህደን እስከፈፀምነው ድረስ አገራዊውን የፖለቲካ ኢኮኖሚ በአጭር ጊዜ በምንፈልገው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ የመገንባት ዕድላችን እየሰፋና እውን እየሆነ ይሄዳል፡፡ ከዚህ በመነሳት

እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄዎችን ሁለተኛውን ዕትዕ ለማሳካት ሲባልና በማሳካትም ሂደት መፈፀም ያለበት መሆኑ ተሰምሮበታል፡፡

### 3.5 አፍራሽ ኃይሎችን ለመመከት ትግሉ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የመታደስ ንቅናቄ

በቅርቡ የተቀሰቀሱት ሁከቶች በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት ላይ የተከሰቱ የራሳችን ችግሮች የፈጠሯቸው እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ አንድም ዕድገታችን የወለዳቸውን አዳዲስ ፍላጎቶች ማርካት ባለመቻላችን፣ አሊያም ደግሞ ድክመቶቻችንን በጊዜ ባለማረማችን የተከሰቱ ችግሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም አለመረጋጋቱን ልንቀርፍ የምንችለው እነዚህን የራሳችንን ችግሮችና ድክመቶች በመፍታት ብቻ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የራሳችን ድክመት በፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ በመታገዝ አፍራሽ ሃይሎች ከባድ ተፅዕኖ ሊያደርሱብን ተረባርበዋል፡፡ ማህበራዊ ድረ ገፆች በከፈቱላቸው ዕድል በመጠቀምና በሌሎች ልዩ ልዩ ስልቶች በመታገዝ ጊዜያዊውን ቀውስ ሊጋልቡት ሞክረዋል፡፡ለዚህም እንዲያመቻቸው እጅግ ኋላ ቀርና ዘረኛ አጀንዳዎች ቀርፀው ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ከአገር ውስጥ ፅንፈኛና የሽብር ኃይሎች በተጨማሪ ከኤርትራ መንግስት እስከ ግብፅ፣ አውሮፓ ፓርላማ ውስጥ ከተሰገሰጉት ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች እስከ ዓለም አቀፍ የቀለም አብዮተኞች ጋር ተቀናጅተው ተረባርበዋል፡፡ ምንም እንኳ በኢትዮጵያ ያለውን ለውጥና ተስፋ ተከትሎ ህዝባችን ለእነዚህ ኃይሎች ፕሮፖጋንዳ መሣሪያ እንደማይሆን ቢያሳይም የቻሉትን ያህል አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍል በማደናገር ወደ ሁከት ለማስገባት ሞክረዋል፤ ወደፊትም መሞከራቸው አይቀርም፡፡

ከዚህ በመነሳት እንደገና በጥልቀት ለመታደስ የምናካሂደው ንቅናቄ የራሳችንን የስርዓት ችግሮች ለመፍታት ቅድሚያ መስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ እነዚህ አፍራሽ ኃይሎች የሚያካሂዱትን የጥፋት እንቅስቃሴ ለመመከትና ለማክሸፍ የሚያልም ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ አፍራሽ ኃይሎች ሁሌም የተሻለ ዕድል የሚያገኙት ሰላምና መረጋጋት ሲደፈርስና በህብረተሰቡ ውስጥ እርግጠኝነት የማጣት ስሜት ሲፈጠር እንደሆነ በመገንዘብ ልማት፣ ዴሞክራሲና ሰላምን የማጠናከር እንቅስቃሴያችን ለውጤት እንዲበቃ መረባረብ ይኖርብናል፡፡ ከአስራ አምስት ዓመታት የተሃድሶ ንቅናቄና በዚሁ ከተመዘገበ አንፀባራቂ ስኬት በመነሳት ሲታይ ኢትዮጵያን የማተራመስ ዕድል የቀን ህልም ቢሆንም በዚህ ከንቱ ምኞት የተነሳ የማንም ዜጋ ህይወት ማለፍ የለበትምና ለአስተማማኝ ሰላም በመረባረብ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄያችንን እናሳካ፡፡

የመጀመሪያው ተሃድሷችንን ስለሁለተኛው በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄ ዋቢ እናድርግ ከተባለ በስኬት ጎዳና ከመረማመድ ውጭ ሌላ ውጤት አንጠብቅም፡፡ ኢትዮጵያና ህዝቦቿ በመታደስ ጎዳና ወደፊት ከመራመድ ውጭ ሌላ ዕድል የላቸውምና፡፡ ድርጅታችንና ልማታዊ መንግስታችንም ጭምር፡፡

# የወጣቶችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እናረጋግጥ!!

## 1. መግቢያ

ኢህአዴግና አባል ድርጅቶቹ ወትሮም እንደሚያደርጉት ሁሉ ዛሬም በየምዕራፉ የተጓዙበትን ርቀት፣ በጉዟቸው ውስጥ ያሳኳቸውን ግቦችና የነበሩባቸውን ጉድለቶች፣ ያጋጠሟቸውን መሰናክሎችና የፈቱበትን አግባብ በጥሞና ገምግመዋል፡፡ በትጥቅ ትግሉ ወቅትም ሆነ የደርግ መንግስት ከወደቀ በኋላ በነበሩት መድረኮች ለድል ያበቃቸው ዋነኛው ምስጢርም ይሄው የግምገማ ልምዳቸውና ራሳቸውን በራሳቸው የማረም ባህሪያቸው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህንን መሰረታዊ ባህሪ የሳቱ እለት ያለአንዳች ጥርጥር ወደ ውድቀት እንደሚያመሩ ስለሚገነዘቡም ሁሌም ራሳቸውን ይገመግማሉ፤ ይታደሳሉ፡፡ እነሆ በቅርቡ የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የኢሕአዴግ ምክር ቤት የኢህአዴግና የአባል ድርጅቶቹን ያለፉት 15 አመታት ጉዞ በዝርዝር ገምግመዋል፡፡ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄ እንዲካሄድም ወስነዋል፡፡ በኢህአዴግ ደረጃ የተካሄደውን ግምገማ መነሻ በማድረግም በየብሔራዊ ድርጅቶቹ ከማዕከላዊ ኮሚቴ ጀምሮ መላ የድርጅቱን አባላትና ህዝቡን ያካተተ ግምገማና የተሃድሶ ንቅናቄ ማካሄድ ተጀምሯል፡፡

እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄው ሰሞኑን በአንዳንድ የአገራችን ክፍሎች በተከሰተው ግጭት ምክንያት የተወሰነ አይደለም፡፡ ከግጭቱ መከሰት በፊት በተለይም ደግሞ አምና በተካሄዱት የአባል ድርጅቶችና የኢህአዴግ ጉባኤዎች በስፋት የተገመገሙትን ችግሮች መሰረት በማድረግ በአመቱ ውስጥ በተለያየ አግባብ በየድርጅቱና በኢህአዴግ ደረጃ ሲካሄድ የቆየውን የውስጠ ድርጅት ትግል ወደ ከፍተኛና ስር ነቀል ለውጥ የሚያመጣ ትግል ለማሸጋገር የተላለፈ ውሳኔ ነው፡፡

እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄው በድርጅት፣ በድርጅት አመራርና አባላት ጀምሮ ወደ ህዝቡ በመውረድ በላቀ ግለት እንዲቀጥልና

መልሶም ድርጅቱን በእሳት እንደሚፈተን ወርቅ ነጥሮ እንዲወጣ በማድረግ የአገራችንን ህዳሴ በላቀ ፍጥነትና ውጤታማነት የማስቀጠል አላማ ያለው ነው፡፡ በዚህ ሂደት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ከሚጠበቁት የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ወጣቱ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ ወጣቱ በትናንት ሳይሆን በዛሬና በነገ የሚኖር፣ በህብረተሰብ የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ አዳዲስና የለውጥ ሃሳቦችን ፈጥኖ የሚቀበል፣ አፍላ ጉልበትና ንቃት ያለው ትኩስ ህብረተሰባዊ ሃይል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ወጣት ደርግን ለመጣል በተደረገው ትግል፣ ከደርግ ውድቀት በኋላም አገሪቱን በማረጋጋትና የኤርትራ መንግስትን ወረራ በመመከት፣ እንዲሁም ኢህአዴግ በቀዳማይ ተሃድሶው የቀየሳቸውን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በመገንባት እንቅሰቃሴዎች በንቃት በመሳተፍ፣ በአጠቃላይ የአገራችንን ህዳሴ በማብሰር ረገድ የነበረው ተሳትፎ የትናንት ታሪክ ተብሎ የሚታለፍ ብቻ አይደለም፡፡ ዛሬ ኢህአዴግ በቀየሰው እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄም ወጣቱ ብቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

ወጣቱ በተሃድሶ ንቅናቄው በብቃት ይሳተፍ ዘንድም የአገሪቱን ሁኔታ በቅርብ መከታተልና የተስተካከለ ግንዛቤ መያዝ፣ የአገራችንን ህዝቦች በአጠቃላይና በተለይም ደግሞ የወጣቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥያቄዎችን ለመፍታት በሚደረገው ጥረት የመፍትሄው አካል መሆን ይኖርበታል፡፡ በኢህአዴግ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄ አማካኝነት የአገራችንን ህዳሴ በላቀ ፍጥነትና ውጤታማነት ለማስቀጠል በሚደረገው ርብርብ የአገራችንን ወጣቶች ሚና አስመልክቶ በድርጅት አባላትና በራሳቸው በወጣቶች ዘንድ የጋራ መግባባት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ይህ ፅሁፍ የአሁኑ ወጣት ትውልድ ካለፈው ትውልድ የተረከበውን መልካም ስራ ጠብቆ ከማቆየት፣ ያለፈው ትውልድ ጀምሮ ያልጨረሳቸውን መልካም ነገሮች ከማጠናቀቅ ወይም በቀደመው ትውልድ የተፈፀሙ ስህተቶችን ከማረም እንዲሁም ለመጪው ትውልድ ትቶት ከሚያልፈው ታሪካዊ አሻራ አንፃር ምን ምን ታሪካዊ ሃላፊነቶች እንዳሉበት በሚያስገነዝብ አግባብ ተዘጋጅቷል። ለፅሁፉ መንደርደሪያነትም አገራችን ያለችበትን ወቅታዊ ሁኔታ፣ ያሏትን ተስፋዎችና ያሉባትን ስጋቶች በተለይም ከወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት አንፃር ለመዳሰስ ተሞክሯል።

አሁን ያሉ ችግሮችን በመቅረፍም ሆነ ወጣቶች ተልዕኳቸውን በሚወጡበት ሂደት ውስጥ የመሪነት ሚናውን በብቃት ለመወጣት ኢሕአዴግ ያለው ዝግጁነትና ቁርጠኝነትም ተመላክቷል። ፅሁፉ አባላት በየአደረጃጀታቸው ለሚያደርጉት ውይይት እንዲሁም ለወጣቶች መድረኮች ማስፈፀሚያ በሚሆን መልኩ ለውይይት መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

## 2. በህዳሴ ሃዲድ በመገስገስ ላይ የምትገኝ አገር

ቀደምት የስልጣኔ ታሪክ የነበራት አገራችን ኢትዮጵያ ስልጣኔዋን የሚያስቀጥልና የህዝቦቿን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍላጎቶች በሚያሟላ ስርዓት እጦት ምክንያት ለዘመናት የድህነትና የኋላቀርነት ተምሳሌት ሆና የምትታወቅበት ሁኔታ ተፈጥሮ ቆይቷል፡፡ ይህ የመላ የአገራችንን ህዝቦች አንገት አስደፍቶ የኖረ አገራዊ ሁኔታ መለወጥና አገሪቱ ወደ ህዳሴ ማምራት የጀመረችው የድህነትና ኋላ ቀርነት ጠበቃ የነበረው ፀረ ህዝብ ስርዓት የመጨረሻው ምሽግ የነበረው የደርግ መንግስት ከተገረሰሰ በኋላ ነው፡፡ የደርግ መንግስት ግብአተ መሬት የተረጋገጠው ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝቦች በኢህአዴግ መሪነት ባካሄዱት መራራ ትግል ነው፡፡

ከደርግ መንግስት መውደቅ በኋላ ባሉት ሃያ አምስት አመታት አገራችን ለዘመናት ተጭኗት ከኖረው ከባድ እንቅልፍ ነቅታለች፡፡ በተለይም ደግሞ በኢትዮጵያ ህዝቦች ይሁንታ የፖለቲካ ስልጣኑን የተረከበው ኢህአዴግ ካካሄደው የተሃድሶ እንቅስቃሴ በኋላ ባሉት አስራ አምስት አመታት ውስጥ በቀደምት ጊዜያት በመቶ አመቶች ያልታዩ አንፀባራቂ እድገቶች ተመዝግበዋል፡፡ አለም ረስቷት፣ እሷም አለምን ረስታ የኖረችው አገራችን በአለም መድረክ ስሟ በበጎ መጠራትና ፈጣን እድገት የታየባቸው ጥቂት አገሮች ተብለው ከሚደነቁት አንዷ መሆን ጀምራለች፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ የአገራችን ህዝቦች መሬታቸውንና ጉልበታቸውን በመጠቀም ከድህነት ለመላቀቅ ባደረጉት ትግልና ባስመዘገቡት የልማት ውጤት እንደሆነ ይታመናል፡፡

ይሁንናም ስር ሰዶ ከኖረ ድህነትና ኋላቀርነት በመነሳታችን ልንፈታቸው የሚገቡን ግን ገና ያልደረስንባቸውና ያልፈታናቸው ችግሮች፣ ከፉኛ በማሽቆልቆል ላይ ከነበረ አገራዊ ኢኮኖሚ በመነሳት በፍጥነት የሚገሰግስ እድገት ማስመዝገብ ከመጀመራችን ጋር በተያያዘ የሚነሱና ራሱ ፈጣኑ እድገታችን የሚመልሳቸው አዳዲስ ጥያቄዎችና ችግሮች እንዲሁም ከኢህአዴግና በሱ ከሚመራው መንግስት የአመራር ብቃትና ብልሽት የሚመነጩ ችግሮች ተደማምረው ከህዳሴው ሃዲድ እንዳያስወጡን በብስለትና በጥንቃቄ መንቀሳቀስ ይጠይቀናል፡፡ ከሃዲዱ ላለመውጣትና አጥብቀን ይዘን ግስጋሴውን ለማፋጠን መስራት የሚጠበቅብን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አሁንም አገራችን በህዳሴ ሃዲድ በመገስገስ ላይ እንደምትገኝ የጋራ መግባባት ልንይዝበት ግን ይገባል፡፡

በአገራችን የሚታየውን እድገት አሳንሶ ማየትም ሆነ ማጋነን ሁለቱም ወደ ትክክለኛ መፍትሄ አይወስዱንም፡፡ ህዝቡን ያስመረሩ በርካታ ችግሮች ስላሉብን ችግሮቹን ለመፍታት መነሻ ሆነው የሚያገለግሉንን አኩሪ እድገቶቻችን መደፈቅ አይኖርባቸውም፡፡ በሌላም በኩል ደግሞ በተገኘው እድገት በመኩራራት ከየአቅጣጫው የሚሰሙትን መፍትሄ የሚሹ ችግሮች ችላ ብሎ ማለፍ ቆይቶ የሚፈነዳ ቦንብ እንዲቀበር ከመተባበር የተለየ ጥፋት አይደለም፡፡ በመሆኑም አገራችን ጊዜ ሳይሰጣቸው መፈታት ያለባቸው በርካታ ችግሮችና ተግዳሮቶች የሚፈታተኑዋት ግን ደግሞ ወደ እድገት ማማ መውጣት የጀመረችና የሚያጋጥሙዋትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል መሰረት በመጣል ላይ የምትገኝ ታዳጊ አገር እንደሆነች ልንጠራጠር አይገባም፡፡ በዚህ የእድገት ጉዞም የአገራችን ወጣቶች የበኩላቸውን አኩሪ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ የአገራችን ህዳሴ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ከህዳሴው ሃዲድ እንዳትወጣ በሚደረገው ትግልም አይነተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ኢህአዴግ ይገነዘባል፡፡

## 3. ለወጣቱ ትውልድ ተስፋ የፈነጠቀ እድገት

የኢትዮጵያ ወጣቶች ያለፈ ታሪክ እንደሚያመለክተው ወላጆቻቸው እንዲያልፉ በተገደዱበት አስከፊ ህይወት ውስጥ የገፈቱ ቀማሽ ሆነው ኖረዋል፡፡ የነሱ የሆነውን ዛሬን እንዲጠሉ፣ ነገን ደግሞ የባሰ ጨለማ አድርገው እንዲመለከቱ በሚያደርገው ህይወት ውስጥ አልፈዋል፡፡ በታሪካቸው

ለመጀመሪያ ጊዜ በድህነትና ኋላቀርነት ከመማቀቅ፣ በስጋት ከመኖርና ለጦርነት ከመታጨት ነፃ የወጡት ከደርግ መንግስት መውደቅ ማግስት ነው፡፡ የደርግን መንግስት በመገርሰስ በአገሪቱ ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማት ለማስፈን በተካሄደው ህዝባዊ ትግል በተሳተፉ ወጣት ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው የህይወት መስዋዕትነት እነሱ ለሌላ ዳግም መስዋዕትነት የማይታጩበት አዲስ መድረክ ተከፍቷል፡፡

አዲሱ የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት መድረክ ለኢትዮጵያ ወጣቶች ታላቅ ተስፋ ፈንጥቋል፡፡ በሁሉም የአገራችን የከተማና የገጠር ቀበሌዎች የተስፋፉት ትምህርት ቤቶች ለወጣቶች ሰፊ የትምህርት ዕድል ፈጥረዋል፡፡ ቀድሞ እንደነበረው ለባለስልጣንና ለሃብታም ልጆች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የአገራችን ወጣቶች እኩል እድል የሰጠ አገራዊ የትምህርትና የስልጠና ፕሮግራም እውን ሆኗል፡፡ የሁሉም ብሄር ብሄረሰቦችን ወጣቶች ተቀብለው የሚያስተምሩና የሚያሰለጥኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሁሉም የአገራችን ክፍሎች ተስፋፍተዋል፡፡ በአመት ከአስር ሺህ የማይበልጡ ወጣቶች የስራ ዕድል የሚያገኙበት አገራዊ ሁኔታ ተለውጦ በየአመቱ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ወጣት ወደ ስራ የሚሰማራበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡

ኢህአዴግና በሱ የሚመራው መንግስት በቀየሱት ስትራቴጂ መሰረት በየደረጃው ወጣቱ በተለያየ ሙያ እንዲሰለጥንና በሰለጠነበት ሞያም የስራ ዕድል እንዲያገኝ፣ ራሱም ስራ ፈጣሪ እንዲሆን የተለያየ ድጋፍ ይደረግለታል፡፡ በዚህ አቅጣጫ ተጠቃሚዎች የሆኑ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች የተሻለ ኑሮ መኖርና ወደ ብልፅግና መሸጋገር ጀምረዋል፡፡ በየአመቱ በመንግስት የሚታቀዱና የሚተገበሩ ትላልቅ (ሜጋ) ፕሮጀክቶች፣ በየጊዜው እያደገ የሚገኝ የውጭ አገሮችና አገራዊ ባለሃብቶች ኢንቨስትመንቶች፣ ከወረዳ እስከ ክልል ድረስ የሚዘረጉና ከመንግስት አገልግሎት እየሰፋ መሄድ ጋር በየጊዜው የሚሰፉ የመንግስት መ/ቤቶች፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ፓኬጆች፣ ወዘተ... ሁሉ በየአመቱ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ወጣቶች የስራ ዕድል ይፈጥራሉ፡፡ በዚህ ላይ በወጣቱ የራስ ጥረት የሚከፈቱ የግል ስምሪቶች ሲታከሉበት በርግጥም ወጣቱን ተጠቃሚ ያደረገና በይበልጥም ተጠቃሚ ሆኖ እንደሚቀጥል ተስፋ የፈነጠቀ አገራዊ ሁኔታ ላይ እንደምንገኝ እንረዳለን፡፡

በሌላም በኩል ልማታዊ መንግስታችን የኢትዮጵያ ወጣቶች በአገሪቱ የዴሞክራሲያዊ ስርዓትና መልካም አስተዳደር ግንባታ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተደራጀና የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉና ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸውን እንዲያረጋግጡ፣ አገር ተረካቢነት ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ የማስቻል አላማ ያለው የልማትና እድገት ፓኬጅ አዘጋጅቶ በስራ ላይ አውሏል፡፡ የኢትዮጵያ ወጣቶች የልማትና እድገት ፓኬጅ የአገራችን ወጣቶች የሚያጋጥሟቸውን ሁለንተናዊ ችግሮች በጥልቀት በመገምገም በየመስኩ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል፡፡ ፓኬጁን በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ በተቻለባቸው ገጠሮችና ከተሞች የወጣቱን ተጠቃሚነት ያረጋገጡ አበረታች ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ ለፓኬጁ ተግባራዊነት መንግስት በጀትን ጨምሮ ሰፊ ድጋፎች ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ መንግስት ለወጣቱ የሚሰጠው ትኩረት የህዳሴ ጉዞውን የማስቀጠል ርብርቡ አካል እና ከአገራችን እድገት ጋር እየሰፋና እየጎለበተ የሚሄድ እንጂ በሆነ ጊዜ ተጀምሮ አንድ ወቅት ላይ የሚቆም አለመሆኑ በርግጥም አገራችን የምትገኝበት ሁኔታ ለወጣቱ ተስፋ የፈነጠቀ መሆኑን ያመለክታል፡፡

አገራችን አሁን የምትገኝበት መድረክ ወጣቱን ተጠቃሚ ያደረገ ብቻ ሳይሆን ነገንም ብሩህ አድርጎ እንዲመለከት የሚያስችል ነው፡፡ ወጣቱ ትውልድ ትናንት ከኖረበት ይልቅ ወደፊት የሚኖርበት እድሜ እንደሚበልጥ ይታወቃል፡፡ ወደፊት የሚኖርበት እድሜ ግን በቁጥሩ ብዛት ብቻ ሳይሆን ብዙ መስራት የሚችልበትና የሚጠበቅበት መሆን አለበት፡፡ የተማረውን ትምህርትና የሰለጠነበትን ሙያ በተግባር ላይ ማዋል የሚጀምርበትና ለውጥ የሚያመጣበት፣ እውቀቱንና ልምዱን የሚያዳብርበት፣ ቤተሰባዊና ማህበራዊ እንዲሁም አገራዊ ኃላፊነት የሚረከብበት፣ የእሱን ወጣትነት ተከትለው ለሚያድጉ ህፃናትና ለቀጣዩ ትውልድ መልካም ቅርስ የሚተውበት በመሆኑ መጪው ጊዜ ለወጣቱ ከፍተኛ ትርጉም አለው፡፡

ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ነገ የተሻለ እድል እንደሚኖር፣ ያንን እድል እውን ለማድረግ ደግሞ ወጣቱ የድርሻውን ማበርከት እንደሚገባው በእምነት ተቀብሎ ሲንቀሳቀስ ነው፡፡ ነገን አጨልሞ የሚመለከት ወጣት መዳረሻው ያማረ አይሆንም፡፡ዛሬ በአገራችን ያለው ሁኔታ ደግሞ ነገን አጨልመን እንድናይ ሳይሆን ተስፋ እንድንሰንቅ የሚያበረታታ ነው፡፡ ሁሉም ነገር ሁላችንም በምንመኘውና

በምናስበው አቅጣጫና ፍጥነት ላይሄድ ይችላል፡፡ ከዚህ በመነሳት ቶሎ ተስፋ መቁረጥ ተገቢ አይሆንም፡፡ ሁሌም የሚያጋጥሙትን ችግሮች ብቻ ሳይሆን እየተደረጉ ያሉትን ጥረቶችና የተገኙትን መልካም ውጤቶችንም ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ ነገን የተሻለ ለማድረግ በአንድ ልብ እስከተንቀሳቀስን ድረስ ያላንዳች ጥርጥር ማናቸውንም አይነት ችግሮች መፍታትና በርግጥም አገራችን ታላቅ ተስፋ የፈነጠቀባት እንደሆነች በግብር የምናረጋግጥበትን ሁኔታ እንፈጥራለን፡፡

## 4. ተስፋና ስጋት የሚታዩበት አገራዊ ወቅታዊ ሁኔታ

አገራችን ኢትዮጵያ በፈጣን እድገትና ህዳሴ ላይ የምትገኝ፣ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት ከፍተኛ ርብርብ የሚካሄድባት የመሆኗን እውነታ ማንም አሌ ሊለው የሚችል አይደለም፡፡ ይህ የፈጠረው የህዝቦች ተጠቃሚነት፣ በየመስኩ ያለው ውጤታማ ስራ በኢትዮጵያ ህዝቦች ዘንድ የፈነጠቀው ተስፋ ምስክር የማያስቆጥር በገሃድ የሚታይ ሃቅ ነው፡፡ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከትናንቷ ኢትዮጵያ ፍፁም የተለየች፣ ህዝቦቿ በኢትዮጵያዊነታቸው ኮርተው መኖር የጀመሩባት፣ በህዝቦቿ መካከል በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ አንድነት የተገነባባት፣ ሊኖሩባት የምታጓጓ የተከበረች አገር መሆን ጀምራለች፡፡

ይህ መልካም ገፅታዋ እንደተጠበቀ ሆኖ እሱን የሚፈታተን ሌላ ገፅታም የሚታይባት አገር እንደሆነች የሚደበቅ አይሆንም፡፡ ዛሬም በአገራችን ስር የሰደደ ድህነት አለ፡፡ ከ20 ሚሊዮን የማያንሱ ወገኖቻችን ከድህነት ወለል በታች በሆነ አስከፊ ህይወት ይማቅቃሉ፡፡ መሰረተ ልማት ያልደረሰባቸው፣ ከአገሪቱ እድገት እኩል ተጠቃሚ ያልሆኑ አካባቢዎችና የህብረተሰብ ክፍሎች ጥቂት አይደሉም፡፡ በዚህ ረገድ የከተማ ነዋሪዎች፣ አርብቶ አደሮች፣ ወጣቶችና ሴቶች ከአገሪቱ ልማትና እድገት የሚጠበቀውን ያህል ተጠቃሚ እንዳልሆኑ ኢህአዴግና የኢፌዴሪ መንግስት ያምናሉ፡፡ በከተሞች የሚታየው የኑሮ ውድነትና ስራ አጥነት እያደገ ከቀጠለው የህዝብ ብዛት ጋር ተደማምሮ በአገሪቱ ያለውን በገሃድ የሚታይ ሁሉን አቀፍ እድገት የሚያደበዝዝና እንደሌለ የሚያስቆጥር የብዙ ዜጎችን ህይወት ስጋት ላይ የሚጥል ችግር ሆኗል፡፡

ትምህርት ቤቶች በመስፋፋታቸው በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወጣቶችን ማስተማር የተቻለ ቢሆንም ከትምህርት ቤት ለሚመረቁት በሙሉ የስራ እድል ባለመፈጠሩ ምክንያት የሚታየውን የወጣቶች ስራ አጥነት ችግር መፍታት የሚቻለው ኢኮኖሚውን በማሳደግ፣ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለመሸጋገር የተቀየሰውን ስትራተጅ በፍጥነት ተግባራዊ በማድረግና ኢንዱስትሪን በማስፋፋት ነው፡፡ ገጠሩ እያስመረረው ሳይሆን የኑሮ ደረጃውን ለማሳደግ ወደ ከተሞች ለሚጎርፈው ወጣት በርግጥም የተሻለ ኑሮ የሚኖርበትን ሁኔታ መፍጠር የሚቻለው ይህንን መሸከም የሚችል ኢኮኖሚ በመገንባት ብቻ ይሆናል፡፡

በአገራችን የስጋት ምንጭ የሆነው ግን ከኢኮኖሚ እድገቱ የሚመነጨው ችግር ብቻ አይደለም፡፡ ከገዥው ፓርቲና ከመንግስታችን የአመራር ድክመት የሚመነጩ ሰፊ ችግሮች አሉ፡፡ በጥቅሉ የመልካም አስተዳደር ችግር እየተባሉ በተከታታይ የሚነሱ ነገር ግን በመሰረታዊነት ገና ስላልተፈቱ ቀጣይ የቤት ስራ ሆነው የሚገኙና ፈጣን ርምጃ የሚሹ በርካታ ችግሮች እንዳሉ አከራካሪ አይሆንም፡፡ በአሁኑ ጊዜ የመንግስት መዋቅሩ ለህዝብ መስጠት የሚገባውን አገልግሎት በብቃት እየሰጠ አይገኝም፡፡ መንግስት ህዝቡ የሚያነሳቸውን ቅሬታዎች በቅጡ አያዳምጥም፣ ለማዳመጥ ሞከርኩ በሚልበትም ተገቢና ፈጣን መልስ አይሰጥም፡፡ በየደረጃው ህዝብን በቅንነት የሚያገለግል፣ ህዝብን ሳያጉላላ ውሳኔ የሚሰጥ አካል ጠፍቷል የሚባልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡ በዚህ ላይ አድሎና ሙስናው በህግ የተፈቀደ ያህል በግላጭ የሚፈፀም ሆኗል፡፡ እነዚህ በድምሩ ህዝቡ በመንግስት ላይ አመኔታው እንዲቀንስና እነዚህ መፍትሄ ያላገኙና እየተባባሱ የመሄድ አዝማሚያ የሚታይባቸው የመልካም አስተዳደር ችግሮች ምን ያስከትሉ ይሆን የሚል ስጋት እንዲያሳድር አድርጎታል፡፡

ወጣቶች ከፈነጠቀው ተስፋ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደረጋቸው፣ “እገሌ አለልኝ” ማለት የማይችሉ፣ በእገሌ አማካይነት መንገዱ የማይመቻችላቸው ወጣቶች የስራ እድል ማግኘት የማይችሉበት፣ በሆነ አጋጣሚ ተወዳድረው ስራውም ቢገኝ ምደባው በአድሎ የሚሰጥበት፣ በራስ ጥረት ኑሮን ለመለወጥ ሲሞክሩም ቁጥር ስፍር የሌላቸውን መሰናክሎች ማለፍ የሚቸገሩበት፣ ወዘተ... ሁኔታ እንዲገነግን ያደረገው የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር የበላይነት በመያዙ ነው፡፡

በርግጥም እጅግ የሚያስጎመኙ እድገትና ተስፋ የሚታይባት አገራችን የኪራይ ሰብሳቢነት አደጋ ተጋርጦባታል፡፡ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ ሊጠናከርና የተጀመረው ህዳሴ ሊቀጥል የሚችለው ኪራይ ሰብሳቢነትን በተሟላ መንገድ ማስወገድ፣ ቢያንስ የህዳሴው ጉዞ እንቅፋት የማይሆንበት ሁኔታ በመፍጠር ብቻ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ገዥው ፓርቲና መንግስት እንዲሁም በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ ግንባታ ተጠቃሚ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ በተለይም ደግሞ አገር ተረካቢ የሆነው ወጣት በተደራጀና በጠራ የትግል አግባብ ኪራይ ሰብሳቢነትን ሊታገሉት ይገባል፡፡ በአገራችን የሚታየው እድገትና ብሩህ ተስፋ ይበልጥ እንዲጎለብት፤ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ከልማቱ ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ አስተማማኝ አገራዊ ሁኔታ ይፈጠር ዘንድ በኪራይ ሰብሳቢነት ላይ የሚካሄደው ትግል ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

ኢህአዴግ ዴሞክራሲ ሲል ዜጎች ሃሳባቸውን በነፃ እንዲገልፁ፣ ሃሳባቸውን ለመግለፅ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ የመሰለፍ ነፃነት እንዲኖራቸው፤ ገዥውን ፓርቲም ሆነ መንግስትን መተቸትና መቃወም እንዲደፍሩና ይህንን በማድረጋቸው ምክንያት አንዳችም ጥቃት እንዳይደርስባቸው የህግ ጥበቃ የሚያገኙበት ሁኔታ መረጋገጥ አለበት ማለቱ ነው፡፡ ስለሆነም በአገራችን የተለያዩ ክፍሎች የተካሄደውን የተቃውሞ ሰልፍ ኢህአዴግና መንግስት ከሁሉ አስቀድሞ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ሲያካሂዱት የነበረው ትግል ፍሬ ማፍራቱን ያመላከተ፣ ዴሞክራሲያችን እያደገ መሄዱን ያበሰረ እንቅስቃሴ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ መንግስት ሊከበር እንጂ ሊፈራ እንደማይገባው የተገነዘበ፣ በኢህአዴግም ሆነ በመንግስቱ ላይ ያሳደረውን ቅሬታ በተሰማው መጠን የሚገልፅ ትውልድ ተፈጥሮ ማየቱ ለኢህአዴግ የትግሉ ውጤት በመሆኑ ይኮራል፡፡

ይሁን እንጂ ወጣቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች በትክክል መልስ እንዲያገኙ የመጀመሪያው ተፈላጊ ጉዳይ ጥያቄዎቹ ሳይደበላለቁ ጥርት ብለው እንዲቀርቡ ማድረግ ይሆናል፡፡ በሁለቱ ክልሎች በተካሄዱት ሰልፎች የቀረቡት ጥያቄዎችና የተስተጋቡት መፈክሮች የህዝቡና የወጣቱ የሆኑ፣ ምላሽ ሊሰጣቸው የሚገቡና የሚችሉት በጭራሽ እሱን ከማይመለከቱና መንግስት ሊታገላቸው እንጂ መልስ ሊሰጣቸው ከማይገቡ ጥያቄዎች

ጋር የተደበላለቁ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ በየደረጃው የሚታየው የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲወገድ፤ በብልሹ አሰራርና ሙስና ላይ አስቸኳይ ርምጃ እንዲወሰድና አጥፊዎች በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ፤ ያላግባብ የከበሩ ዜጎች የሃብት ምንጫቸው እየተጣራ በህግ እንዲጠየቁ፤ የወጣቱ የስራ አጥነት ችግር እንዲቃለል፣ በማንነትና በወሰን ዙሪያ የሚነሱ ጥያቄዎች በህገ መንግስቱ መሰረት እንዲፈቱ፤ የንፁህ መጠጥ ውሃ፣ የመብራት፣ የስልክ፣ የመንገድ፤ የመሳሰሉ የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲሻሻሉና እንዲሟሉ የሚሉትና ከዚህ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ተገቢ ናቸው፡፡

መንግስትም ህዝቡን ባሳተፈ አኳኋን ፈጣንና የማያዳግም ምላሽ መስጠት፣ በተሟላ መንገድ መመለስ ያልተቻለውን ደግሞ ምክንያቱን ለህዝብ እያስታወቀ ለማሟላት ህዝቡን ባሳተፈ አኳኋን ጥረቱን መቀጠል ይኖርበታል፡፡ በሌላ በኩል ግን በመከባበርና በእኩልነት መርህ ላይ በተመሰረተ አንድነት አዲሲቷን ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ የገነቡትን የአገራችንን ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የሚከፋፍሉና ጥላቻን የሚቀሰቅሱ፤ የዜጎችን ህገ መንግስታዊ መብት የሚፃረሩ፤ በህገ መንግስት የተደነገጉና የመላ የኢትዮጵያ ህዝቦች የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች መሆናቸውን የሚያረጋግጡበት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያወጣቸውን ህጎች የሚጥሱ በርካታ መፈክሮች ተስተጋብተዋል፡፡ ይህ ሊታረምና መቸም ቢሆን ሊደገም የማይገባው ስህተት ነው፡፡

ኢህአዴግና መንግስት የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደታችን መልካም ልምዶቻችንን እያቀብንና እያጎለበትን፣ የሚታዩ ስህተቶችን ደግሞ በወቅቱ እያረምንና የማይደገሙበትን ሁኔታ እየፈጠርን መሄድን የግድ የሚል እንደሆነ ስለሚያምኑ በሰልፎቹ የተስተጋቡትን የህዝብ ያልሆኑና ህዝቡን የማይጠቅሙ መፈክሮች በጭራሽ መነሳት አልነበረባቸውም አይሉም፡፡ ወጣቱን በማስተማር ስህተቱን እንዲታረም ማድረግ እንጂ ለምን ተናገራችሁ በሚል አንዳችም አይነት እርምጃ አይወስዱም፡፡ የተሳሳቱ ጥያቄዎችንም በማስተጋባት በሰላማዊ መንገድ ተጀምረው በሰላማዊ መንገድ በተጠናቀቁ ሰልፎች በተሳተፉ ወጣቶች ላይ መንግስት ህዝብን የሚከፋፍልና ጥላቻን የሚፈጥር መፈክር አሰምታችኋል፤ የአገሪቱን ህጋዊ ባንዲራ በማውረድ በሌላ ተክታችኋል፤ የባለስልጣናትን ስም እያነሳችሁ ተሳድባችኋል፣ ፎቶ

አቃጥላችኋል፤ ወዘተ… በሚል አንዳችም ርምጃ እንዳልወሰደ ከማንም በላይ በሰልፉ የተሳተፉና ቁጣችንን ይገልፅልናል ባሉት አግባብ መፈክር ሲያሰሙ የዋሉ ወጣቶች ይመሰክራሉ፡፡

ነገር ግን የሰሞኑ ሰልፎች ወጣቱትክክለኛ የሆኑትንም ሆነ የተሳሳቱትን ጥያቄዎች በሰላማዊ መንገድ ብቻ የገለፀባቸው አልነበሩም፡፡ ቁጣቸው በማን ላይ እንደሆነ አይደለም ለተመልካች ለራሳቸው ለፈፃሚዎቹም ግልፅ ባልሆነ አኳኋን ለብዙ ወጣቶች የስራ እድል የፈጠሩና ለህዝቡ አልግሎት በሚሰጡ የመንግስት፣ የህዝብና የግለሰቦች ሃብት የሆኑ የልማት ተቋማት ላይ ከፍተኛ ውድመት አድርሰዋል፡፡ የስራ አጥነት ችግር ይፈታ እያሉ ለወንድም እህቶቻቸው የስራ እድል የፈጠሩ ተቋማትን በማፈራረስ ከነበራቸው ስራ ተፈናቅለው ለስራ አጥነት የሚዳርጉ፤ የመሰረተ ልማት አልተሟላልንም እያሉ የተገነቡ መሰረተ ልማቶችን የሚያወድሙ፤ የኑሮ ውድነት ይቃለል የሚል መፈክር እያሰሙ ዜጎች የእለት ስራቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዳያከናውኑ፣ የሸቀጦች ዝውውር እንዳይኖር መንገድ በመዝጋት፣ የንግድ ቤቶች እንዳይከፈቱ በማወክ ተግባር ላይ የሚሰማሩ ወጣቶች በምንም መመዘኛ ህዝቡ ተጠቃሚ የሚሆንበት ለውጥ እንዲመጣ የተሰለፉ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡

በርግጥ ኢህአዴግና መንግስት በሰልፎቹ የተሳተፉ ወጣቶች በሙሉ በእንደዚህ አይነት አፍራሽ ድርጊት ተሰማርተዋል የሚል እምነት የላቸውም፡፡ ጥፋቱን የሚፈፅሙትና በሰልፉ ቦንብ፣ ሽጉጥና ጠመንዣ ታጥቀው በመግባት የፀጥታ ሃይሎች ህግ ለማስከበር ያደረጉትን ጥረት ወደ ግጭት የቀየሩት ጥቂት የተለየ አላማ ካላቸው ሃይሎች ጋር የተሳሰሩና የተወናበዱ ወጣቶች እንደሆኑ ይገነዘባሉ፡፡ በዚህ ሂደት የገበያ ግርግር እንዲሉ በሁከቱ የሚሳተፉ የነበሩትን ያህል ጥያቄያችንና ተቃውሟችንን በሰላማዊ መንገድ ነው ማሰማት ያለብን ብለው የተከራከሩና በቻሉት አቅምም ጥፋቶች እንዳይፈፀሙ ሲከላከሉ የነበሩ በርካታ ወጣቶች እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም መንግስት ችግሩን ለመፍታት የሚወስደው ማናቸውም ርምጃ ይህንን ግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል፡፡ ያስመረሩት ችግሮች እንዲፈቱለት ለመጠየቅና እስካሁን ስላልተፈቱለትም በመንግስት ላይ ያሳደረውን ቅሬታ ለመግለፅ አደባባይ የወጣውንና ይህንን አጋጣሚ አገሪቱን ለማፈራረስ ወደ ታቀደ የቀለም

አብዮት ለመለወጥ የተንቀሳቀሰውን አፍራሽ ሃይል ኢ.ህአዴግና መንግስታችን አደበላልቀው አይመለከቱም፡፡

በአመቱ ውስጥ የታየው ይህ አገራዊ ሁኔታ ለኢ.ህአዴግና ለመንግስት እንዲሁም ለኢ.ትዮጵያ ወጣቶችና ለመላው የአገራችን ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ትልቅ ትምህርት የሰጠ ነበር፡፡ የተቃውሞ ሰልፉና ግርግሩ በዋነኛነት በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ይታይ እንጂ ሌሎች ክልሎች ከችግሩ ነፃ ናቸው የሚባል አይደለም፡፡ የችግሩ ዋነኛ መንስኤ ነው ያልነው ህዝቡ በመንግስት ላይ ቅሬታ እንዲያሳድር ያደረገው የመልካም አስተዳደር፣ የድህነት፣ የስራ አጥነት፣ የማንነት፣ የወሰን፣ የመሰረተ ልማትና የተለያዩ አገልግሎቶች አለመሟላት፣ ወዘተ … ችግሮች መጠናቸው ሊለያይ ካልሆነ በቀር በሁሉም ክልሎች እንዳሉ፣ ከዚህም የተነሳ ህዝቡ ተቃውሞውን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እንደሚገልፅ ይታወቃል፡፡ አንድ አቀጣጣይ ነዳጅ በተፈጠረበት ቅፅበት ደግሞ ይቀጣጠላል፡፡ በመሆኑም በመላው አገራችን መሰረታዊውን ችግር ለመፍታት በፍጥነትና ውጤታማ በሆነ አግባብ መረባረብ የሚጠይቀን መድረክ ላይ እንደምንገኝ በኢ.ህአዴግ ደረጃ የጋራ መግባባት ተፈጥሮበታል፡፡

ለምዕራባውያን ፍላጎት የማያድሩ ናቸው የሚሏቸውንና በተጠናከሩ መጠንም አይታዘዙንም ብለው የሚፈርጇቸውን መንግስታት ከውስጥ የሚኖርን ቅሬታ በማራገብና ከውስጥም ከውጭ የሚኖርን ተቃዋሚ ሃይል ገደብ በሌለው ድጋፍ በማደራጀት በተለያየ ቀለም የተሰየሙ አመፆችን በማነሳሳት ጠንካራውን መንግስት በመጣል አሻንጉሊታቸው በሆነ ደካማ መንግስት የመተካት ልምድ ያላቸው የቀለም አብዮተኞች በኢ.ህአዴግ የሚመራውን መንግስት በተለያየ ጊዜ ሞክረውት አልሆነላቸውም፡፡ ዘንድሮ ግን ከመቸውም ጊዜ የተሻለ አጋጣሚ ተገኝቷል በሚል ባለ በሌለ አቅማቸው ሲረባረቡ ቆይተዋል፡፡ ለዚህም የኤርትራ መንግስትን፣ የተፈጥሮ ሃብታችንን ለመጠቀም የምናደርገው ርብርብ ስጋት የፈጠረባቸውን አገሮች፣ በውጭ የሚኖሩ ፅንፈኛ ኢ.ትዮጵያውያንና ትውልደ ኢ.ትዮጵያውያንን፣ በአገር ውስጥ ህጋዊ እውቅና ያላቸውና ህጋዊውንና ህገ ወጡን መንገድ እያደባለቁ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በአጠቃላይ በኢ.ህአዴግ የሚመራውን መንግስት በመጣል ኢ.ትዮጵያን የማፈራረስ አላማቸውን ለማሳካት መሳሪያ

ይሆነናል የሚሉትን ሃይል ሁሉ አረባርበዋል፡፡ በተለያዩ የአገሪቱ ድምበሮች በድብቅ የገንዘብ ክምር እያስገቡ ለአመፁ ማካሄጃ በየቦታው ዘርተዋል፡፡ ብዙም ባይሳካላቸውም አመፁን በነጭ ቀለም ለመሰየምም ሞክረዋል። የታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ አራተኛ አመት መታሰቢያን እንደመነሻ በመውሰድ ነጭ ቲሸርት አዘጋጅተው ለመበተን፣ ቲሸርቱ ያልደረሰውም የየራሱን ነጭ ልብስ ለብሶ አደባባይ እንዲወጣ በማህበራዊ ሚዲያዎች አውጀው ነበር፡፡

ስለሆነም ባንድ በኩል የችግሩ ዋነኛ ምንጭ የሆነውን ውስጣዊ ድክመታችንን ይዋል ይደር ሳንል መፍታት፣ በዚህ ረገድ መላው ህብረተሰብና ወጣቱ የመፍትሄው አካላት በመሆን የሚጠበቅባቸውን ሚና መጫወት የሚችሉበትን ሁኔታ ማረጋገጥ ይገባል፡፡ መንግስትም የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚያረጋግጡ መድረኮችን መክፈት፣ በህዝቡና በመንግስት መካከል ከመቸውም ጊዜ በላይ መቀራረብና ጠንካራ ትስስር መፍጠር፣ ይህንንም የሚያሳልጡ አስፈላጊ የሆኑ የፖሊሲ፣ የአደረጃጀትና አሰራር ለውጦችን ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አገሪቱን ለማተራመስ የሚደረግን ማናቸውንም አፍራሽ ድርጊት የመመከትና በመላ አገሪቱ ህግና ስርዓትን የማስከበር፣ የህግ የበላይነትንና ሰላምን የማስጠበቅ ሃላፊነቱን በብቃት መወጣት ይኖርበታል፡፡

## 5. ችግሮችን በመፍታት የአገራችንን ህዳሴ የሚያስቀጥል አቅም አለን

ከፍ ብሎ በቀረቡት ክፍሎች እንደተመለከትነው አገራችን ብዙ ተስፋ የሚሰጡ ለውጦች የሚታዩባት የመሆኗን ያህል መፍትሄ ያላገኙ በርካታ ችግሮችም አሉባት፡፡ በቅርቡ በኦሮሚያና በአማራ ክልል የታዩት ሁከቶችም በመሰረቱ ሳይፈቱ የቆዩት ችግሮቻችን መገለጫ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ የተጀመረው እድገትና ተስፋ ሰጭ ጉዞ ሳይሰናከል ቀጥሎ ያልተፈቱት ችግሮች የሚፈቱበት ሁኔታ እንዲኖር እና የአገሪቱ ሰላም እንዳይናጋ በሚፈልጉት የህብረተሰብ ክፍሎችና በኢትዮጵያ ወዳጆች ዘንድ ስጋት ፈጥሯል፡፡ በርግጥ ችግሩ ይፈታ ይሆን ወይ የሚል ጥርጣሬም ማሳደር ጀምሯል፡፡ አፍራሽ ሃይሎች ዋነኛ መሳሪያቸው ባደረጉት ማህበራዊ ሚዲያ በየደቂቃው የሚሰራጨው የፈጠራ ወሬና አሸባሪ መልእክትም

ቀላል በማይባል ደረጃ ህዝቡን እያደናገረ ይገኛል፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ከኢ.ህአዴግና ከመንግስት በኩል ህዝቡ እንዳይደናገርና ትክክለኛውን ሁኔታ እንዲረዳ ለማድረግ የሚሰራው ስራ ደካማ መሆኑ ችግሩ መፍትሄ ሊያገኝ ስለመቻሉ ያሳደረውን ጥርጣሬ የሚያባብስ ሆኖ ይገኛል፡፡

ኢ.ህአዴግና መንግስት የህዝቡን ስጋት ይረዳሉ፣ ስጋቱን የሚያቃልል ተጨባጭ ስራ መስራት እንደሚያስፈልግም ያምናሉ፡፡ ይህንን እውን ሊያደርግ የሚችል እንቅስቃሴም ጀምረዋል፡፡ ኢ.ህአዴግ በ40 አመት የትግል ጉዞው ውስጥ በርካታ ችግሮች ተፈታትነውት ሁሉንም ትክክለኛ የችግሮች አፈታት ስልት በመጠቀም ብዙም ጉዳት ሳያደርሱ መፍታት እንደቻለ የድርጅቱ ታሪክ ያስረዳል፡፡ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የኢ.ህአዴግ መስራች የሆኑት ህወሓትና የያኔው ኢ.ህዴን ያሁኑ ብአዴን በየድርጅታቸው ከመለስተኛ እስከ የድርጅቱን ህልውና የሚፈታተኑ ፈተናዎች አጋጥመዋቸው ሰፋፊ የእርማትና የተሃድሶ ንቅናቄዎችን በማካሄድ ስር ነቀል መፍትሄ መስጠትና ለድል መብቃት ችለዋል፡፡ ደርግ ከወደቀም በኋላ በኢ.ህአዴግ ደረጃ ያጋጠመውን የጥገኛ ዝቅጠት ችግር ድርጅታዊ ተሃድሶ በማካሄድ በመፍታት ባለፉት አስራ አምስት አመታት ለተጎናፀፍናቸው አበይት ድሎች በቅተናል፡፡ ይህ ድርጅታዊ ባህሉና የዳበረ ልምዱ ከፅኑ ህዝባዊ ወገንተኛነቱ ጋር ተዳምሮ ዛሬም ሆነ ወደፊት የሚያጋጥሙትን ማናቸውንም ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ትልቅ አቅም የገነባ ድርጅት እንደሆነ ያስረዳናል፡፡

ኢ.ህአዴግ የሚያጋጥሙትን ፈተናዎች በብቃት ለማለፍ የሚጠቀምበት የመጀመሪያውና ዋነኛው ስልት የችግሮቹን ምንነት፣ የችግሮቹን ስፋትና ያስከተሉትን ጉዳት፣ የችግሮቹን መንስኤዎች፣ ችግሮቹ እንዲቀጥሉ ከተፈቀደላቸው በድርጅት፣ በህዝብና በአገር ላይ ሊፈጥሩት የሚችሉት ሳንካ፤ ወዘተ… አስመልክቶ በዝርዝር ግምገማ ማካሄድ ነው፡፡ በግምገማው ላይ በመመስረትም ችግሮቹ የሚፈቱበትን አቅጣጫ፣ ማን ምን ሃላፊነት እንደሚጠበቅበት፣ እያንዳንዱ ተግባር የሚከናወንበት የጊዜ ሰሌዳ እንዲሁም ችግሮቹን ለመፍታት በሚደረገው እንቅስቃሴ ሂደት ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ እንቅፋቶችና እንዴት መሻገር እንደሚገባ ዝርዝር ያለ መርሃ ግብር ያስቀምጣል፡፡ በግምገማውና ችግሩን ለመፍታት

የተቀየሰውን መርሃ ግብር ስራ ላይ በማዋሉ ሂደትም ከላይ እስከ ታች የጋራ መግባባት በመፍጠር አንድ ላይ ተሳስሮና ተዋህዶ ይተማል፡፡

ኢህአዴግ ዛሬ በአገራችን የተከሰተውንም ችግር በተመሳሳይ መንገድ ለመፍታት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ባለፈው አመት በተካሄዱት የአባል ድርጅቶቹና የግንባሩ ጉባኤዎች ላይ የነበረውን ግምገማና የተደረሰበትን ስምምነት መሰረት በማድረግ አንዳንድ የመፍትሄ ርምጃዎችን እየወሰደ ከቆየ በኋላ በቅርቡ በኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚና በምክር ቤት ደረጃ ያለፉትን አስራ አምስት አመታት ጉዞውን በጥልቀት በመገምገም ችግሮቹን በብቃት ለመፍታት ተነስቷል፡፡ በዚህ የአመራሩ ግምገማ መሰረት ባለፉት አመታት በአግባቡ ያልተፈቱና እየተከማመሩ የመጡ ችግሮች በአሁኑ ወቅት አገራችን በጀመረችው የህዳሴ ጉዞ በፍጥነት እንዳትገሰግስ እንቅፋት እየሆኑ መጥተዋል፡፡ ጊዜ የለንም በሚል ቅኝት ተረባርበን መፍታት ካልቻልን እየዳበረ የመጣው የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት ግስጋሴ ሊገታ የሚችልበት እድል ዝግ እንዳልሆነ ታምኖበታል፡፡

በዚህ ረገድ የችግሮቹ ሁሉ መንስኤ የገዥው ፓርቲ አመራር ድክመት ሲሆን ዋነኛ መገለጫውም የመንግስት ስልጣንን የህዝብን ጥቅም ለማስከበር የሚያገለግል መሳሪያ ከማድረግ ይልቅ የግል ጥቅም ማግኛና ሃብት ማበልፀግያ አድርጎ መጠቀም እንደሆነ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ይህንን ችግር በማያዳግም አኳኋን ለማስወገድም በድርጅቱ ውስጥ እንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄ እንዲካሄድ ተወስኗል፡፡ እንደገና በጥልቀት የመታደሱ ንቅናቄ በታለመለት አግባብ ይከናወን ዘንድም አመራሩ ከወዲሁ በታላቅ የሃላፊነት መንፈስና ቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ጀምሯል፡፡

የመባባስ አዝማሚያ እንደሚታይባቸው የሚታመኑት የአገራችን ችግሮች የተወሳሰቡና ከባድ ቢሆኑም ከአመራሩ አቅም በላይ እንዳልሆኑ ኢህአዴግ የፀና እምነት አለው፡፡ ኢህአዴግ ይህንን በድፍረት የሚናገረው በታሪኩ ተመሳሳይ ከባድ ችግሮች አጋጥመውት የፈታበት ልምድ ስላለውና በቁርጠኝነት ስለተነሳ ብቻ አይደለም፡፡ በቀደምት የእርምትና የተሃድሶ ንቅናቄዎቹ ያልነበሩ አዳዲስ አቅሞችንም ይዞ ስለሚሰማራም ነው፡፡ ኢትዮጵያን ወደ ህዳሴ ማስገባት ባስቻሉት ያለፉት አስራ አምስት አመታት እንቅስቃሴዎቹ በተግባር የተፈተነና ትክክለኛነቱ ባመጣቸው ውጤቶች

የተመሰከረለት መስመር ባለቤት ሆኗል፡፡ በዚህ መስመር እየተመራ ባካሄደው የተሳካ ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴም ከፍተኛ የህዝብ አመኔታና ድጋፍ አፍርቷል፡፡ ስለሆነም በአስራ አምስቱ አመት የለውጥ እንቅስቃሴ ተጠቃሚ የሆኑት ማህበራዊ መሰረቶቹ ያገኙት ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲቀጥልና በአንዳች አይነት ስህተት እንዳይደናቀፍ ከጎኑ ይሰለፋሉ፡፡ ህዝቡ በመንግስት ላይ ቅሬታ ቢኖረውም ሰላም እንዲደፈርስ፣ የተጀመረው ልማት እንዲሰናከል በጭራሽ አይፈልግም፡፡

በሌላም በኩል አገሪቱን ለማፍረስ የሚደረግን ማናቸውንም አይነት የአፍራሽ ሃይሎች ሙከራ መከላከልና መመከት የሚችል ከኢኮኖሚያዊ እድገታችን ጋር አብሮ ያደገ የፀጥታ አስከባሪ ሃይል አቅም ተፈጥሯል፡፡ እነዚህ በድምሩ በወቅቱ የአገራችን ሁኔታ ላይ የሚታዩት ችግሮች ተጨማሪ ጉዳት ሳያስከትሉ እንደሚፈቱ እንድንተማመን ያደርጉናል፡፡ በመሆኑም የህዝቡ ትክክለኛ ጥያቄዎች እንዲመለሱ፣ የተጣመመ የገዥው ፓርቲና የመንግስት አሰራሮችና አመራሮች እንዲቃኑ ይደረጋል፡፡ ሊያከራዩት የሚችሉትን ማናቸውንም በአቋራጭ መክበሪያ ነገርን በሙሉ በማከራየት ያላግባብ በከበሩና ልማታዊውን ጉዟችንን በሚያደናቅፉ ኪራይ ሰብሳቢዎች ላይ ምህረት የለሽ ትግል ይካሄዳል፡፡ በውጤቱም ለልማታዊ እንጂ ለኪራይ ሰብሳቢነት የማትመች ኢትዮጵያን እንገነባለን፡፡

## 7. ከአገራችን ወጣቶች ምን ይጠበቃል

ከአለማችን ቁንጮ ከበርቴዎች አንዱ የሆነው ዋረን ቡፌት እንደገለፀው "አንድ ሰው ዛፍ ጥላ ስር አረፍ የሚለው ዛፉን ሌላ ሰው ቀደም ብሎ ስለተከለው ነው፡፡ ማንኛውም አገር የሚገነባውም በትውልዶች ቅብብሎሽ ነው፡፡ አዲሱ ትውልድ የሚጠበቅበትን አገራዊ ተልእኮ ለመፈፀም መነሻውና መሰረቱ ከሱ በፊት የነበረው ትውልድ ትቶለት የሚያልፈው ግንባታ ይሆናል፡፡ ከዋረን ቡፌት አባባል መረዳት እንደሚቻለው አንድ መንገደኛ ከፀሐይ ቃጠሎና ከድካሙ አረፍ የሚልበት የዛፍ ጥላ ሊያገኝ የሚችለው ከዛፉ እድሜ በፊት በአካባቢው ሲኖሩ የነበሩ ሰዎች የዛፉን ችግኝ በመትከላቸውና ገና ማቆጥቆጥ ሲጀምርም ሆነ ካደገ በኋላ ቆርጠው

ስላላጠፉት ነው፡፡ ዛፉን ከተከሉት ሰዎች ውስጥ እድሜያቸው ፈቅዶላቸው አድጎ ለማየትም ሆነ በዛፉ ጥላ ስር አረፍ ብለው ድካማቸውን የተወጡ ላይኖሩ ወይም ቢኖሩም ጥቂቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነሱ ከዛፉ ቀጥተኛ ጥቅም ባይቋደሱም ግን ለመጭው ትውልድ ማረፊያ ጥላ ተክለው አልፈዋል፡፡የአገር ግንባታምእንደዚሁ ነው፡፡

አዲሱ ትውልድ ከአገር ግንባታ አኳያ ሶስት ሃላፊነቶች አሉበት፡፡ የመጀመሪያው ያለፈው ትውልድ ሰርቶት ያለፈውንና የተረከበውን መልካም ስራ ጠብቆ የማቆየት፣ የተደረሰበት እድገት ወደኋላ እንዳይመለስ፣ የትላልቅ ወንድሞቹና እህቶቹ ድካምና መስዋእትነት መና ሆኖ እንዳይቀር በታላቅ የሃላፊነት መንፈስ መንቀሳቀስ ነው፡፡ ያለፈውን ትውልድ አኩሪ ታሪክ ጥላሸት ለመቀባትና የተገነባን አገር ለማፍረስ የሚደረግን ማናቸውንም ጥቃት በመመከት የተረከበውን አደራ በብቃት የመወጣት ሃላፊት ይኖርበታል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ያለፈው ትውልድ ጀምሮ ያልጨረሳቸውን መልካም ነገሮች የማጠናቀቅ፣ የፈፀማቸውን ስህተቶች ደግሞ የማስተካከል የቤት ስራ ነው፡፡ ባለፈው ትውልድ ድክመትና ስህተት አዲሱ ትውልድ ተጠያቂ ባይሆንም እኔን አይመለከተኝም በሚል ጎደሎዎቹን ከመሙላትና የተጣመመውን ከማቃናት ወደ ኋላ በጭራሽ ማለት አይችልም፣ አይገባውምም፡፡ ጎደሎዎቹና ጠማማዎቹ የሚያስከትሉት ችግር ሰለባ የሚሆነው ያለፈው ትውልድ ሳይሆን አገር ተረክቦ የሚገኘው አዲሱ ትውልድ ነውና ሸሽቶ የማያመልጠው ሃላፊነቱ ይሆናል፡፡ ሶስተኛው ሃላፊነት እሱን ለሚተካው ቀጣዩ ትውልድ ትቶት የሚያልፈውን ታሪካዊ አሻራ በጥንቃቄና በብቃት ማከናወን ነው፡፡ ካለፈው ትውልድ የተረከበውን መልካም ስራ በመጠበቅ፣ የተጓደሉትን ደግሞ በማሟላትና የተሳሳቱትን በማረም በኩል ያከናወናቸው ተግባራት በራሳቸው ለቀጣዩ ትውልድ ጠንካራ መሰረት ሆነው ያገለግሉታል፡፡ ይህ ብቻ ግን በቂ አይደለም፤ ለአዳዲስ ሁኔታዎችና መድረኩ ለሚጠይቃቸው ጉዳዮች ብቁና ትክክለኛ መልስ በመስጠት የአገር ግንባታውን ወደ ከፍታ ማሸጋገር ይጠበቅበታል፡፡ ቀጣዩ ትውልድ እሱ በተጓዘባቸው አስቸጋሪ መንገዶች እንዳይጓዝ፣ እሱን የፈተኑት ችግሮች በተተኪውም ላይ እንዳይደርሱ፣ እሱ ታላቅ ወንድሞቹና እህቶቹ ያጓደሉትንና የተሳሳቱን የማስተካከል ሃላፊነት እንደተረከበው ሁሉ ለታናሽ ወንድሞቹና እህቶቹ የቤት ስራ ትቶ እንዳያልፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ስራዎችን በንቃት ማከናወን ይኖርበታል፡፡

አዲሱ ትውልድ ወይም ወጣት የምንለው ከታላቆቹ የተረከበውን አደራ በብቃት የሚወጣውም ሆነ ለታናናሾቹ መልካም ነገር ለማስተላለፍ መሰረት የሚጥለው ዛሬ በሚያከናውናቸው ተግባራት ነው፡፡ ወጣቱ ትውልድ የሚፈፅማቸው መልካም ነገሮች ነገ እሱን ለሚተኩት ታዳጊዎች ጠንካራ መሰረት ይሆናቸዋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የሚያበላሻቸው ነገሮችና የሚፈፅማቸው ስህተቶች በታዳጊዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዲሁም ወደፊት የሚጋፈጡት የቤት ስራ ይፈጥርባቸዋል፡፡ ዛሬ ያለው የኢትዮጵያ ወጣት በዚህ መሰረተ ሃሳብ ላይ የተሟላ ግልፅነት መያዝና አገር ተረካቢነት ሚናውን በብቃት ለማከናወን መረባረብ ይጠበቅበታል፡፡

ለዛሬው የኢትዮጵያ ወጣት አገር ያስረከቡት የትናንት ወጣቶች ከታላቆቻቸው የተረከብዋት ኢትዮጵያ ጭራሹን መልካም የሚባል ነገር አልነበራትም ባይባልም እልቆ መሳፍርት ችግሮች የተደራረቡባት እንደነበረች ግን የማይደበቅ የትናንት ታሪካችን ነው፡፡ ሰፊው የአገራችን ህዝብ የእለት ጉርሱን አሟልቶ ማግኘት የማይችልባት፤ ለጥቂቶች መሳፍንትና መኳንንት ምድራዊ ገነት ለብዙሃኑ ደግሞ ሲኦል የሆነች፣ የዜጎች ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች የተረገጡባት፤ “ባለስልጣን አይከሰስ፣ ሰማይ አይታረስ” የሚል ይትባህል የሰፈነባት፣ የብሄሮችና ብሄረሰቦች እስር ቤት የሆነች አገር ነው የነበረችው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች የሚደርስባቸውን አስከፊ ብዝበዛና ጭቆና ተቃውመው ያደረጉትን ትግል እርካብ በማድረግ በስልጣን ኮርቻ ላይ የተፈናጠጠው የደርግ መንግስትም በህዝቦች ላይ የሚደርሰውን ጭቆናና ብዝበዛ በአዲስና በከፋ መንገድ ነበር ያስቀጠለው፡፡

ስለሆነም ለዛሬው ወጣት አገር እያስረከበ የሚገኘው ትውልድ አገራችንን የወደቀችበትን አስከፊ ሁኔታ የመቀየርና ለቀጣዩ ትውልድ የተሻለች ኢትዮጵያን የማስረከብ ሃላፊነት ተሸክሞ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ የደርግ መንግስት የመጨረሻዎቹ አመታት በመላ አገሪቱ የጦርነት ነዲድ የሚንቀለቀልበት፣ ሁሉም ነገር ወደ ጦርነት በሚለው የደርግ አዋጅ የተነሳ የአገሪቱ ወጣቶችና ቁሳዊ ሃብት ለጦርነቱ የሚገበሩበት፣ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ተሽመድምዶ የወደቀበት ህዝቡ የዛሬን ካልሆነ በቀር ነገ ምን ይዞ እንደሚመጣ ርግጠኛ ያልነበረበት፤ አገሪቱ ዛሬ ወይም ነገ እንደነ ሶማሊያ ትበታተናለች ተብሎ የሚሰጋበት ብቻ ሳይሆን የማያጠራጥር ፍፃሜ ተደርጎ

የተወሰደበት፣ በአጠቃላይ አገራችን በድቅድቅ ጨለማ የተዋጠችበት ወቅት ነበር፡፡ የያኔው ወጣት ይህንን ጨለማ ለመግፈፍ መከፈል የሚገባውን የህይወት መስዋእትነት ከፍሎ የዛሬ 25 አመት ብሩህ ተስፋ የናኘበት አዲስ የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት መድረክ ከፍቷል፡፡ እነሆም ባለፉት 25 አመታት በአገራችን ተአምር የሚባሉ ለውጦች መጥተዋል፡፡ በማያቋርጥ ማሽቆልቆል ወደ ውድቀት በማምራት ላይ የነበረችው አገራችን በማያቋርጥ አኳኋን ማንሰራራትና ወደ እድገት መሸጋገር ችላለች፡፡ በሰላምና ዴሞክራሲ መታጣት ምክንያት የመበታተን ስጋት ተጋርጦባት የቆየችው አገራችን በህዝቦቿ ፈቅዶ መዋሃድ ጠንካራ አንድነት የፈጠረች አገር ሆናለች፡፡

በፈጣን እድገት እየገሰገሰች የምትገኘውን አገር የተረከበው የዛሬው ወጣት አዲሱ መድረክ የዛሬ 25 አመት ሲከፈት በአብዛኛው ያልተወለደና ነብስ ያላወቀ የነበረ ቢሆንም የሚረከባት ኢትዮጵያ ታላቅ ወንድምና እህቶቹ ባለፉበት አስቸጋሪ ሁኔታ እንዲያልፍ የማይጠየቅባት፣ የተሻለ እድልና ተስፋ የሚያገኝባት፣ ቀጣይነት ባለው እድገት ወደፊት የሚራመድበት እንጂ ባለበት የማይቆምባት ወይም ደግሞ ወደኋላ የማይመለስባት፣ ሰላም የሰፈነባትና መብቱ የተከበረባት እንድትሆን የተደረገውንና በመደረግም ላይ ያለውን ጥረት እያስተዋለ እንዳደገ ይታመናል፡፡ ይህ ወጣት ከታላቆቹ እየተረከባት ያለችውን በፈጣን እድገት ላይ የምትገኝና ታላቅ ተስፋ የፈነጠቀባትን አገር በጀመረችው ብቻ ሳይሆን በላቀ ፍጥነት ወደፊት እንድትገሰግስ ሌት ተቀን መትጋት፣ ወደ ኋላ ሊመልሳት የሚችልን ማናቸውም አይነት አፍራሽ ድርጊት በንቃት መጠበቅ ይገባዋል፡፡ ሰሞኑን በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ተከስተው በነበሩት ሁከቶች የተሳተፉ ወጣቶች እንዲሁም መላው የአገራችን ወጣቶች ሁኔታውን ከዚህ መሰረተ ሃሳብ አኳያ በጥሞና መገምገምና ዳግም የማይከሰትበትን አጋጣሚ ዝግ ለማድረግ የሚጠበቅባቸውን ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንን ሚና በብቃት መወጣት ይችሉ ዘንድም የሚከተሉትን አበይት ጉዳዮች በተግባር መተርጎም ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 7.1 መንግስት የዘረጋቸውን መልካም እድሎች አሚጦ መጠቀም

መንግስት ወጣቶች በአገራቸው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ከውጤቱም ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥን አላማ ያደረገ የወጣቶች የልማትና የእድገት ፓኬጅ አዘጋጅቷል፡፡ ከፓኬጁ በመነሳትም ወጣቱ በቀጥታ የሚሳተፍባቸውና ተጠቃሚ የሚሆንባቸው የተለያዩ የልማት ፕሮግራሞችና እቅዶች እየተዘጋጁ በየክልሉ ወደ ትግበራ ገብተዋል፡፡ በዚህ ረገድ የአነስተኛና ጥቃቅን ድርጅቶች ስትራቴጂ፣ የቴክኒክና ሙያ እንዲሁም የፖሊ ቴክኒክ ስልጠናዎች፣ የከፍተኛ ትምህርት ቤቶችንና የስልጠና ተቋማትን ከኢንዱስትሪ ጋር የማስተሳሰር ፕሮግራሞች፣ የማሽነሪ ሊዝ አገልግሎት የሚሰጡ፣ ብድር የሚያቀርቡ ተቋማት እንዲቋቋሙና በስራ ላይ ያሉትም ለልማት ተኮር የወጣቶች ፕሮግራሞች ቅድሚያና ፍትሃዊ አገልግሎት እንዲሰጡ፣ ወዘተ… የሚያደርጉ ስራዎች ተጀምረው ጥቂት የማይባሉ ወጣቶችም ተጠቃሚዎች ሆነዋል፡፡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን የአምስት አመት እቅድ ዘመን በአገር ደረጃ ከ10 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡ በ2008 ደግሞ 1.7 ሚሊዮን ወጣቶች ስራ አግኝተዋል፡፡

ይሁንናም ሁሉም ወጣቶች ይህንን የመንግስት ጥረት አሚጠው መጠቀም አልቻሉም፡፡ በዚህ በኩል ቀላል የማይባሉ ድክመቶች ይታያሉ፡፡ ቀዳሚውና ዋነኛው ችግር ሁሉንም ነገር መንግስት እንዲያሟላ የመፈለግ የጠባቂነት አስተሳሰብ ነው፡፡ መንግስት ማድረግ የሚገባውን ሊያደርግ በሚችለው መጠን ማከናወን ይኖርበታል፡፡ ይህም ሆኖ ግን ሁሌም ሁሉ ነገር በታቀደው መልክ ይከናወናል ማለት አይሆንም፡፡ መንግስት እስካላሟላ ድረስ ሁሉም ነገር ይቅርብኝ የሚል አስተሳሰብ ተገቢም ጠቃሚም አይደለም፡፡ ወጣቱ ከሁሉ በፊት ራሱን ለለውጥ ማዘጋጀት፣ ከእሱ የሚጠበቀውን ሙሉ አቅሙ በፈቀደለት መጠን ማከናወን፣ የመንግስትን ሚና እንደ አጋዥነት በመውሰድ አሚጦ መጠቀም ይኖርበታል፡፡

ሌላው ድክመት ደግሞ ስራ በማማረጥ በኩል የሚታየው ዝንባሌ ነው፡፡ የተሻለ ነገር መፈለግ በራሱ ስህተት ወይም ነውር አይደለም፡፡

ህብረተሰብ የሚያድገው የሰው ልጆች ሁሌም ወደ ተሻለና ያደገ ደረጃ ለመሸጋገር በሚያደርጉት ጥረት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በወጣቶች ዘንድ ይታያል የምንለው የስራ ማማረጥ ድክመት ብዙ አማራጮች በቀረቡበት ሁኔታ የተሻለ ጥቅም የሚያስገኘውን፣ በቀጣይም ወደ ከፍተኛ ተጠቃሚነት ሊያሸጋግራቸው የሚችለውን ለምን ይመርጣሉ ከሚል እንደማይነሳ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ በወጣቶች የሚታየው የስራ ማማረጥ ችግር ስራ አጥቶ በመቀመጥና ያለውን የስራ እድል በመጠቀም አማራጭ ላይ በሚወስዱት ውሳኔ ላይ ያለ ችግር ነው፡፡ አንዱን ስራ የተከበረ ሌላውን ደግሞ የተዋረደ አድርጎ የሚመለከተው አስተሳሰብ ነው ሊስተካከል ይገባዋል የምንለው፡፡

ከዚሁ ጋር የሚያያዘው ሌላው ድክመት ደግሞ የወር ደሞዝተኛ በሚያደርግ ስራ መቀጠርን እንደብቸኛ አማራጭ የመውሰድ ችግር ነው፡፡ ወጣቱ ትውልድ ተዘጋጅቶ የሚጠብቀው ስራ ፈላጊ ሳይሆን ስራ ፈጣሪ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከትምህርትና ስልጠና የሚገኘው እውቀትና ክህሎት ስራ ለመፍጠር ትልቅ መነሻ ይሆናል፡፡ ስራ ለመጀመር የሚያስፈልጉትን ሌሎች ግብአቶች ለማግኘት ደግሞ የተለያዩ በሮችን ማንኳኳት ይጠይቃል፡፡ ይህ እንዲሆን ዋነኛው ሃብት ራስን ማዘጋጀትና የሚጠይቀውን ያህል ጥረት ማድረግ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህን ጉዳዮች አስመልክቶ በየደረጃው በወጣቱና አግባብ ባላቸው የመንግስት አካላት መካከል ግልፅና ዝርዝር ውይይት በማድረግ ወጣቱ በመንግስት በኩል የተቀየሱትን ፕሮግራሞች አሟጦ መጠቀም የሚችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## 7.2 መልስ ያላገኙ የወጣቱ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ከመንግስት ጎን መቆም

በአገራችን እየተከናወነ ካለው ፈጣን እድገት ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ በመሆን ላይ እንደሚገኝ የሚታወቅ ቢሆንም በሚፈለገው መጠን ያልተጠቀሙ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዳሉ በተደጋጋሚ አንስተናል፡፡በሚፈለገው መጠን አልተጠቀሙም ከምንላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አንዱ ወጣቱ እንደሆነም አያከራክርም፡፡ እንዲሟሉለት የሚፈልጋቸውና በብቃት ምላሽ ያላገኙ የወጣቱ ጥያቄዎች እንዳሉ

መንግስት ይረዳል፤ ትኩረት ተሰጥቷቸው መፈታት እንደሚገባቸውም ያምናል፡፡ በዚህ ረገድ ከሚነሱት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የስራ አጥነት፣ የትምህርትና ስልጠናው ጥራት፣ ከመልካም አስተዳደር ጋር የሚያያዙት የአድልዎና በፍጥነት ውሳኔ ያለማግኘትና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

በየትኛውም አካባቢ ያሉ ወጣቶች በግልፅ የሚያቀርቡዋቸው ከስራ እድል ጋር የተያያዙ የመልካም አስተዳደር ችግሮች መንግስት ተገቢ ትኩረት ሰጥቶ ይዋል ይደር ሳይል ሊፈታቸው የሚገቡ ናቸው፡፡ ከመሰረቱ ለመፍታት ርብርብ ማድረግ ከሚጠይቀው የስራ አጥነት ችግር በተጓዳኝ በተገኘውም የስራ እድል በመጠቀም በኩል ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድ በጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ለመሳተፍ፣ መንግስት በሚከፍታቸው መዋቅሮችና ፕሮጄክቶች በነፃ ተወዳድሮ ተጠቃሚ ለመሆን እንቅፋቶቹ እጅግ ሰፊ ናቸው፡፡ አላስፈላጊ በሆነ መንገድ ከሚጠየቅ የትምህርት ደረጃና የስራ ልምድ ጀምሮ፣ የድርጅት አባልነት፣ ብሄር፣ ወዘተ... የሚባሉት መመዘኛዎች ማነቆ ይሆናሉ፡፡ አስቀድመው ተይዘው ለይስሙላ ያህል የሚወጡ ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያዎች እንዳሉ፣ በዘመድ፣ በመተዋወቅ አሊያም በጉቦ ካልሆነ በቀር በነፃ ስራ እንደማይገኝ ፀሐይ የሞቀው ሐቅ መሆን ከጀመረ ቆይቷል፡፡ እንደነዚህ ያሉት ከመልካም አስተዳደር ጋር የተያያዙ እንቅፋቶች የስራ አጥነቱን ችግር የሚያባብሱ ከመሆናቸው ሌላ ለማህበራዊ ጠንቆችም መዘዝ ይሆናሉ፡፡ በተጨባጭም ብዙ ወጣቶች ተስፋ እንዲቆርጡና ራሳቸውን እንዲጠሉ፣ ለተለያዩ ሱሶች እንዲዳረጉ፣ ለወንጀለኛነትና አመፀኝነት እንዲጋለጡ፣ በመንግስት ላይ እምነት የማጣትና የጥላቻ መንፈስ እንዲያሳድሩ፣ አገራቸውን ምኔ ናት እንዲሉ ወደተገደዱበት ደረጃ እየደረሱ ነው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ በሰሞኑ ተቃውሞ ተንፀባርቀዋል፡፡

መንግስት ለነዚህና መሰል ወጣቱን ያስመረሩ ችግሮች ጆሮ ዳባ ብሎ ማለፍ ከቶ አይችልም፡፡ በኢህአዴግ አመራር የተወሰነው የእንደገና በጥልቀት የመታደስ ንቅናቄ ስር ነቀል በሆነ መንገድ እንዲፈታቸው የሚጠበቁት ችግሮች እነዚህንም የሚያካትት ይሆናል፡፡ በመሆኑም ወጣቱ ኢህአዴግና መንግስት የወጣቱን ችግሮች ለመፍታት በቁርጠኝነት እንደተነሱና ወጣቱ አልተመለሱልኝም የሚላቸው ጥያቄዎች መልስ እንደሚያገኙ በእምነት

መቀበል፣ ቢያንስ ደግሞ ጊዜ ሰጥቶ በትእግስት ለመጠበቅ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ሁሉም ነገር በአንድ ጀንበር የሚሰራ እንደማይሆን ለማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ በህብረተሰብ ውስጥ የሚካሄድ ለውጥ ሂደት እንጂ የአንድ ቅፅበት ስራ ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም የአገራችን ወጣቶች የሚፈታተኗቸውን ችግሮች ለመፍታት በመንግስት በኩል የሚካሄዱትን ጥረቶች መደገፍ፣ ከወጣቱ የሚጠበቀውን ድርሻ በአግባቡ መወጣት፣ ጥረቶቹን ለማደናቀፍ የሚደረጉ ሙከራዎችን ከመንግስት ጋር በመሆን ማክሸፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 7.3 የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ድርጊትን አምርሮ መታገል

ኪራይ ሰብሳቢነት አገራችን የተያያዘችውን ልማታዊና ደሞክራሲያዊ የእድገት አቅጣጫ የሚፈታተን የስርዓታችን አደጋ ነው፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነት ሙሉ በሙሉ የበላይነቱን እስከሚያጣ ድረስ በተለያየ መልክ እየተከሰተ ልማታዊና ደሞክራሲያዊ ጉዟችንን ከማደናቀፍ ቤት አይውልም፡፡ የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ድርጊት ደግሞ በእገሌና በእዚያ ቦታ ላይ ብቻ የማይወሰን፣ ከደሙ ንፁህ ነኝ የማይባልበት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በአንዱ ወይም በሌላው መገለጫ ተጠናውቶ የሚገኝ ችግር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ወጣቱም የዚህ ችግር ሰለባ እንደሆነ በቂ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡

በአሁኑ ወቅት በአገራችን ኪራይ ሰብሳቢነት ከሚገለፅባቸው ችግሮች አንዱና ዋነኛው ትምክህትና ጠባብነት ነው፡፡ የሁለቱም መነሻ ብሄራዊ ማንነትን መጠጊያ በማድረግ በአቋራጭ መጠቀም ነው፡፡ አገራችን የየራሳቸው ማንነት ያላቸው የብዙ ብሔር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች አገር ናት የሚለውን የማይቀበልና ፌዴራላዊ ስርዓቱን አምርሮ የሚቃወመው ትምክህትና ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር አብሮ መኖር ተጠቃሚ አያደርገኝም በሚል በራሱ ብሄር መታጠር የሚፈልገው ጠባብነት ሁለቱም አገራችን እየተጓዘችበት የምትገኘውን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ የእድገት አቅጣጫ ይቃወማሉ፡፡

ትምክህትና ጠባብነት ተፃራሪ የሚመስል አቋም ያላቸው ቢሆኑም ሁለቱም ፀረ ዴሞክራሲ፣ ፀረ አንድነትና የህዝቦች ዘላቂ ጥቅም ፀሮች ናቸው፡፡

የህዝቦችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ በሚኖርበት ወቅት ደግሞ የጋራ ግንባር ፈጥረው ይፋለሙታል፡፡ ዛሬ በአገራችን እየታየ ያለውም ይኸው ነው፡፡

ትምክህተኞች አስፀያፊ ዘረኛ ፕሮፖጋንዳ በመንዛት በህዝቦች መካከል ጥላቻና ቂም እንዲነግስ ለማድረግ መሄድ የሚችሉበትን ያህል ርቀት ሄደዋል፡፡ ጠባቦችም ተበድለናል በሚል በብሄሩ ተወላጅ መካከል የተዳበለ አንድነት እንዲፈጠርና ራሳቸው ከሚፈጥሩለት ሃሳባዊ ጥቃት እንዲከላከል በሚችሉት መንገድ ሲሰብኩ ሰንብተዋል፡፡ ሁሉም ግን ጠባቸው አገራችን በታሪኳ አይታው በማታውቀው ደረጃ ኢኮኖሚዋ እንዲያድግ፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ፤ ሁሉም ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ኢትዮጵያ የጋራ አገራችን ናት ብለው እንዲያምኑና ለእድገት ብልፅግናዋም ተሳስረው እንዲንቀሳቀሱ፣ የሚያጋጥማትንም ማናቸውንም ጥቃት እንደ አንድ ህዝብ ሆነው እንዲመክቱ ካበቃው ፌዴራላዊ ዴሞክራያዊ ስርዓት ጋር ነው፡፡ በተፈጠረው ሁከት በአማራም ሆነ በኦሮሚያ ክልል የኢትጵያ ብሔር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የአንድነታቸው መገለጫ እንደሆነ የተቀበሉት አርማ ያለው የኢትየጵያ ሰንደቅ አላማ መውረዱም ይህንኑ ነው የሚያስረዳው፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ወጣቶች ትምክህትንና ጠባብነትን መታገል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከትምክህትና ጠባብነት የሚነሱ ጥያቄዎች በጥንቃቄ ካልተያዙና የተሳሳቱ መሆናቸው በአግባቡ ካልተጋለጠ የሚያስከትሉት መዘዝ ቀላል አይደለም፡፡ አለማችን በትምክህትና ጠባብነት ምክንያት ከፍተኛ ደም መፋሰስ የተካሄደባቸው በረጅም ጊዜ የገነቡት በሰአታትና በቀናት የተናደባቸው፣ ከትልቅ አገር ወደ ትናንሽና ደካማ አገሮች የተበተኑ ብዙ አገሮችን አይታለች፡፡ ትምክህትና ጠባብነት ሁለቱም የኪራይ ሰብሳቢነት ፍላጎት የሚወልዳቸው ናቸውና ፍፃሜያቸው የዜሮ ድምር ጨዋታ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከዚህ ጨዋታ፣ ከመበታተን የዳነችው ለትምክህትና ጠባብነት እድል የማይሰጥ ጠንካራ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመትከል በመቻሏ ነው፡፡ በአገራችን በመገንባት ላይ ያለው ስርዓት አንድ ብሄር በሌሎች ላይ የበላይ ሊሆን የሚችልበት አንዳችም ቀዳዳ የለውም፡፡ እየገነባን ያለነው ስርዓት ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች አካባቢያቸውን እንዲያስተዳድሩ፣ የአካባቢያቸውን ፀጋ በማልማት ኢኮኖሚያቸውን እንዲያሳድጉ የሚፈቅድ

እንጂ የአንዱን እጅና እግር አስሮ ሌላውን እንደፈለገ እንዲፏልል እድል የሚሰጥ አይደለም፡፡ ፌዴራል ስርዓቱ ከሚፈቅደው ውጭ በመንቀሳቀስ አላግባብ የተጠቀሙ የየትኛውም ብሄር ተወላጅ የሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ቢኖሩ በጭራሽ ብሄራቸውን አይወክሉም፣ በነሱ ምክንያትም የተወለዱበት ብሄር ህዝብ ተወቃሽም ተጠያቂም አይሆንም፡፡ ኪራይ ሰብሳቢዎች የመጡበትንም ህዝብ ጥቅም የሚፃረሩ በመሆናቸው ሁላችንም ብሄር ሳንለይ በጋራ ልንታገላቸው ነው የሚገባው፡፡ የአገራችን ወጣቶች ይህንን በጥሞና ማስተዋልና ሁሌም ራሳቸውን ከትምክህትና ጠባብነት አስተሳሰብ ነፃ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በሌላም በኩል የአገራችን ወጣቶች በራሳቸው ጥረትና የስራ ውጤት እንጂ በአቋራጭ መንገድ የመክበር ፍላጎትና ተግባርን እንዲፀየፉ ይጠበቃል፡፡ እውቀታቸውንና ተነሳሽነታቸውን በመጠቀም በፍጥነት ወደ እድገት በመረማመድ ላይ የሚገኙ በርካታ ወጣቶች ያሉትን ያህል በአቋራጭ መንገድ ለመክበር የሚሯሯጡና መክበርም የጀመሩ እንዳሉ እናያለን፡፡ ከፊሉ በስልጣን ላይ ባለ ዘመድ ወይም አብሮ አደግና ሌላ ግንኙነት አማካይነት በማለፍ፣ አንዳንዱ ወጣትም በሚሰራበት ቦታ ያገኘውን ለዝርፊያና ለማጭበርበር የተመቸ አጋጣሚ በመጠቀም፤ ሌላው ደግሞ ከሌቦችና ዘራፊዎች ጋር በመተባበር፣ በዘመኑ ቋንቋ "ቢዝነስ በመስራት" የወጣትነት እድሜው ያስገኝለታል ተብሎ ከሚገመተው በላይ ሃብታም ሲሆን ይታያል፡፡ እንደነዚህ ያሉት ሁኔታዎች በቀሪውም ወጣት እንደነእንቶኔ "ልናውቅበት ይገባል" የሚል "የአባትህ ቤት ሲወረር አብረህ ውረር" ቅኝት እየያዘ የኪራይ ሰብሳቢነትን ጎራ የሚያጠናክር ሁኔታ በመፈጠር ላይ ይገኛል፡፡ የአገራችን ወጣቶች ከእንደዚህ አይነቱ አገርን ከሚያጠፋ የሙስናና በአቋራጭ የመክበር ቅኝት መላቀቅ፣ በሙስና የሚታወቁና የሚጠረጠሩ ሰዎችን ቤተሰብንም ጭምር ከአድራጎታቸው እንዲቆጠቡ መታገልና ከጥፋታቸው እንዲታረሙም ማጋለጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በሙስና የከበሩትን ሳይሆን እውቀታቸውንና ጉልበታቸውን በመጠቀም የተሻለ ኑሮ መኖር የቻሉትን ወጣቶች አርአያነት መከተል ይገባቸዋል፡፡ "የሚሰራ ቢዝነስ" ካለም ትክክለኛው መንገድ የራስህን የፈጠራ ችሎታና ታታሪነት እንዲሁም በአገሪቱ የተፈጠረውን አስቻይ ሁኔታ በአግባቡ በመጠቀም ውጤታማ ሆኖ መገኘት እንደሆነ ብሄራዊ መግባባት ሊፈጠርበት ይገባል፡፡

## 7.4 ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ ባህሎችን ማጎልበት

አዲሲቷን ኢትዮጵያ የሚረከቡት የአገራችን ወጣቶች ከሚጠብቃቸው የትውልድ ሃላፊነት አንዱ በአገሪቱ የተጀመረው የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲሸጋገር ማድረግ ነው፡፡ በተደጋጋሚ እንደሚገለፀው የዴሞክራሲ ጉዳይ ለእኛ ኢትዮጵያውያን የህልውና ጉዳይ ነው፡፡ ዴሞክራሲያችን ባደገና በሰፋ መጠን የአገራችን እድገትና የህዝቦችዋ ብልፅግና እየሰፋና ስር እየሰደደ ይሄዳል፡፡ ዴሞክራሲው መሸራረፍ ሲጀምርና በጨቅላነቱ ሲቀጭ ደግሞ የአገራችን እጣ ፈንታ መበታተን፣ ህዝቦቿም በየተበተኑበት ሆነው በድህነትና ኋላቀርነት ሰቆቃ እየማቀቁ መኖር ይሆናል፡፡ ስለሆነም በአንድ በኩል የአገራችን ወጣቶች ለዴሞክራሲ ቀናኢና ዴሞክራሲያችን እንዲጎለብትና ስር እንዲሰድ፤ ዴሞክራሲያዊ ግንኙነቶች እንዲዳብሩ፣ ዴሞክራሲያዊ ባህሎች እንዲስፋፉ፣ የቡድንና የግለሰቦች መብቶች ያለአንዳች መሸራረፍ እንዲከበሩ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ የሆኑ አስተሳሰቦችና ተግባሮች ፈጥነው እንዲታረሙ የዜግነት ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ በአገራችን ጎልተው የሚታዩ ለዴሞክራሲያችንና ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ ባህሎች እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን መዳሰስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የመጀመሪያው ችግር በቡድን መብቶች አከባበር ላይ ያለው ዝንባሌና የተሳሳተ ተግባር ነው፡፡ የቡድን መብቶች የሚባሉት የብሄርና ብሄረሰቦች፣ የሴቶችና የሃይማኖቶች እኩልነትን ይመለከታል፡፡ የእነዚህ መብቶች መሰረተ ሃሳብ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባልነበረበት ዘመን እኩልነታቸውን ተነፍገው የኖሩት የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል መሆናቸው በተግባር የሚረጋገጥበት ስርዓት ይገንባ የሚል ነው፡፡ በዚህ ረገድ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት እኩል መሆናቸውን በግልፅ ደንግጓል፡፡ የእነዚህን ህብረተሰቦች እኩልነት በተግባር የማረጋገጥ ጉዳይ ግን ከህገ መንግስታዊ እውቅና ባሻገር ሄዶ ዴሞክራሲያዊ ባህል መሆንን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ አኳያ የተጀማመሩ አበረታች ስራዎች የሉም፣ አንዳችም መልካም ውጤት አልተገኘም ባይባልም ቀጣይ ትግል የሚጠይቁ በርካታ ችግሮች አሉ፡፡ በዚህ ረገድ የብሄር ብሄረሰቦችን እኩልነት በሚመለከት ከትምክህትና ጠባብነት ችግር

ጋር በማያያዛ ከሞላ ጎደል ስለዳሰስነው በሴቶችና የሃይማኖቶች እኩልነት ላይ የሚታዩ ችግሮችን አስመልክቶ የተወሰኑ ጉዳዮችን ማንሳት ተገቢ ይሆናል፡፡

በየትኛውም የአገራችን ክፍል የሴቶችን እኩልነት በሚመለከት ገና ብዙ መስራት የሚጠይቅ አንዳንዴም እጅግ የሚያስፈራ ሁኔታ ይታያል፡፡ ሴቶችን የበታች አድርጎ የሚያቀርበው አስተሳሰብና ልማድ በሁሉም ቦታ ማለት በሚያስችል ደረጃ መረን በለቀቀ አኳኋን ተንሰራፍቶ ይገኛል፡፡ ዛሬም ሴቶች በጎጅ ባህሎች ይሰቃያሉ፣ በወንዶች ይጠቃሉ፣ በፍትህ እጦት ይንገላታሉ፡፡ እኩልነታቸው በህግ እውቅና ቢያገኝም ህጉን የሚፃረር አድሎ ይፈፀምባቸዋል፡፡ ሴቶች በአገራቸው ጉዳይ ላይ እኩል የመሳተፍና የመወሰን መብት እንዲኖራቸው በማስቻል በኩል የተሰራውና የተገኘው ውጤት አነስተኛ ነው፡፡ በየደረጃው ባለ የመንግስት መዋቅርና መንግስታዊ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን በግል ተቋሞችና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ጭምር ወደ አመራር የሚመጡት ሴቶች ከቁጥር የሚገባ አይደለም፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንገንባ ሲባል አንዱ መፈታት ያለበት ችግር ይህ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የአገራችን ወጣቶች በሴቶች ጥያቄ ላይ የተስተካከለ አስተሳሰብ ሊይዙ ይገባል፡፡ የህብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑት ሴቶች መብት ባልተከበረበት ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንገነባለን ማለት ፖለቲካዊ ሽፍጥ ብቻ ነው የሚሆነው፡፡ ሴትን የሚያዋርድ፣ የሴትን መብት የሚጋፋ፣ በሴት ላይ ጉዳት በማድረስ በበላይነት ስሜት የሚኮፈስ ወጣት የዛሬዋም ሆነ የነገዋ ኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሃይል ሊሆን አይችልም፡፡ ከዚህ በመነሳት የሴቶችን እኩልነት በተግባር ለማረጋገጥ መንቀሳቀስ፣ የሴቶችን እኩልነት የሚፃረሩ ሁሉንም አይነት ተግባራት መታገል ከኢትዮጵያ ወጣቶች ይጠበቃል፡፡ ይህ ሲባል ትግሉ የወንዱ ወይም የሴቷ ወጣት የተናጠል ጥረት ሳይሆን ሁለቱም ፆታዎች እንደወጣት በአንድነት የሚያካሂዱት እንደሆነ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡

ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ ባህሎችን ከማጎልበት አኳያ ሌላው ትኩረት የሚያስፈልገው ጉዳይ የሃይማኖት እኩልነትን የሚመለከተው ነው፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተቻችለውና ተከባብረው አብረው የኖሩባት አገር እንደሆነች ይታወቃል፡፡ ይህ አብሮነት ደግሞ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት ላይ ሁሉም ሃይማኖቶች በህግ እኩል እውቅና

እንዳላቸው፣ መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ እንደሆኑና መንግስታዊ ሃይማኖት እንደሌለ በሚደነግገው ህግ ይበልጥ ዳብሯል፡፡ ይህ የቡድን መብት ማንኛውም ዜጋ የፈለገውን እምነት የመከተል ነፃነት አለው ከሚለው የግለሰብ መብት ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ከዚህ ህግ አንዱ ሃይማኖት ከሌላው የበላይ ወይም የበታች ተደርጎ መታየት እንደሌለበት፣ ማንኛውም ዜጋ ለምን የዚህ ሃይማኖት ተከታይ ሆንክ ተብሎ ሊወገዝ ወይም ሊጥላላ እንደማይገባው ወይም ደግሞ የአንድ ሃይማኖት ተከታይ እንዲሆን ማስገደድ ህጋዊ እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡

ይሁንናም በአሁኑ ሰአት በአገራችን ለረጅም ጊዜ ተጠብቆ የቆየውን መቻቻልና አብሮነት እንዲሁም በኢፌዴሪ ህገ መንግስት እውቅና የተሰጠውን የሃይማኖት እኩልነት የሚፃረሩ ድርጊቶች ይታያሉ፡፡ በሁሉም ሃይማኖቶች የአክራሪነት ዝንባሌዎች እየሰፉ በተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ግጭቶች የሚያጋጥሙበት ሁኔታ ሰፋ ያሉ አካባቢዎችን የሚሸፍን ችግር እየሆነ መጥቷል፡፡ በመሰረቱ ከዴሞክራሲ እሴቶች አንዱ የሆነውንና በብዙዎቹም ሃይማኖቶች የሚነገረውን "በአንተ እንዲደረግ የማትፈልገውን በሌሎች አታድርግ" የሚለውን አስተምህሮ የሚፃረሩ አፍራሽ እንቅስቃሴዎች በብዙ አካባቢዎች ይታያሉ፡፡ እሱ ቅዱስ የሚለውን የእምነት ቦታ የሚደፍርበት፣ የሚያዋርድበት እንዲኖር እንደማይፈልግ እያመነ ሌላው ቅዱስ የሚለውን ቦታ ይደፍራል፤ እንዲያም ሲል ያወድማል፡፡ የራሱ እምነት እንዲወገዝ እንደማይፈልገው የሌላውም ሰው እምነት መወገዝ እንደሌለበት ባለመቀበል የሌሎችን እምነት ያወግዛል፣ የእሱ ብቻ ትክክለኛ የሌላው ግን የተሳሳተ እንደሆነ ይሰብካል፣ እንዲያም ሲል የግድ የእኔን እምነት ተቀበሉ በሚል ሁከት ይፈጥራል፡፡ የዚህ አይነቱ አስተሳሰብና ድርጊት ህጋዊ አይደለም፤ ለአገርና ለህዝብም አይጠቅምም፡፡ የዚህ አይነት አፍራሽ አስተሳሰብና ድርጊት በመሰረቱ ከሃይማኖቶቹ አስተምህሮ የሚመነጭ ሳይሆን በሃይማኖቶቹ ስም ለመጠቀም የሚደረግ የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር ነው፡፡ ስለሆነም የአገራችን ወጣቶች በሃይማኖቶች መካከል ተቻችሎና ተከባብሮ አብሮ የመኖር ዴሞክራሲያዊ ባህል እንዲጎለብት፤ በየትኛውም ሃይማኖት ስም የሚራመድ አክራሪነትና ሃይማኖትን ሰበብ በማድረግ የሚፈጠር ሁከት እንዲወገድ በንቃት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም ለሁሉም

የሃይማኖት ተከታዮች አገልግሎት የሚሰጡ (Secular የሆኑ) እንደ ት/ቤቶችና የመንግስት መ/ቤቶች የመሳሰሉት ገለልተኛነታቸው መከበር ይኖርበታል፡፡

የአገራችን ወጣቶች ከዴሞክራሲያዊ ባህል ግንባታ ጋር በተያያዘ ትኩረት ሊሰጡዋቸው የሚገቡ ሌሎችም እሴቶች አሉ፡፡ ምክንያታዊነት (Rationality)፣ የተለየ ሃሳብን ማስተናገድ (Tolerance)፣ የህግ የበላይነት (Rule of Law) የሚሉት የዴሞክራሲያዊ ባህል ግንባታችን መሰረት የሆኑ እሴቶች ናቸው፡፡ የአገራችን ወጣቶች የእነዚህን እሴቶች መሰረት ሃሳብ በትክክል መረዳትና አስታዋሽ ሳያስፈልጋቸው በቀን ተቀን እንቅስቃሴያቸው በተግባር የሚተረጉሟቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ ወጣቶች በስማ በለው የሚመሩ፣ በአሉባልታ የሚነጉዱ መሆን የለባቸውም፤ የሰሙትን፣ የተነገሩትን በሙሉ እንዳለ የሚቀበሉም እንዲሆኑ አይጠበቅም፡፡ የሚናገሩትን፣ የሚሰሩትን፣ የሚወስኑትን በሙሉ ለምን እንደሚያደርጉት አመዛዝነውና ሙሉ እምነት ይዘውበት የሚፈፅሙበት ሁኔታ መኖር አለበት፡፡ በተለይም ማንም ተቆጣጣሪና ተጠያቂ በሌለበት ማንኛውም ሰው የፈለገውን ነገር በማህበራዊ ሚዲያ ማሰራጨት በሚችልበት በዚህ ወቅት ወጣቱ ሊቀበው የሚገባውና የማይገባውን መረጃ በጥንቃቄ መለየት መቻል ይኖርበታል፡፡ ያለአንዳች ምክንያታዊነት እገሌ ስላለ ወይም ከነእገሌ ላለመለየት በመሳሰሉ ኢ-ምክንያታዊነት የሚወሰዱ ውሳኔዎች ፍፃሜያቸው ጉዳት መሆኑ አይቀርም፡፡

ሌላው ከወጣቶች የሚጠበቀው ዴሞክራሲያዊ ባህል ደግሞ የተለየ ሃሳብን የማስተናገድ እሴት ነው፡፡ መስማት ያለብን መስማት የምንፈልገውን ብቻ አይደለም፤ ይህንን ለማድረግ ዴሞክራሲያዊ መሆንን አይጠይቅም፡፡ የዴሞክራሲ ቃሉ እንኳ በማይታወቅበት ዘመንም መኳንንቱና መሳፍንቱ አወዳሾችን የሚሰሙበት ፕሮግራም ነበራቸው፡፡ ዴሞክራሲያዊ ባህል እንገንባ ሲባል የማንፈልገውንም የመስማት፣ ማንኛውም ሰው ሃሳቡን በነፃ እንዲያቀርብ መፍቀድ ወይም አለማደናቀፍ፣ ልዩነቶችን ለማስተናገድ ዝግጁ መሆን፤ የተለየ ሃሳብና አቋም ያለውን በጥላቻ አለመመልከት ወይም በጠላትነት አለመፈረጅና ወደ መጠቃቃት አለማምራትን ይጠይቃል፡፡ አንድ ሰው የተሳሳተ ነገር ቢናገርም የተሳሳተውን ሃሳቡንና ግለሰቡን በሚለይ አግባብ

ማስተናገድ የመሳሰሉትን መርሆዎች ያካትታል፡፡ የዚህ አይነት እሴት ማሳደግ በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ጠንካራ መሰረት ይጥላል፡፡ በዚህ ዙሪያ ሰፊ ችግር ስለሚታይ ወጣቱ ትውልድ ከወዲሁ ባህሉን እየገነባ እንዲሄድ ይጠበቃል፡፡

የህግ የበላይነትን ማክበርም ሌላው በዴሞክራሲያዊ ባህል ግንባታ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ እሴት ነው፡፡ የህግ የበላይነት በሌለበት ስርዓት አልበኝነት እንጂ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሊገነባ አይችልም፡፡ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት የዜጎች መብት ያላንዳች ገደብ ይከበራል፣ ነገር ግን የሌላውን ዜጋ መብት መጋፋት አይፈቀድም፡፡ ዴሞክራሲው የሚያገለግለው የህዝቦችን መብትና ጥቅም ለማስከበር በመሆኑ የህዝብን ጥቅምና መብት መፃረር የህግ ገደብ ይጣልበታል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ሰላም ያስፈልጋል፣ ሰላምን የሚያደፈርስ የህግ ክልከላ ይደረግበታል፡፡ ስለሆነም የአገራችን ወጣቶች የመብታቸውን መከበር ብቻ ሳይሆን ግዴታቸውንም ማወቅ፣ ማድረግ የሚፈልጉትንና የሚችሉትን ብቻ ሳይሆን እንዳያደርጉ የሚከለከሉትንም መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡ የልማትና የመልካም አስተዳደር ፍላጎቶቻቸው ሊሟሉላቸው የሚችሉት ጥያቄዎቻቸውን ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሲያቀርቡ እንደሆነ የጋራ መግባባት ሊፈጠር ይገባዋል፡፡ የህግ የበላይነት በሰፈነበት ሁኔታ ብቻ ነው አገር ሰላም የሚሆነው፣ የህዝቦችም ፍላጎት ሊሟላ የሚችለው፡፡ የሰላምና የህግ የበላይነት የመከበር ጉዳይ ስንፈልግ የምናደርገው፤ ካልፈለግን ደግሞ የምንሽረው ሊሆን ከቶ አይችልም፡፡

ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ ባህልን አስመልክቶ ከአገራችን ወጣቶች ከሚጠበቀው ውስጥ ሳይነሳ መታለፍ የሌለበት ሌላው ጉዳይ በብዙ አካባቢዎች የሚታየውና እንደሰደድ እሳት በመስፋፋት ላይ የሚገኘው የባህል ዝቅጠት ነው፡፡ አያሌ የአገራችን ወጣቶች በጫት፣ ሽሻና የተለያዩ አደንዛዥ እፆች ተጠቃሚነት፣ ከምእራባውያን በተቀዱ በየመጠጥና ምሽት ቤቱ በሚከናወኑ ፀያፍ ባህሎች አስፈሪ በሆነ ደረጃ በመበከል ደረጃ ይገኛሉ፡፡ የባህል ዝቅጠቱ መዘዝም ወንጀለኝነትንና ስራ ጠልነትን እያበራከተ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በባህል ዝቅጠት የተበከሉ ወጣቶች ብቁ አገር ተረካቢዎች አይሆኑም፡፡ በሱሶች የደነዘዙ ወጣቶች በትምህርትና ስልጠና ማደግ፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚና አበልፃጊ፣ አምራችና አገር ገንቢ የመሆን አቅማቸው ይሰለባል፡፡ ውሎ አድሮም

የአገር ሸክም ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም የአገራችን ወጣቶች ከዚህ አስፈሪ ዝቅጠት እንዲወጡ በመንግስት፣ በእያንዳንዱ ቤተሰብና በአጠቃላይም በህዝቡ ሰፊ ዘመቻ ማካሄድን ይጠይቃል፡፡ በዚህ ዘመቻ ውስጥ ወጣቶች ራሳቸው ንቁ ተዋንያን ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ እያንዳንዱ ወጣት ራሱን ከዚህ ችግር ነፃ ማውጣት፣ ቀጥሎ ደግሞ በቅርብ የሚያውቃቸውን ወጣቶች ማሳመን ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አግባብ ወጣቶች ከእነሱ የሚጠበቀውን እያከናወኑ ከህዝቡና መንግስት ጋር በመሆን በዘመቻው በንቃት መሳተፍ ይኖርባቸዋል፡፡

## 7.5 አገራዊ ፍቅርን ማሳደግ

ወጣቱ ትውልድ አገር ተረካቢ ነው ሲባል የእኔ የሚለው፣ ተወልዶ ያደገበትና የሚኖርበት አገር እንዳለው ታሳቢ ያደርጋል፡፡ ቢወለድና ቢያድግበትም ሊኖርበት የማይፈልግ ትውልድ አገር ተረካቢ አይሆንም። እንደዚህ ያለ ትውልድ ያለበት አገር የወላድ መካን በመሆኑ ቀጣይ መድረሻው ለእድል የተተወ ይሆናል፡፡ ወጣቱ ትውልድ በርግጥም አገር ተረካቢ እንዲሆን የመጀመሪያው ጉዳይ አገሩን የሚወድ መሆን ይኖርበታል፡፡ የአገሩን ታሪክ የሚያውቅ፣ አገሩ ያላትን ተስፋና ተግዳሮት የሚገነዘብ፤ ከዚህም በመነሳትም ከእሱ የሚጠበቀውን ሁሉ ለማድረግ የተዘጋጀ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ አገር ወዳድነት ብሄራዊ ስሜትን (nationalism) ማዳበር ማለት ነው፡፡ ብዙዎቹ አገሮች ብሄራዊ ስሜትን ለአገራቸው ግንባታ ተጠቅመውበታል፡፡ በኢትዮጵያም ብሄራዊ ስሜት አገርን ከውጭ ወራሪዎች ለመከላከል በተካሄዱ ጦርነቶች ሁሉ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡ አገራችን ሌላ ጦርነት፣ ከድህነትና ኋላ ቀርነት ነፃ ለመውጣት ሌላ ክተት በጠራችበት በአሁኑ ወቅት ከወራሪዎች ጋር እንደተደረገው ጦርነት ሁሉ የአገራችን ወጣቶች በታላቅ ብሄራዊ ስሜት እንዲከቱ ይጠበቃል፡፡

ይሁንናም የሚጠበቀውን ያህል ጠንካራ የአገር ፍቅርና ብሄራዊ ስሜት ተገንብቷል ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ ላይ አንገኝም፡፡ በዚህ ረገድ ኢህአዴግና የሚመራው መንግስት የሰሩት ስራ ደካማ እንደሆነ ይቀበላሉ፡፡ በትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የስነ- ዜጋ ትምህርት የታሰበውን ያህል ውጤታማ አልሆነም፡፡ የመንግስትም ሆነ የግል ሚዲያዎች ዜጎች ብሄራዊ ስሜትና የአገር ፍቅር እንዲያጎለብቱ የረባ አስተዋፅኦ አላደረጉም፤ ይልቁንም አሉታዊ አስተዋፆቸው የሚያይልበት ሁኔታ ይታያል፡፡ በአሁኑ

ወቅት በወጣትነት እድሜ ያለው በኢህአዴግ በምትመራው ኢትዮጵያ ያደገ በመሆኑ በታላላቅ ወንድሞቹና እህቶቹ የነበረውን ብሄራዊ ስሜትና አገራዊ ፍቅር ሊወርስ ላለመቻሉ ዋነኛው ተጠያቂ ኢህአዴግ እንደሆነ አያከራክርም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ወጣቱም በአይኑ ከሚያየውና ከነጉድለቱም ቢሆን ተጠቃሚ ከሆነበት አገራዊ ለውጥና እድገት እንዲሁም በቀጣይ ከፈነጠቀው ተስፋ በመነሳት በአገሩ ላይ ፍቅርና እምነት ማሳደር ይገባዋል፡፡

የዛሬዋ ኢትዮጵያ ሊኖሩባት የሚያስጎመጁ በርካታ እድሎች የሚታዩባት አገር ሆናለች፡፡ በአገራቸው የተፈጠሩትን እድሎች በመጠቀም ሰርተው መኖርና ኑሮአቸውን ማበልፀግ የጀመሩ በርካታ ወጣቶች አሉ፡፡ ወደ ውጭ አገር የመሄድ እድል አግኝተው የማይጓጉ፣ በውጭ አገር አድገውና ተምረው ያላቸውን ሙያና ሃብት ይዘው ወደአገራቸው በመመለስ ሰርተው የሚኖሩ፤ ለሌሎችም አርአያ የሚሆኑ አገር ወዳድ ወጣቶችም ጥቂት አይደሉም፡፡ ይሁንና ብሄራዊ ስሜትን ከማጎልበት አንፃር በወጣቱ ዘንድ ያሉትን ጉድለቶች በዝርዝር እየፈተሹ ሁኔታውን ለመለወጥ መንቀሳቀስ ይገባል፡፡ በአሁኑ ሰአት የሚታየውን በአገር ውስጥ ለመኖር ያለመፈለግ፣ በአገር ውስጥ ስራ ላይ ቢውል ብዙ ጥቅም ሊያስገኝ ይችል የነበረ ከፍተኛ ገንዘብ ድረስ ወጭ በማድረግ ስደት መሄድ የመሳሰሉ ችግሮችን ተገቢ ትኩረት ሰጥቶ መታገል ያስፈልጋል፡፡ በውጭ አገር ምን አይነት አስቸጋሪ ኑሮ እንደሚገፉ በመደበቅ ሌሎችም እንዲሰደዱ የሚቀሰቅሱ ዳያስፖራዎች እንዲሁም ህገ ወጥ አዘዋዋሪዎችን ወጣቱ በቃችሁ ሊላቸው ይገባል፡፡

## 7.6 የተደራጀ ተሳትፎን ማጠናከር

ከአገራችን ወጣቶች ምን ይጠበቃል በሚለው ርእስ ትኩረት በመስጠት መሰራት የሚገባቸውን በርከት ያሉ ተግባራት ዘርዝር አድርገን ተመልከተናል፡፡ ወጣቶች እነዚህን ተግባራት ማከናወንና በአገራችን ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት የሚችሉት ግን በተናጠል በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በጭራሽ አይሆንም፡፡ በአገሪቱ ያሉትን አስቻይ ሁኔታዎችን አሟጦ መጠቀምና መልስ ያላገኙት ጥያቄዎቻቸው በአግባቡ እንዲመለሱላቸው መታገል የሚችሉት የተደራጀ ሃይል ከሆኑ ብቻ ነው፡፡ በርግጥም መደራጀት ሃይል ነው፤ በጋራ ፍላጎት ዙሪያ የሃሳብና የተግባር አንድነት መፍጠር

የሚቻለው በጋራ መምከር፣ ማቀድና መሰማራት የሚያስችል አደረጃጀት ሲኖር ይሆናል፡፡ ከዚህ አኳያ የአገራችን ወጣቶች ቀደም ሲል የተጀመሩ አደረጃጀቶችን ማጠናከር፣ ባልተደራጁበት ደግሞ ፈጥኖ ወደ መደራጀት መግባት ይኖርባቸዋል፡፡ ወደ መደራጀት ለማምራት እንቅፋት የሚሆኑትን ጉዳዮች በዝርዝር በመፈተሽ በብቃት መሻገር መቻላቸውን ማረጋገጥ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በዚህ ረገድ መደራጀት የኢህአዴግ ተቀጥላ ያደርጋል፣ በነፃ መንቀሳቀስ አይቻልም፣ ከኢህአዴግ ነፃ የሆነ አደረጃጀት አይፈቀድም፣ በይፋ ባይከለከልም የተለያየ ሰበብ እየተፈለገ እንዳይንቀሳቀስ ይደረጋል የሚሉና የመሳሰሉ ጥርጣሬዎች ይኖራሉ፡፡ በመሰረቱ ወጣቶች ይደራጁ ሲባል በዋነኛነት በእድሜ አደረጃጀት እንጂ በፖለቲካ ድርጅት አይደለም፡፡ የፖለቲካ ፓርቲ ማደራጀት የሚፈልግ ወይም በተደራጁት ፓርቲዎች አባል ሆኖ የሚሰለፍ መብቱ ስለሆነ አይከለከልም፡፡ ነገር ግን ሁሉም ወጣቶች የፓርቲዎች አባላት ሊሆኑ አይችሉም፡፡ እንደ ወጣት ያሏቸውን የጋራ ፍላጎቶችና ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ በጋራ የሚታገሉበት መድረካቸው ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በእድሜያቸው ተለይተው የሚደራጁበት ማህበር ይሆናል፡፡ ኢህአዴግ ባለፉት አመታት የነበረውን ጉዞ ሲገመግም ብዙሃን ማህበራትን በሚመለከት በነፃ እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ በኩል ድክመት እንደነበረበት በመገምገም ማህበራት በነፃነት እንዲደራጁና በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ የሚያደርጉ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት የወጣቶች ማህበር የነፃነት ጉዳይ ችግር እንደማይሆን በመረዳት ወጣቶች በየአካባቢያቸው መደራጀትና የአገሪቱን ችግሮች በስር ነቀል ደረጃ ለመለወጥ በኢህአዴግ የታወጀው እንደገና በጥልቀት የመታደስ አገራዊ ንቅናቄ አካል መሆንና የተደራጀ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 7.7 የአገሪቱን ህዳሴ ለማስቀጠል አቅም ያለው ፓርቲና መንግስት

ኢ.ህአዴግና አባል ድርጅቶቹ በአገራችን ውስጥ የስርዓት ለውጥ ለማምጣት ትግል ጀምረው፣ ትግሉን በትክክለኛ መስመር መርተው ለድል ያበቁ፣ ባለፉት 25 አመታትም ኢ.ትዮጵያን በመምራት አገራችንን ለከፍተኛ እድገትና የህዝብ ተጠቃሚነት ያበቁ፣ ይህ እውን ይሆን ዘንድም ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉ ናቸው፡፡ ህዝባዊ ትግልን ጀምሮና መርቶ ለድል ለመብቃት ጠንካራ ድርጅት መሆንን ይጠይቃል፡፡የማንኛውም ድርጅት የጥንካሬው መሰረት ደግሞ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ መስመሩ ነው፡፡ ኢ.ህአዴግ በተግባር የተፈተነና ውጤታማነቱ በተግባር የተረጋገጠ የጠራ መስመር አለው፡፡ ከዚህ መስመሩ የሚመነጭ ዴሞክራሲያዊ ድርጅታዊ አሰራርና ውጤታማ የድርጅት ግንባታ አቅጣጫን ይከተላል፡፡ በድል አድራጊነት ለመቀጠሉ አይነተኛው ምስጢርም ይህ ነው፡፡

የኢ.ህአዴግ አልፋና ኦሜጋ የህዝብን ጥቅምና መብት ማስከበር ነው፡፡ ኢ.ህአዴግ በአገራችን ህዝቦች ጥቅም ላይ አይደራደርም፣ የአገራችንን ህዝቦች ጥቅም አሳልፎ የሚሰጥ ማናቸውንም አይነት ዝንባሌና ድርጊት አምርሮ ይታገላል፡፡ የህዝቦችን ጥቅም በማስከበር ረገድ ራሱን የህዝብ ሞግዚት አድርጎ አያይም፡፡ የኢ.ህአዴግ ሚና ህዝቡ ከራሱ ተሞክሮ እየተማረ መብትና ጥቅሙን ለማስከበር በሚደረገው እንቅስቃሴ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን ብቁ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ አመራር መስጠት እንደሆነ ያምናል፡፡ ለህዝብ ጥቅም ቀን ከሌት የመስራት፣ ከህዝብ ጋር ተዋህዶ የመንቀሳቀስ ባህልና ጥልቅ ህዝባዊነት ገንብቷል፡፡ህዝቡ በአገሪቱ በተጀመረው ለውጥና እድገት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን በሚሰጠው አመራር የህዝቡን ድጋፍና አለኝታነት ገብይቷል፡፡ ይህ ላለፈው፣ አሁንም እያካሄደው ለሚገኘውና በቀጣይም እንዲያከናውን ለሚጠበቀው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ትልቅ አቅም ሆኖ ያገለግለዋል፡፡ እናም ኢ.ህአዴግ ባለፉት 40 አመታት የትግልና የድል ጉዞው ያካባተው ግዙፍ የአመራር አቅም እንዳለው፣ የሚመራውም መንግስት በዚህ የአመራር አቅም እየታገዘ ድሎቹን እያቀበና ድክመቶቹን እያረመ እንደሚጓዝ በተግባር የሚገለፅ እውነታ ነው፡፡

የኢህአዴግ የአርባ አመት የትግል ጉዞ የድል ብቻ ግን አልነበረም፡፡ ኢህአዴግ በትጥቅ ትግሉም ሆነ ባለፉት ሃያ አምስት አመታት በድርጅቱ ውስጥ ከሚያቆጠቁጡ የተለያዩ ዝንባሌዎችና ከውጭ ደግሞ ድርጅቱ የያዘውን የህዝብን ጥቅም የማስከበር አላማ ከሚፃረሩ ኃይሎች የሚመነጩ የተለያየ መልክና ስፋት ያላቸው ፈተናዎች ሲያጋጥሙት ቆይቷል፡፡ ይሁንናም እንዳቸውም ለውድቀትና መበታተን አላበቁትም፡፡ ችግሮቹ የተከሰቱበትና ድርጅቱን የተፈታተኑበት ጊዜ ርዝመት የፈለገውን ያህል ቢሆንም ሁሉንም በብቃት ፈትቶ የድል ጉዞውን አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ሁሉንም ችግሮች መፍታትና በድል አድራጊነት ማጠናቀቅ የቻለው ደግሞ የአገራችንን ህዝቦች ጥቅም የሚጎዱ ጉዳዮችን ባለመደራደርና ህዝባዊነቱን በዘላቂነት ጠብቆ በመጓዙ ነው፡፡ ይህ የኢህአዴግ ባህሪና ህዝባዊነቱ የሚሰጠው ጠንካራ አቅም ዛሬም ሆነ ነገ ሊያጋጥሙን የሚችሉትን ማናቸውም ከውስጡና ከውጭ የሚመጡ ችግሮችን ለመመከት እንደማይቸገር ያስገነዝበናል፡፡

የኢፌዴሪ መንግስትን በቀላሉ መናድ፤ አስገድዶ በአገርና በህዝብ ጥቅም ላይ እንዲደራደርና አሳልፎ እንዲሰጥ ማድረግ ይቻላል ብለው የሚገምቱ ቢኖሩ መንግስታችንና የሚመራውን ፓርቲ ኢህአዴግን የማያውቁ ብቻ ናቸው፡፡ ሃያላኑ የአለም መንግስታትና በነሱ የሚመሩት አለም አቀፍ ድርጅቶች የመንግስትን እጅ በመጠምዘዝ ውሎ አድሮ የኢትዮጵያን ህዝብ የእነሱ ጥገኛና ምፅዋት ለማኝ ሆኖ እንዲኖር ለማድረግ የሞከሩዋቸውን ሁሉንም አይነት ማግባባትና አለፍ ሲልም ሴራና ተንኮሎች “በመቃብሬ ላይ ካልሆነ በቀር አልቀበልም” ብሎ በፅናት የዘለቀ ድርጅት ነው ያለን፡፡ ማህበራዊ መሰረቶቹ የሆኑት ህዝቦች በስህተት ጥቅሞቻቸውን የሚፃረሩ አቋሞች ቢይዙ እንኳ በትዕግስት ስህተቱን በማሳየትና ከራሳቸው ተሞክሮ እንዲማሩ እድል በመስጠት ወደ ትክክለኛው አቋም እንዲመጡ ይጥራል እንጂ አድርባይ አቋም አይወስድም፡፡ ህዝቡን ለማስደሰት ብሎ የተሳሳተውን የህዝብ ሃሳብ አይቀበልም፣ ህዝቡ የተሳሳተ አቋም ይዞ ወደ ጥፋት ሲያመራም እስከፈለገ ድረስ ይሂድና ይቅመሰው፣ ከደሙ ንፁህ ነኝ በሚል ህዝቡን ክዶ አይቆምም፡፡ ህዝቡን እያስተማረ የተሳሰተ አቋም በመያዙ ምክንያት የሚከሰተውን ጉዳት ከህዝቡ ጋር ሆኖ ይልቁንም ግንባር ቀደም ሆኖ መስዋእት እየከፈለ ወደ ትክክለኛው አቋም እንዲመለስ አመራር ይሰጣል፡፡ ይዋል ይደር እንጂ ህዝብ ትክክለኛውን አቋም መያዙ፣ ስህተትን

ማረሙ ስለማይቀርም በተሳሰተ መንገድ ተጉዞ ለጉዳት ሲዳረግ ያልከዳውን ሀይል ማቀፉ አይቀርም፡፡ የዚህ አይነት ጠንካራ ህዝባዊ ወገንተኛነት ያለው ፓርቲና መንግስት በርግጥም የአገራችንን ህዳሴ ለማስቀጠል የሚያስችል ጠንካራ አቅም እንዳለው መረዳት ከባድ አይሆንም፡፡

# 8. ማጠቃለያ

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በበርካታ ስኬቶች የታጀቡ የለውጥ እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱባት፣ ህዝቦቿ የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲን ጣፋጭ ፍሬ ማጣጣም የጀመሩባት ታዳጊ አገር ናት፡፡ የለውጥ እንቅስቃሴው ያልዳሰሰው የአገራችን ክፍል፣ በለውጥ እንቅስቃሴው ያልተሳተፈ የህብረተሰብ ክፍል የለም፡፡ የአገራችንም ወጣቶች በዚህ የለውጥ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ተሳትፎ እንደነበራቸው ይታመናል፡፡ አገራችን የጀመረችውን ህዳሴ በማስቀጠልና የሚያጋጥሟትን ተግዳሮቶችና ችግሮች በብቃት በመፍታት በኩልም ከወጣቶች ንቁና የተደራጀ ተሳትፎ ይጠበቃል፡፡ ሁሌም ወጣቱ እንደ አንድ የህብረተሰብ ክፍል በአገር ልማትና እድገት ላይ የሚኖረውን ሚና በትክክል ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

በግለሰቦች ዘንድ ከሚታይ ጉድለት ወይም ብርታት በመነሳት ጠቅላላ ወጣቱን ትውልድ በጅምላ እንዲህ ነው፣ እንዲህ አድርጓል ብሎ መሳል ተገቢ እንደማይሆን መገንዘብ ይገባናል፡፡ ብዙውን ጊዜ ለጥፋት የሚሰማሩ ጥቂቶች እንጂ ብዙሃኑ እንደማይሆኑ ማመን ተገቢ ይሆናል፡፡ አጥፊዎችን ከጥፋት እንዲታረሙ፣ ለራሳቸውም ሆነ ለአገር የሚጠቅመውን ትክክለኛ መንገድ እንዲከተሉ ማስተማር ከሁሉም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ይሆናል፡፡ የማይማር፣ የማይለወጥ የሰው ልጅ እንደማይኖር፣ ዞሮ ዞሮ የትኛውም የህብረተሰብ ክፍል ዘላቂ ጥቅሙን ከሚያስከብርለት አላማ ጎን እንደሚሰለፍ የተሟላ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡ በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች በተከሰተው ሁከት የተሳተፉ ወጣቶችም መላ የአገራችንንም ሆነ ሁከቱ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ያሉትን ወጣቶች የሚወክሉ አይደሉም፡፡ ጥቂቶች መሆናቸው ብቻም ሳይሆን ሊማሩና ከስህተታቸው ሊታረሙ እንደሚችሉ በመገንዘብ ትክክለኛ አቀራረብና አያያዝ መከተል አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የአገራችን ወጣቶች ባለፉት 25 አመታት ብዙ ነገሮችን ተምረዋል፡፡ በየሚኖሩበት የገጠርም ሆነ የከተማ ቀበሌ በየጊዜው አዲስ ነገር ሲሰራ፣ አካባቢው ሲለወጥ፣ የህዝቡ ገቢ ሲሻሻል፣ የሰው አመለካከት ሲቀየር በአይናቸው አይተዋል፡፡ አነሰም በዛ ከ25 አመት በፊት ህዝቡ እንዴት ይኖር እንደነበር፣ ምን አይነት በደል እንደደረሰበት፣ የያኔው ወጣት ይኖርበት በነበረውና በአሁኑ ወቅት ያለው ወጣት በሚኖርበት ሁኔታ መካከል ስላለው ልዩነት ከቤተሰቦቻቸው ሰምተዋል፡፡ ከዚህ አኳያ በአይናቸው የሚያዩትንና ከወላጆቻቸው የሰሙትን እውነታ በሃሰት ቀምመው ሊሰብኳቸው የሚመጡ ሃሳዊ መሲሆችን አሳፍረው ሊመልሷቸውይገባል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በእለታዊ ኑሯቸው ሳንካ የሆነባቸውንና አቤት ቢሉ ሰሚ አጥተው ተስፋ የቆረጡበትን ችግር የለም ብለው ሊደፍቋቸው የሚሹ ሰሞነኛ ባለስልጣኖችን በድምፅ መስጫ ካርዳችን እንደሾምንህ በካርዳችን እናወርድሃለን፣ ካስፈለገም የምርጫ ጊዜ ሳንጠብቅ ልክህን እንሰጥሃለን፣ ለራስህ ብትል ጣፍጥ አሊያ እንወረውርሃለን ማለት አለባቸው፡፡ በእነሱና ይሁንታ ሰጥተው ባቋቋሙት መንግስት መካከል የሚኖርን አለመግባባት እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ቀዳዳውን ለማስፋትና ወደ ጥፋት ለማምራት የሚደረግን አፍራሽ ጥረት ደግሞ የዘንዶ ጉድጓድ ለመለካት የተዘጋጀ ክንድ የለንም፣ እጅህን አንሳ ማለት ይኖርባቸዋል፡፡

በታሪክ ሂደት ብዙ አጋጣሚዎች ይፈጠራሉ፣ ድልና ሽንፈት፣ ስኬትና ውድቀት፣ ወደፊት መገስገስና ወደ ኋላ ማፈግፈግ የመሳሰሉ ሁኔታዎች የሚፈራረቁበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይሁን እንጂ ከድል በኋላ ሽንፈት፣ ከስኬት በኋላ ውድቀት፣ ወደ ፊት በመገስገስ ላይ የነበረ ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ ሲገደድ የሚኖሩት ሂደቶች ብዙ ዋጋ የሚያስከፍሉና እንደገና ወደ ድልና ስኬት ለመመለስ ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስዱ ምናልባትም ወደ ሙሉ ሽንፈትና ውድቀት የሚያመሩ የሚሆኑበት እድል ይኖራል፡፡ አገራችን ኢትዮጵያም ለዘመናት የነበረችበትን ሁኔታ በአይነቱ የቀየረና ወደ ህዳሴ ያስገባት ለውጥ እውን ሆኗል፡፡ አዲሱ መድረክ ከተከፈተ በኋላ ባሉት 25 አመታት በተለይም ደግሞ መሰረታዊ ለውጥ በመጣባቸው 15 አመታት ውስጥ አንፀባራቂ ድሎችን ተጎናፅፋለች፡፡ በመሆኑም የተያያዘችው ፈጣን የእድገት ጉዞ በጭራሽ እንዳይስተጓጎል፣ ህዝቡና ወጣቱ ማየት የጀመረው

ብሩህ ተስፋ እንዳይጨልም መረባረብ ይኖርብናል፡፡ ይህንን እድል በዋዛ ፈዛዛ ካስመለጥነው ግን ወደ ኋላ የምንሄድበትን ርቀት መገመት ያስቸግራል፤ እንደገና ወደ ህዳሴው መድረክ ለመመለስ የሚኖረውም ጉዞ ወደ ኋላ ከሄድንበት ርቀት እጅግ የረዘመ ሊሆን ይችላል፡፡

የአገራችን ወጣቶች የኢትዮጵያ የወደፊት እድል በእጃቸው ላይ እንዳለ መገንዘብ አለባቸው፡፡ ይህን እድል አጥብቀው ሊይዙትና በየጊዜው እየዳበረ እንዲሄድ የሚጠበቅባቸውንም ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡ በምንም ቢሆን በእጃቸው ባለው እድል ላይ ቁማር እንዲጫወቱ ህዝቡና ኢህአዴግ እንደማይፈቅዱላቸው መረዳት አለባቸው፡፡ ኢህአዴግ የአገራችን ወጣቶች አገር የመረከብ ሚናቸውን በብቃት እንዲወጡ ለማስቻል ዛሬም እንደዱሮው የሚጠበቅበትን የመሪነት ሚና እንደሚጫወት በዚህ አጋጣሚ ማረጋገጥ ይወዳል፡፡ የወጣቶች የልማትና መልካም አስተዳዳር ፍላጎቶች ሊሟሉ የሚችሉት በአገራችን ሰላምና የህግ የበላይነት በተረጋገጠበት ሁኔታ ብቻ ስለሆነ ወጣቶች ሰላምና የህግ የበላይነትን የማረጋገጡ አካል እንዲሆኑ ኢህአዴግ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

# በሶሻል ሚዲያ ምህዳሩ ተሳትፏችንን በማሳደግ ግንባር ቀደም ሚናችንን እንወጣ !!

## 1. መግቢያ

አሁን ባለንበት ዘመነ ግሎባላይዜሽን አለምን ወደ አንድ መንደር ተቀይራለች ካስባሏት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ መረጃን በፍጥነትና በብዛት መለዋወጥ መቻሉ ነው፡፡ መረጃን ከአንዱ የአለም ጫፍ ወደ ሌላኛው የአለም ጫፍ ለማድረስ የሚወስድው ጊዜ እያጠረ ሄዶ አሁን ክስተቱ እንደተፈፀመ ወዲያውኑ ማስተላለፍ ተችሏል፡፡ ምስልና ድምፅን አዋህደው በሚጠቀሙ እንደ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ባሉ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የሚደረገው የመረጃ ስርጭት ሰዎች በየደቂቃው ከፍተኛ መጠንና አይነት ያለው መረጃ እንዲቀበሉ አድርጓል፡፡ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ቀጥታ ስርጭቶች ለዚህ ማሳያ ናቸው፡፡

በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1982 ጥቅም ላይ የዋለው የኢንተርኔት አገልግሎትና በሱ ላይ ተመስርቶ ወደ ሁለተኛ ምዕራፍ የተሸጋገረው የዌብ 2.0 አገልግሎት ደግሞ ይህን ፈጣንና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ እጅግ ወደላቀ ደረጃ ከማሳደጉም ባሻገር የመረጃ ልውውጡን መሰረታዊ ባህሪዎችም ቀይሯል፡፡ ቀድሞ የነበረው ሁሉንም አይነት መረጃ የመቀበል የውዴታ ግዴታ አሁን የፈለጉት መረጃ ብቻ መርጦ በመውሰድ ተቀይሯል፡፡ ቀድሞ የነበረው የአንድ አቅጣጫ የመረጃ ቅብብሎሽ ተቀይሮ አሁን ዜጎችም የመረጃ አቀባይ ጭምር ሆነዋል፡፡ በተለይም የሞባይል ቴክኖሎጂ እየተስፋፋ መሄድ ሰዎች የሚያገኙትና የሚያስተላልፉት መረጃ በከፍተኛ መጠን እንዲጨምር አይነተኛ ምክንያት ሆኗል፡፡

የሞባይልና (ስማርት ፎንና ታብሌት ኮምፒውተርን ጨምሮ) ዌብን መሰረት ያደረጉ ቴክኖሎጂዎች እየዘመኑና እየተስፋፉ መምጣት በበኩሉ ይህን በብዙ ምንጮችና በብዙ ተደራሾች(many sources to many receivers ) መካከል የሚደረግ ግዙፍ የመረጃ ልውውጥ በአዲሱ የሚዲያ ስርዓት አማካኝነት ወደ ላቀ ደረጃ አሸጋግሮታል። ይህ ፅሁፍም አዲሱ ሚዲያ ወይም ደግሞ ሶሻል ሚዲያ የሚል ስያሜ ባገኘው በአዲሱ የሚዲያ ስርዓት ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡

የምንገነባው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ከምንም በላይ መላ ህዝባችን በሂደቱ በባለቤትነት የሚሳተፍበትና ከውጤቱም ተጠቃሚ የሚሆንበት መሆን ይገባዋል፡፡ በተለምዶ መገናኛ ብዙሃን (ህትመትና ብሮድካስት) እንዲሁም በገፅ ለገፅ በምንፈጽመው የህዝብ ግንኙነት ስራ ሚሊዮኖችን ለልማት ማንቀሳቀስ በመቻላችን በአካባቢ ጥበቃ፣ በጤና ልማት፣ በትምህርት ልማት፣ ወዘተ… ከራሳችን አልፈው አለምን ያስደመሙ ውጤቶችን አስመዝግበናል፡፡ ይህ የህዝብ ግንኙነት ስራችን ዘመኑ ከደረሰበት ደረጃ ጋር እራሱን እያዘመነ መሄድ እንዳለበት ሆኖ በተለይ በተለምዶ ሚዲያው በአግባቡ የማንደርስባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ለማግኘት አዳዲስ ስልቶችን መቅረፅ ተገቢ ነው፡፡ በማራቶን ሩጫ መልክ ሳይሆን በትውልዶች የዱላ ቅብብሎሽ አማካኝነት የሚሳካው የኢትዮጵያ ህዳሴ ባለአደራ የሆነውን ወጣቱን ትውልድ እንዲሁም ምሁራንና የሚበዛውን የከተማ ነዋሪ መድረስ የምንችለው በአዲሱ ሚዲያ አማካኝነት መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ድርጅታችን በሶሻል ሚዲያው ዘርፍ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም ይህ ፅሁፍ ሶሻል ሚዲያው ለፖለቲካና ህዝብ ግንኙነት ስራችን በሚኖረው ፋይዳ፣ እስካሁን ባሉ ጅምር ስራዎች፣ ሚዲያውን በስፋትና በተደራጀ ሁኔታ ለመጠቀም በቀጣይ መፈፀም በሚገባቸው ተግባሮችና በአጠቃቀም ሂደት ልንከተላቸው በሚገቡ መርሆዎችና ስልቶች ላይ አተኩሮ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. የሚዲያ ታሪክ በኢትዮጵያና በአለም

ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ ሁለተኛው የአለም ጦርነት ማጠናቀቂያ ድረስ የመገናኛ ብዙኃን የሚለው ስያሜ በአለም አቀፍ ደረጃ የነበረው አረዳድ ከህትመት ውጤቶች ጋር የተሳሰረ ነበር። ይህም ቢሆን ከመረጃ ወይም ዜና ምንጭነት ጋር የተሳሰሩትን ህትመቶች ለማመልከት እንጂ መፅሃፍትን ጨምሮ እንደ በራሪ ወረቀቶች ያሉትን የህትመት ውጤቶች ከተመለከትን የህትመት ታሪኩ ብዙ ክፍለ ዘመናትን ወደኋላ ይሄዳል። ከሁለተኛው የአለም ጦርነት መጠናቀቅ በኋላ የብሮድካስት ሚዲያ (ሬዲዮና ቴሌቪዥን) ለአገልገሎት መዋል ሲጀምር ድምፅና

ምስልን እያዋሃደ አድማጭ ተመልካቾችን ማዝናናት፣ ማስተማርና ማሳወቅ የጀመረው የመገናኛ ብዙሃን ተቀባይነቱ እያደገ መጥቷል። የኢንተርኔት መፈጠር ደግሞ በተለያዩ ድረ ገፆች አማካኝነት ዜጎች በቀላሉ ዜና ብቻ ሳይሆን ሁሉን አቀፍ የመረጃ ቋት ባለቤት እንዲሆኑ አስችሏል። እናም አሁን ዘመኑ የደረሰበት የመገናኛ ብዙሃን ( mass media) ትርጓሜ ህትመቶችንም፣ ብሮድካስት ሚዲያውንም፣ በኢንተርኔት ላይ የተመሰረተውን የመረጃ አቅርቦትም ሁሉ ያካተተ ሆኗል።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የጋዜጣ ህትመት እንደሆነ የሚነገርለት አዕምሮ የሚባለው ሲሆን በእጅ ተጽፎ በ4 ገጽ እና በ24 ቅጂዎች በአዲስ አበባ የሚሠራጭ ነበር። በፈረንሳይኛ ቋንቋ ይታተም የነበረው ላ ሲሜዩኒ ዲ ኢትዮጵ (le semalne d'ethiopie) የተሰኘው ሳምንታዊ ጋዜጣም ከቀዳሚዎቹ የህትመት ሚዲያ የሚጠቀስ ነው። በሀገራችን የሬዲዮ ስርጭት በአጭር ሞገድ አገልግሎት እ.አ.አ በ1931 ሬዲዮ አዲስ አበባ በሚል መጠሪያ ነው የጀመረው። ይህ የሬዲዮ ጣቢያ በፋሽስት ጣሊያን ወረራ ወቅት ለወራሪው ሃይል የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ እንዲሆን ተገዶ ነበር። ወረራው ከተቀለበሰ በኋላ በአዲስ መጠሪያ የኢትዮጵያ ሬዲዮ አገልግሎት ተብሎ በአራት ቋንቋዎች አገልግሎት መስጠት እንደጀመረ ታሪክ ያስረዳል። በሀገራችን የቴሌቪዥን አገልግሎት እ.አ.አ በ1963 የመጀመሪያውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ስብሰባ በመዘገብ የተጀመረ ሲሆን በወቅቱ ጥቁርና ነጭ ቀለም ምስሎችን ብቻ ነበር የሚያሳየው። ባለቀለም ቴሌቪዥን የተጀመረው በ1977 ዓ.ም ለአስረኛው የአብዮቱ ምስረታ በዓል ነው። የኢንተርኔት አገልግሎት እ.አ.አ ከ1993 ጀምሮ ወደ ሀገራችን የገባ ሲሆን በወቅቱ በአዲስ አበባ የሚገኙ አለም አቀፍ ድርጅቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ብቻ ይጠቀሙበት ነበር።

በአለም አቀፍ ደረጃ በአጠቃላይ የኢንተርኔትና በተለይ ደግሞ የሶሻል ሚዲያ ተጠቃሚዎች ቁጥር ከሚገመተው በላይ ፈጣን እድገት እያሳየ ነው። በዘርፉ ጥናት ከሚያደርጉ ኩባንያዎች ውስጥ አንዱ የሆነው emarketer.com በ2016 ከአለም ህዝብ ሶስት አራተኛው የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ተንብዮ ነበር፡፡ የቅርብ መረጃዎች የሚያመለክቱት ግን የተጠቃሚው ቁጥር 45 በመቶ መድረሱን ነው። በተመሳሳይ በፈረንጆቹ

2015 መጀመሪያ ላይ 1.82 ቢሊዮን እንደሚደርስ የተገመተው ሶሻል ሚዲያ አካውንት ያላቸው ግለሰቦች ቁጥር ወደ 2.1 ቢሊዮን ተጠግቷል። የቅርብ ጊዜ መረጃዎች ይህን አሃዝ ወደ 2.3 ቢሊዮን ያሳድጉታል። እነዚህ ጥሬ ሃቆች የሚያሳዩት የኢንተርኔት አገልግሎት መስፋፋትና መበልፀግ እንዲሁም የሶሻል ሚዲያ ተጠቃሚዎች እድገት ቀጣይነት እንዳለው ነው፡፡

ይህ አዲስ ሚዲያ አገልግሎት ወደ ሀገራችን ከገባ እድሜው አጭር ቢሆንም በተጠቃሚ አንፃር ያሳየው እድገት ግን ከፍተኛ ነው፡፡ አገልግሎቱ በግለሰቦች ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በመገናኛ ብዙሃን፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በንግድና ትምህርት ተቋማት ደረጃም እየተስፋፋ ነው፡፡

በታህሳስ ወር 2005 ዓ.ም በሃገራችን የነበረው 2.5 ሚልዮን ያክል የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ መጥቶ በተጠናቀቀው የ2008 በጀት አመት የዳታና ኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥር 13.6 ሚልዮን መድረሱን የኢትዮ ቴሌኮም የቅርብ ጊዜ መረጃ ያመለክታል። የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥር በፍጥነት ማደግ የሶሻል ሚዲያ ተጠቃሚዎችን ቁጥር በዛው ልክ እንዲያድግ አድርጓል።

የሚያዚያ 2005 መረጃ እንደሚያሳየው ከኢትዮጵያ የሚነሳ የፌስቡክ ተጠቃሚ በህዳር 2003 ዓ.ም ከነበረበት 250 ሺ የተጠቃሚ ቁጥር በአራት እጥፍ እድገት አሳይቶ በ2005 ዓ.ም አንድ ሚልዮን ደርሶ ነበር። ይህ ቁጥር የሀገሪቱ ንቁ የፖለቲካ ተሳታፊ ከሆነው የከተሜው ማህበረሰብ ውስጥ ወደ 7 በመቶ የሚሆነውን የሚሸፍን ነበር፡፡ በወቅቱ በተደረገ ጥናት መሰረት እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ የፌስቡክ ተጠቃሚዎች ቁጥር 4 ሚልዮን ሊደርስ እንደሚችል ተገምቷል። ሆኖም እስከ ሰኔ 2008 ዓ.ም ድረስ ብቻ የፌስቡክ ተጠቃሚዎቹ ቁጥር 4.3 ሚልዮን መድረሱን የኢፌዴሪ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል። ይህ ቁጥር በውጭ ከሚገኘው ከ2 ሚልዮን በላይ የሚገመት ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ውስጥ በየአገራቱ የኢንተርኔት ተደራሽነት ስሌት መሰረት የኢንተርኔት ተጠቃሚ ከሆነው ዲያስፖራው ጋር ሲደመር ከ5 ሚልዮን በላይ እንደሚሆን ይታሰባል።

## 3. የሶሻል ሚዲያ ባህሪያትና አይነቶቹ

አዲሱ ሚዲያ ወይም ሶሻል ሚዲያ አንዳንዴም ዌብ 2 ሚዲያ በመባል የሚታወቀው የብዙ አይነት ማህበራዊ ድረ ገጾች የጋራ መጠሪያ ነው፡፡ ሶሻል ሚዲያ ሰዎች በህይወታቸው ስለሚያጋጥሟቸው የእለት ተእለት ጉዳዮች በፎቶ፣ በፅሁፍ፣ በድምፅ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል ወይም እነዚህን ባጣመረ መልኩ መረጃን በነፃነት የሚቀያየሩበትና የሚጋሩበት በኢንተርኔት አገልግሎት ላይ የተመሰረተ የሚዲያ አይነት ነው፡፡ በአዲሱ ሚዲያ አማካኝነት ሁሉም የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች የጋዜጠኝነት ሚናን / citizen journalism / ይጫወታሉ፡፡ በመሆኑም የመረጃ ልውውጥ ምህዳሩ እንደ ቀድሞው ጥቂት መገናኛ ብዙሃን ብቻ የሚቆጣጠሩት መሆኑ እያበቃለት ነው፡፡

አዲሱ ሚዲያ ከተለምዶ ሚዲያው ከሚለይባቸው ባህሪዎች አንዱ ተጠቃሚዎችን ንቁ ተሳታፊ ማድረጉ ነው፡፡ በተለምዶ ሚዲያ አንባቢዎች፣ አድማጮች ወይም ተመልካቾች በጋዜጠኞች የተዘጋጀላቸውን መረጃ ከመቀበል ውጪ የተሻለ አማራጭ የላቸውም፡፡ በአዲሱ ሚዲያ ግን ራሳቸው መረጃ አመንጪና አቀባይ ይሆናሉ፣ የፈለጉትን መረጃ ብቻ መርጠው የመቀበል ነፃነቱም አላቸው፡፡ በተለምዶ ሚዲያው የሚተላለፉ ዘገባዎች የተወሰነ ህብረተሰብ ተኮር ሲሆኑ በሶሻል ሚዲያ ግን ጥቅል የሆኑ መረጃዎች በአንድ ጊዜ ለሁሉም ተጠቃሚዎች ይደርሳሉ፡፡ ኢ-መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም፣ ያልተረጋገጠ የመረጃ ምንጭና ተጠያቂነት ያለመኖር አዲሱን ሚዲያ ከተለምዶው ሚዲያ ከሚለዩት ባህሪዎች ይጠቀሳሉ፡፡

የሶሻል ሚዲያዎች በአይነታቸውና አጠቃቀማቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ እነዚህ የሶሻል ሚዲያ አይነቶች በግለሰብ ምርጫ ላይ መመስረታቸው እንዳለ ሆኖ በሚሰጡት አገልግሎት አይነትም የተፈላጊነት መጠናቸው ይለያያል፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ከሞላ ጎደል በሁሉም አካባቢዎች በስፋት ጥቅም ላይ የሚውሉት ፌስቡክ፣ ቲዊተር፣ ጎግል ፕላስ፣ ብሎግ፣ ማይ ስፔስ፣ ሊንክድኢንና ዩቲዩብ ናቸው፡፡ ያም ሆኖ በሀገራችን በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉት ፌስቡክ፣ ቲዊተር፣ ዩቲዩብ፣ ብሎግና በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ሊንክድኢን ናቸው፡፡

በአለም የላቀ ተቀባይነት ያለው የሶሻል ሚዲያ አይነት ፌስቡክ ነው፡፡ እ.አ.አ በ2004 በሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የተፈለሰፈው ፌስቡክ ሲጀምር ለዩንቨርስቲው ተማሪዎች አገልግሎት ብቻ የተወሰነ ነበር፡፡ ብዙም ሳይቆይ ግን ወደ ሌሎች ዩንቨርስቲዎችና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተስፋፍቷል፡፡ ከፈረንጆቹ 2006 ጀምሮ ደግሞ ማንም 13 አመት ሞልቶኛል የሚል ግለሰብ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን ችሏል፡፡ ፌስቡክ በቋሚነት ጓደኝነት በፈጠሩ ተጠቃሚዎች መካከል ቀጣይነት ያለው ውይይትና የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ ተመራጭ ነው፡፡ ይህ ገፅ ከሌሎች ተመሳሳይ አላማ ካላቸው ቡድኖች ጋር ወይም በስራ ቦታ ወይም በት/ቤት የሚቀራረቡ በአንድ ቡድን ሆነው መረጃ ለመለዋወጥና መልዕክት ለማስተላለፍ የሚችሉበትን እድል ይፈጥራል፡፡ በየካቲት 2012 ZDNet ድረ ገፅ /zdnet.com/ ላይ የወጣ መረጃ እንደሚያሳየው ሶሻል ሚዲያ የሚጠቀሙ ዜጎች ከአንድ ወር ውስጥ በአማካኝ 6 ሰዓት ከ45 ደቂቃውን የሚያሳልፉት ፌስቡክ ላይ ነው፡፡ ዜፎራ ማርኬቲንግ በሐምሌ 2016 ያወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው 1.13 ቢልዮን ያክል ሰዎች በቀን ቢያንስ አንድ ጊዜ ፌስቡክን ይጠቀማሉ። በአለማችን በየሰከንዱ አምስት አዲስ የፌስቡክ አካውንቶች እንደሚከፈቱም በጥናት አረጋግጫለሁ ብሏል።

ቲዊተር እ.አ.አ ከ2006 ጀምሮ ስራ ላይ የዋለ የሶሻል ሚዲያ አይነት ሲሆን መረጃን በፍጥነት ለማግኘትና ለማሰራጨት የሚያስችል ነው፡፡ ቲዊተር ምንም አይነት ትውውቅ ለሌላቸው በርካታ ሰዎችም ጭምር በአጭር ጊዜ መረጃ ለማሰራጨት ያስችላል፡፡ በዚህም አማተር የዜና አዘጋገብ ይባላል፡፡ በአንድ ጊዜ ማስተላለፍ የሚያስችለው የፅሁፍ ብዛት ከ140 ፊደሎች የማይበልጥ ቢሆንም ከሌሎች ገፆች ጋር በሊንክ በማስተሳሰር በርካታ መረጃን በየሰከንዶች ለማስተላለፍ ያስችላል፡፡ ተቋሞች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ከፍተኛ ባለስልጣኖች መልዕክቶቻቸውን በአጭሩ ለማስተላለፍ ሲሉ ቲዊተርን ቀዳሚ ምርጫቸው ያደርጉታል፡፡ ቲዊተር ከሶሻል ሚዲያ አይነቶች ሁሉ ተጠቃሚዎቹን በፍጥነት እያሳደገ የሚገኝ ነው፡፡ በግሎባል ዌብ ኢንዴክስ መረጃ መሰረት ከፈረንጆቹ ሰኔ 2012 እስከ መጋቢት 2013 ባሉት ስምንት ወራት እንኳን የተጠቃሚዎቹ ቁጥር በ44 በመቶ አድጓል፡፡ ስታቲስታ ድረ ገፅ እንዳሰፈረው ከ2015 መጨረሻ ወዲህ ቢያንስ

በወር አንድ ጊዜ እንኳን ቲዊተርን የሚጠቀሙ ደንበኞች ቁጥር ከ300 ሚልዮን በልጧል። ሆኖም ጥናቶቹ የሚያሳዩት ቲዊተር ለወጣቶች ተመራጭ ሶሻል ሚዲያ እንዳልሆነ ነው፡፡ በፍጥነት እየጨመረ ያለው የተጠቃሚዎች ቁጥር ከ55 እስከ 64 ባለው የእድሜ ክልል ካሉ ግለሰቦች የሚነሳ ነው፡፡

ብሎግ ፅሁፎችና መረጃዎች በተደጋጋሚ የሚጫኑበት ብዙውን ጊዜ በግለሰቦች ወይም ጥቂት አባላት ባሉት ቡድን የሚንቀሳቀስና እንደ ቲዊተርና ፌስቡክ ካሉት ገፆች ጋር በቀላሉ ማስተሳሰር የሚቻል ገፅ ነው፡፡ ሰፊና መሰረታዊ ይዘቶችን ያዘሉ የመወያያ መልዕክቶችና ሃተታዎች የሚሰፍሩበት ነው፡፡ ይህ የሶሻል ሚዲያ አይነት ለባለቤቱ መረጃን በማቅረብና በመቆጣጠር ሂደት ከሌሎቹ በተሻለ የመቆጣጠር ስልጣን የሚሰጥ ነው፡፡ የብሎጉ ባለቤት እነማን ብቻ ማንበብ እንደሚችሉ፣ ማን አስተያየት መስጠት እንደሚችልና የትኞቹስ አስተያየቶች በሌሎች እንደሚታዩ የመወሰን እድሉ ይኖረዋል፡፡ እ.አ.አ በ1990ዎቹ ማብቂያ የተጀመረው የብሎግ አገልግሎት አሁን በአለም ላይ ከ1 ቢልዮን በላይ የሚሆኑ ብሎጎችን አፍርቷል፡፡ የብሎገሮች ቁጥርም በሶስት አመት ውስጥ ብቻ የ31 በመቶ እድገት አሳይቷል።

ዩቲዩብ እ.አ.አ በ2005 የተቋቋመና በጎግል ባለቤትነት የሚተዳደር ግዙፍ የቪዲዮ ማከማቻና መከታተያ ድረ ገፅ ነው፡፡ በገፁ ላይ ብዙ ቪዲዮዎችን የሚጭኑት ግለሰቦች ቢሆኑም ትላልቅ የመገናኛ ብዙሃንም ከጎግል ጋር በሚኖራቸው ስምምነት መሰረት የራሳቸውን አካውንት በመክፈት ቪዲዮ ይጭኑበታል፡፡ ማንኛውም ግለሰብ አስቀድሞ አካውንት መክፈት ሳያስፈልገው ዩቲዩብ ከፍቶ ቪዲዮዎችን መመልከት ይችላል፡፡

## 4. የሶሻል ሚዲያ መልካም እድሎቹና ተግዳሮቶቹ

ሶሻል ሚዲያ ሰዎች በአቅራቢያቸውና በአለም አቀፍ ደረጃ እየተካሄዱ ስላሉ እንቅስቃሴዎች መረጃ እንዲኖራቸውና ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ፣ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁና ከሌሎችም ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ፣ ስሜታቸውን እንዲገልፁና የሌሎችንም እንዲጋሩ፣ በዝቅተኛ ወጪ የምርትና አገልግሎት ማስተዋወቂያ ለመስራትና ዘመናዊ የግብይት ትስስር ለመፍጠር አዎንታዊ አስተዋፆ አለው። የፖለቲካ ድርጅቶችንም

ደጋፊዎችን በማደራጀነትና አስተሳሰባቸውን በማስረፅ ተጠቃሚ አድርጓቸዋል። ሶሻል ሚዲያ በተጨማሪም ለሰብዓዊ ተግባሮች፤ ለጥናትና ምርምር፤ ለትምህርት ስራዎችና መሰል በጎ ተልዕኮዎች ይውላል።

እነዚህን ያክል ጠቀሜታዎች ያሉት ሶሻል ሚዲያ በአንፃሩም ተጠቃሚዎችን ሱሰኛ ወይም የረጅም ሰዓት ተጠቃሚ በማድረግ ከመደበኛ ተግባራቸው የማዘናጋት፣ የንባብና የተግባር ትምህርት መቅሰሚያ ጊዜን የመሻማት፣ የገፅ ለገፅ ግንኙነትን በማላላት ማህበራዊ እሴቶችን የማናጋት የጎንዮሽ ጉዳቶች አሉት። ዚግመንት ቦውማን የተባሉ ታዋቂ ሶሲዮሎጂስት እንደሚገልፁት

*"ብዙ ሰዎች ሶሻል ሚዲያን የሚጠቀሙት አንድነትን ለመፍጠር ወይም የእውቀት አድማሳቸውን ለማስፋት ሳይሆን በተቃራኒው ራሳቸውን ከሌሎች ለመነጠልና ራሳቸውን ብቻ የሚያዳምጡበትና የራሳቸውን ገፅታ ብቻ የሚያዩበት የምቾት ከባቢ ለመፍጠር ሲሉ ነው፡፡"*

በተጨማሪም ሶሻል ሚዲያው የሽብር ቡድኖች ሰዎችን በፅንፈኛ አስተሳሰቦች እንዲያጠምዱ፣ አባላትን እንዲመለምሉና የገቢ ምንጫቸውን እንዲያሰፉ አግዟቸዋል። በፀረ ሰላምና የሽብር ሃይሎች መካከል ግንኙነትን ለማቀላጠፍ እንዲሁም ዜጎችን በአሉባልታ ለመጥመድና ግጭትን ለመቀስቀስ ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ይገኛል፡፡ የመረጃ ምንጮቹን ማንነት በእርግጠኝነት ለማወቅ የማይቻልበትና የተጠያቂነት አሰራር የሌለበት በመሆኑ የሃሰት መረጃዎች በሰፊው ይሰራጩበታል። በአለም ላይ በፌስቡክ ብቻ 83 ሚልዮን ያክል የሃሰት አካውንቶች እንደተከፈቱ ሲኤንኤን ዘግቧል። ቲዊተርም በተመሳሳይ ከ20 ሚልዮን በላይ የሃሰት አካውንቶች የተመዘገቡበት ነው።

በእኛ ሀገር ያለው የሶሻል ሚዲያ አጠቃቀም የዚሁ አለም አቀፍ ሁኔታ ነፀብራቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የራሱ ልዩ ባህርይም አለው። በአለም አቀፍ ደረጃ ሶሻል ሚዲያው የሚያስተናግዳቸው አጀንዳዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ ያሉና በዛው ልክ ከወቅቱ ጋር ተቀያያሪ ቢሆኑም በእኛ ነባራዊ ሁኔታ የምህዳሩን አብዛኛውን ቦታ ሸፍኖ ያለው ፖለቲካዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊ ሽፋኑም ፅንፍ የያዘ (Polarized) የፖለቲካ አመለካከት ምንጭና መገለጫ ሆኖ ይታያል።

እንደሚታወቀው ሀገራችን የበርካታ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ባለቤት፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋና የባህል ልዩነቶችን ያቀፈች ነች። ህብረ ብሔራዊ አንድነታችን ተጠብቆ በሰላምና በእድገት ጎዳና ልንዘልቅ የምንችለው እርስ በርሳችን ተከባብረንና ተቻችለን መኖር ስንችል ብቻ ነው። ሆኖም ሶሻል ሚዲያው ይህን እሴት ከማጎልበት ይልቅ የፀረ ሰላምና ፅንፈኛ ሃይሎች የጥላቻ ፖለቲካ ማራመጃ መሳሪያ ሆኖ ይታያል። በህዝቦች መካከል ጥላቻን ለመዝራትና የእርስ በርስ መተላለቅን የሚጋብዙ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ የሚውልበት አጋጣሚ እየተበራከተ ነው፡፡ በሀገር ውስጥ ያለውም ሆነ በውጭ ሀገራት ያለው አክራሪውና ፅንፈኛው ተቃዋሚ ሃይል ሶሻል ሚዲያውን እንደ ዋነኛ የእኩይ አላማው ማስፈፀሚያ መሳሪያ አድርጎ እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡

የአክራሪውና የፀረ ሰላም ሃይሉ የሶሻል ሚዲያ ገፆች ኢላማ ያደረጉት የኢፌዴሪ መንግስትንና የኢህአዴግን ገፅታ ለማጉደፍ፤ ህዝባዊ ተቀባይነትንና አመኔታን ለማሳጣት፤ ወጣቱና የተማረውን የህብረተሰብ ክፍል በተራ አሉባልታና የሀሰት ፕሮፓጋንዳ በመጥመድ ጊዜውንና ጉልበቱን በሀገር ግንባታ ላይ እንዳያውል ለማድረግ ነው፡፡ በሃገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሶሻል ሚዲያን በተለይም ፌስቡክን ለአፍራሽ ተግባራቸው የሚያግዙ ሃይሎችን ለማሰባሰብና ድርጅታችን የሚያስመዘግባቸውን ስኬቶች ጥላሸት ለመቀባት ይጠቀሙበታል፡፡ የፓርቲና የመንግስት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎችን ስም በሃሰት ለመወንጀል፤ በግንባሩ አባል ፓርቲዎች መካከል ግጭት እንዳለ አስመስሎ ለመሳልና የአንድ ብሔር የበላይነት እንደነገሰ አስመስሎ ለማሳየት ሶሻል ሚዲያውን በመጠቀም ላይ ናቸው፡፡

ግዙፍ የልማት ፕሮጀክቶችን ከአካባቢ ጥበቃ፣ ከሰብዓዊ መብቶች አያያዝ፣ ከቅርስ ጥበቃ፤ ከሙስና፣ ከዜጎች ማፈናቀል ጋር ሲያስተሳስሩ የነበሩትም ሶሻል ሚዲያውን በመጠቀም ነው፡፡ ስርዓቱን የሚደግፉትን ለማስገለልና ተስፋ ለማስቆረጥ የግለሰቦችን ስብዕና የሚነኩ መግለጫዎችን በመለጠፍ ጭምር ይህን መሳሪያ የተናጠል ሃብት ለማድረግ የቻሉትን ያክል ርቀት ተጉዘዋል፡፡ በሀገራችን የሚታዩ የአክራሪነት ዝንባሌዎችን በተመለከተም በእምነት ሽፋን የሚካሄድ የሃይማኖት አክራሪነትን

ለፖለቲካዊ ትርፍ ማግኛ ለመጠቀም ከተገበሯቸው ስልቶች ቀዳሚው ሶሻል ሚዲያ ነው፡፡ ውሃ የማይቋጥሩ መረጃዎችን በፍጥነት በማሰባሰብ መልክ በማስያዝና ካገኙም በሀሰት የቪዲዮና ኦዲዮ ክሊፖች ጭምር በመደገፍ እውነት አስመስለው ያቀርባሉ፡፡

የእነዚህ ሃይሎች የሶሻል ሚዲያ አጠቃቀም ድምር ውጤት ልማታዊው የሰው ሃይል በተራ አሉባልታና የጥላቻ ፖለቲካ ተጠምዶ እውቀቱንና ጉልበቱን ለልማትና ለሀገር ግንባታ እንዳያውል ማሰናከል ነው፡፡ በሀገሩ ብሔራዊ ጥቅም ላይ የሚደራደር፤ የመንግስትን የልማት እንቅስቃሴዎች ሁሉ የሚጠራጠርና በምክንያት ሳይሆን በደጋፊ/ ተቃዋሚ ብዛት የሚያምን ትውልድ የመፍጠር ሚናም ያለው ነው፡፡

ተቃዋሚና ፀረ ሰላም ሃይሎች የሚጠቀሙበት የሶሻል ሚዲያውም ሆነ ሌላው በኢንተርኔት ላይ የተመሰረተ የሚዲያ ስራ ልዩ መገለጫ እርስ በርሳቸው ያላቸው ጥብቅ ትስስር ነው፡፡ ይህ ትስስር በሀገር ውስጥ ባሉትና በውጭ ባሉት ገፆች፤ በሶሻል ሚዲያውና በሌሎቹ ሚዲያዎች እንዲሁም በሚያራምዱት አጀንዳ በግልፅ የሚታይ ነው፡፡ ለአብነት የፕሬስ ነፃነት ጥያቄ በተቃዋሚው በኩል ሲነሳ አክራሪውም ሃይል አብሮ ያራግባል፡፡ በሌላ በኩል የሃይማኖት ጉዳይ ሲነሳ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች አብረው ይጮሃሉ፡፡ ሽብርተኝነትን በተመለከተ ከመንግስት የሚወጡ መግለጫዎችን በመቃወም በኩልም ሶስቱም ሃይሎች እኩል ይሰለፋሉ፡፡ መልዕክቶቻቸውንም በሁሉም በእጃቸው ባሉ የመገናኛ ስልቶች ሁሉ በአንድ ጊዜ ያሰራጯቸዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው ከአንድ ማእከል በሚቀዳ መልእክት የሚሰሩ መሆኑን ነው፡፡

## 5. ምርጫችን ሶሻልሚዲያው የሚሰጣቸውን መልካም እድሎች በስፋት መጠቀምና ተግዳሮቶቹን መቀነስ ነው

አለም አቀፍ ሁኔታውን ስንመረምረው የፖለቲካ ፓርቲዎችና መሪዎች በአንድ በኩል ይህ አዲስ ሚዲያ ይዞት የመጣውን ፈተና ለመቋቋም ጥረት እያደረጉ በሌላ በኩል ደግሞ ሚዲያው የሚሰጣቸውን እድሎች አሟጠው ለመጠቀም ስልቶችን ይነድፋሉ፡፡ ከነዚህም አንዱ ከተለምዶ ሚዲያው እየራቀ ላለው ወጣት ሃይል የፖለቲካ ስራዎች

ቅስቀሳንና በተለይም በምርጫ ወቅት የምረጡኝ ቅስቀሳን ለማስተላለፍ ሶሻል ሚዲያውን በስፋት መጠቀም ነው፡፡ አሁን አሁን ባደጉት ሀገራት ያለው የተለምዶ ሚዲያ የወጣቱን አስተሳሰብ በመቅረፅ ረገድ ያለው ተፅዕኖ የማሳረፍ አቅም እየቀነሰ ነው፡፡ በአንፃሩ እንደ ፌስቡክ፤ ቲዊተርና ማይስፔስ አይነቶቹ በወጣቶች ተወዳጅ ሚዲያ ሆነዋል፡፡ ይህን የተረዱት ፖለቲከኞችም መራጮችን በምርጫ እንዲሳተፉ ለመቀስቀስ፤ የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን ለማስተዋወቅና መራጮችን ለማሳመን እንደ ዋነኛ የህዝብ ግንኙነት መሳሪያቸው አድርገው እየተጠቀሙበት ነው፡፡

ሶሻል ሚዲያው በሀገራችን ከላይ የተጠቀሱት አይነት ጠቀሜታዎችና የጎንዮሽ ጉዳቶች ቢኖሩትም ድርጅታችን ኢሕአዴግ የሚኖረው አማራጭ ሚዲያው የሚሰጠውን እድል አሟጦ መጠቀምና የሚፈጥራቸውን ስጋቶች ደግሞ መቀነስ ብቻ ነው፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ከቴክኖሎጂ አንፃር የሶሻል ሚዲያውን አገልግሎት መወሰን ወይም መግታት የማይቻል ስለሆነ አይደለም፡፡ ይልቁንም የምንከተለው ዴሞክራሲያዊ መስመርና የምንገነባው ስርዓት ይህንን ግድ ስለሚል ነው፡፡ በሌላ በኩል ኢህአዴግ ይህን አዲስ የሚዲያ አይነት በአግባቡ ቢጠቀም ዘርፉ በሰላም፣ በልማት፣ በዴሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ስርዓት ግንባታችን ውስጥ ከፍተኛ ሚና ሊኖረው እንደሚችል ይታመናል፡፡

የምንከተለው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ዜጎች የመሰላቸውን አመለካከት የሚይዙበትና ይህንኑም በነፃነት የሚገልፁበት ነው፡፡ የተለምዶ የመገናኛ ብዙሃንም ሆኑ አዲሱ ሚዲያ የተለያዩ አስተሳሰቦች በነፃነት የሚንሸራሸሩባቸውና በዚህም የዜጎች ህገ መንግስታዊ መብት የሚተገበርባቸው መሆን አለባቸው፡፡ ይህ የሚሆነው ከዴሞክራሲ መብት ማክበር ጎኑ ብቻ ሳይሆን የተሳሳተ አመለካከት ሊስተካከል የሚችለው አመለካከቱ በመድረክ ወጥቶ ሲታወቅ በመሆኑም ጭምር ነው፡፡ 'የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ጉዳዮች በኢትዮጵያ' በሚለው የፖሊሲ ሰነድ ላይ በግልፅ የሰፈረው አቅጣጫም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡

*"በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ጠባብና ትምክህተኛ አመለካከቶችን በሀይልና ሰላማዊ መንገድ እንዳይቀርቡ ማገድ አይገባም፡፡ እነዚህን በህግ እናግዳለን ማለት ዞሮ ዞሮ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ሁሉ ማገድን ያስከትላል፡፡ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሁሉም ሃሳቦች ከላይ የተጠቀሱትን ትምክህትና ጠባብነትን የሚያንፀባርቁ የተሳሳቱ ሃሳቦችም ጭምር የሌላን መብት ሳይደፍሩ፣ ጦርነት ሳይቀሰቅሱ እንዲቀርቡ መፍቀድ፣ እነዚህን የተሳሳቱ አመለካከቶች በተስተካከሉ አመለካከቶች በሰላማዊ መንገድ ማጋለጥ፣ ማፍረስና ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ማድረግ ነው ተገቢ የሚሆነው፡፡"*

ከዚህ መሰረታዊ እምነት በመነሳት በቅርብ አመታት በኢህአዴግና በአባል ብሔራዊ ድርጅቶቹ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል፡፡ እንደ ኢህአዴግ በዘርፉ የምናደርገው እንቅስቃሴ የሚመራበት ስትራቴጂ ተቀርፆም ነው እየተሰራ ያለው። ስትራቴጂው በሶሻል ሚዲያ ምህዳሩ የልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰቦች የበላይነት ተረጋግጦ የማየት ራዕይ ያነገበ ሲሆን ከነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ኢህአዴግ በሶሻል ሚዲያው ለመሳተፍ ያሉትን ጥንካሬዎችና ድክመቶች ይዘረዝራል፡፡ ድርጅታችን የዘረጋቸው መስመሮች፣ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሁሉም መስኮች ተጨባጭ ስኬቶች እያስመዘገቡ መሆናቸው በሶሻል ሚዲያው ለሚኖረን እቅስቃሴ ትልቅ አቅም የሚሆነን ነው፡፡ ድርጅታችን በርካታ አባላትና ደጋፊዎች ያፈራና ሰፊ ማህበራዊ መሰረት ያለው መሆኑ በአመራር ግንባታ ሂደታችን በየደረጃው ተልእኮውን መፈጸም የሚችል አመራር ከመገንባታችን ጋር ተዳምሮ በጥንካሬ የሚወሰድ ነው፡፡ የውጤታማ መስመሮችና የወርቃማ ስኬቶች ባለቤት ብንሆንም እነዚህ ስኬቶች ሶሻል ሚዲያውን ተጠቅሞ በአግባቡ የመግለፅ አቅማችንና ልምዳችን ውስን መሆኑን ስትራቴጂው በድክመት ገምግሟል፡፡ በዋና ዋና ሀገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ የጋራ ብሔራዊ መግባባት በመፍጠር ረገድ የሚታዩ ክፍተቶችም በተግዳሮትነት ተቀምጠዋል፡፡

በዘርፉ ያለንበትን ሁኔታ በስፋት ከተነተነ በኋላ በስትራቴጂው ዘመን መጨረሻ ሊደረስ የታሰበውን ራዕይ ለማሳካት የተመረጡ ስልቶችንም ከነምክንያታቸው ያብራራል፡፡ ድርጅታችን በተለያዩ መስኮች የልማት ሰራዊት የመገንባት ልምዶች ያሉት በመሆኑ ይህንን ልምዱን በሶሻል ሚዲያ እንቅስቃሴውም መጠቀም እንዳለበት ያሳያል፡፡ ኢህአዴግ በሶሻል ሚዲያው የሚኖረው የተደራጀ ንቅናቄ በአደረጃጀቱም ሆነ በአሰራሩ አዲስ ከመሆኑ አንፃር የሰራዊቱ ክንፎች በተናጠል ያላቸውን ተልዕኮ የሚፈፅሙበትና በጋራ በሚፈፅሟቸው ተልዕኮዎች ላይ ደግሞ እርስ በርስ የሚቀናጁበት የአሰራር ስልትም የስትራቴጂው አካል ነው፡፡ ከህብረተሰብ ክፍሎች በወጣቶች ላይ፣ ከሶሻል ሚዲያ አይነቶችም ብዙ ተጠቃሚዎች ላሉት ፌስቡክ ላይ ልዩ ትኩረት የመስጠት ስልት እንደምንከተልም በግልፅ ተመላክቷል፡፡

ስትራቴጂ ከመቅረፅ ጎን ለጎን በኢህአዴግ ምክር ቤት ፅ/ቤት ደረጃ ቀድሞ ከነበረው ዌብ ሳይት (http://www. eprdf. org. et/) በተጨማሪ ይፋዊ የፌስቡክ ገፅ(EPRDFofficial)፣ የቲዊተር አካውንት(@EPRDFEthiopia)፣ ብሎግ (http://Eprdfblog.blogspot.com/) እና ዩቲዩብ አካውንት ተከፍተው የድርጅታችንን አቋም፣ ወቅታዊ መረጃዎችንና መልዕክቶችን በፅሁፍ፣ በምስል፣ በቪዲዮና በግራፊክስ ስራዎች ማስተላለፍ ተጀምሯል። ብሔራዊ ድርጅቶችም በተመሳሳይ ይፋዊ የሶሻል ሚዲያ ገፆችን ከፍተው በመስራት ላይ ናቸው። ወጥነትና ጥልቀት ባይኖራቸውም እስከ ወረዳ ድረስ ባሉ በበርካታ የድርጅታችን መዋቅሮችም የሶሻል ሚዲያ አካውንቶች ተከፍተዋል። እነዚህን ስራዎች የሚደግፉ፣ የሚያስተባብሩና የሚመሩ አደረጃጀቶችም በየደረጃው ተፈጥረዋል። በተወሰነ አካባቢዎችም ለአባላት በሶሻል ሚዲያ ስትራቴጂውና በሶሻል ሚዲያ አጠቃቀም ላይ ኦረንቴሽን ተሰጥቷል፡፡

## 6. የሶሻል ሚዲያ ስራችን ያለበት ሁኔታ

ያለፉት ሶስት አመታት ለሶሻል ሚዲያ ስራችን መሰረት የጣልንባቸውና በተወሰነ መልኩም ያስቀመጥነውን ራዕይ ለማሳካት የሚያስችሉ ተግባሮችን መፈፀም የጀመርንባቸው ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ለአብነት ያክል በ2007 በተካሄደው አጠቃላይ ምርጫ ወቅት በሶሻል ሚዲያው የምረጡኝ ቅስቀሳዎችን ስናደርግ ነበር፡፡ በተለምዶ መገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ የድርጅታችን መልዕክቶች በሙሉ በሶሻል ሚዲያውም ተደራሽ የሚሆኑበትን ስርዓት ዘርግተን እየሰራን ነው፡፡ የድርጅታችንን አቋሞችና ወቅታዊ ሁኔታዎችን የተመለከቱ ፅሁፎች እየተዘጋጁ የሶሻል ሚዲያ ተጠቃሚዎች እንዲያነቧቸውና እንዲወያዩባቸው ማድረግ ተችሏል፡፡ በቅርቡ ተጀምሮ በድርጅታችን ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን ዳግም በጥልቀት የመታደስ ሂደት አስመልክቶም ተከታታይ መረጃዎችንና መልዕክቶችን በማስተላለፍ ላይ እንገኛለን፡፡ እነዚህ ጅምርና ገና ብዙ ያልተኬደባቸው ስራዎች ቢኖሩም በጥቅል ሲታይ ግን ድርጅታችን አዲሱን ሚዲያ ከመጠቀም አንፃር የሚገባውን ያክል ሰርቷል ለማለት አያስደፍርም።

በመገናኛ ብዙሃን የሚሰራው የህዝብ ግንኙነት ስራችን ማዕከል በስርዓቱ ላይ ተፅዕኖ የሚኖረው ብዙሃኑ የገጠር ህዝብ ነው ከሚለው ተገቢና ትክክለኛ፣ ነገር ግን ከወቅቱ ጋር መጣጣም ካለበት እምነታችን በመነሳት ትኩረታችን እስከነ እጥረቱም ቢሆን በተለምዶ መገናኛ ብዙሃን ላይ ብቻ ሆኖ ቆይቷል፡፡ መንግስታትና ድርጅቶች ይቅርና ግለሰቦች የመረጃ አቅራቢዎችና አሰራጮች በሆኑበት በአሁኑ ዘመን በሁሉም ዘርፎች ታሪክ በመስራት ላይ የሚገኘው ድርጅታችን ግን ለሶሻል ሚዲያ ትኩረት ባለመስጠቱ የተነሳ ይህ አዲስ ሚዲያ የሚሰጣቸውን እድሎች ለመጠቀም አልቻለም። በአንፃሩ ምንም አይነት የልማት፣ የሰላም፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር አስተዋፅኦ ያላበረከተው ይልቁንም ስኬቶችን በማጠልሸት ላይ የተሰማራው ፅንፈኛ ተቃዋሚው ሃይል ያገኛቸውን አጋጣሚዎች ሁሉ ለጥፋት ተልዕኮው ማስፈፀሚያ ሲጠቀም ይስተዋላል፡፡

ኢህአዴግ ከ7 ሚሊዮን በላይ አባላት እንዳሉት ይታወቃል፡፡ ሶሻል ሚዲያውን የመጠቀም እድሉ ያለው የተማረውና የከተማ አባላችን በመሆኑ የሶሻል ሚዲያ ተጠቃሚ አባላት ብዛት አነስተኛ መሆኑ አይቀርም፡፡ አብዛኛው ዜጋችን የሚጠቀምባቸው የተንቀሳቃሽ ስልኮች ዘመናዊነት የሚጎድላቸውና ፈጣን የኢንተርኔት አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ከመሆናቸው ጋር ሲዳመር ደግሞ በሶሻል ሚዲያ የነቃ ተሳትፎ ያላቸው አባሎቻችን አነስተኛ ቁጥር ሊኖራቸው እንደሚችልና እነዚህም በመንግስት ስራና በተወሰነ ደረጃም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ተቀጥረው የሚሰሩና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉ ተማሪዎች መሆናቸውን ለመገመት አይከብድም፡፡ በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖም እንኳን ከሁሉም የሀገሪቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተጠቃሚ አባላት ድምር ጋር ቢነፃፀር የተሻለ ቁጥር ያለው የሶሻል ሚዲያ ተጠቃሚ አባል እንደሚኖረን ግልፅ ነው፡፡

ይህ በራሱ ግን በሶሻል ሚዲያ ላይ ያለንን ተሳትፎ ለመተንተን ወይም ለመለካት በቂ አይሆንም፡፡ ይልቁንም በዘርፉ የሚደረገው እንቅስቃሴ ከብዛት ይልቅ ጥራት ያለው ተሳትፎን /active engagement/ መሰረት ያደረገ ሲሆን ነው የብቃት ደረጃው ከፍተኛ ሊሆን የሚችለው፡፡ ምክንያቱም የሶሻል ሚዲያውን ቅርፅና ይዘት በመወሰን ረገድ አቅሙ ያላቸው እነዚህ ጥቂትም ቢሆኑ የነቃ ተሳትፎ ያላቸው ግለሰቦች ናቸውና፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት

እንደ አሜሪካ ባሉ በሰለጠኑ ማህበረሰቦች ውስጥ የሳይበር ምህዳሩን አጀንዳ የመቅረፅ አቅም ያላቸው ከአጠቃላይ ተሳታፊው ከ15 በመቶ በታች የሆኑት ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ከኢትዮጵያ አንፃር ሲለካ ደግሞ ከዚህም ያነሰ እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡ በህገራችን የሶሻል ሚዲያ አጠቃቀም ላይ በተግባር እንደሚታየውም ብዙው ተጠቃሚ ጥቂት አጀንዳ ቀራጮች የሚያወጧቸውን መረጃዎች በመቀባበልና የነሱን ትንታኔዎች ላይክና ሼር በማድረግ ግፋ ሲልም አጫጭር አስተያየቶችን በመስጠት የተወሰነ ነው፡፡

የአባላችን ብዛት፤ ያለን የኢንተርኔት ተጠቃሚ ቁጥር አናሳነትና ከሌሎች ፓርቲዎች አንፃር ያለን የቁጥር የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ላይ ግን የምህዳሩን የበላይነት ለአክራሪው ሃይልና ለተቃዋሚው ጎራ አሳልፈን የሰጠንበት ሁኔታ ይታያል፡፡ አባሎቻችን ለድርጅትና ለመንግስት ተልዕኮዎች ስኬት ቅድሚያ በመስጠት ላይ ብቻ በማተኮር ዘርፉ ለስኬታችን ማስተዋወቂያነትም ሆነ አፍራሽ ተልዕኮዎችን ተከታትሎ ለማምከን የሚሰጠውን እድል አልተጠቀሙበትም፡፡

ከላይ ያየናቸው እንቅስቃሴዎች መደረግ ከጀመሩ ወዲህ በአባላት ዘንድ ለውጦች በመታየት ላይ ናቸው፡፡ ኢህአዴግን በመርሆቹና ባስመዘገበው ውጤት የሚደግፉ ግለሰቦችም ቀላል በማይባል ደረጃ በሶሻል ሚዲያው ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ሆኖም ለእነዚህ ሃይሎች በተደራጀ ሁኔታ ድጋፍ አይደረግላቸውም፡፡ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ መረጃ የሚያቀርብላቸው አደረጃጀት የለም፡፡ እውቅና የሚያገኙበትና የሚበረታቱበት አሰራርም አልተዘረጋም፡፡

ልክ እንደ አባሉ ሁሉ በየደረጃው ያለው የድርጅት አመራርም ለሶሻል ሚዲያ ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ አይታይም፡፡ የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ የሚያሳየው የሀገር መሪዎችና ታዋቂ ግለሰቦች በግላቸው አካውንቶችን በመክፈት ለተከታዮቻቸው ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፤መረጃያቀብላሉ፡፡ የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ በ75.5 ሚልዮን የቲዊተር ተከታይ ከመሪዎች ቀዳሚ ናቸው፡፡ ከአፍሪካ መሪዎችም የደቡብ አፍሪካው ጃኮብ ዙማ፤ የኬንያው ኡሁሩ ኬንያታና የሩዋንዳው ፖል ካጋሚ በርካታ ተከታይ ያላቸው መሪዎች ናቸው፡፡ በስራቸው ያሉ ከፍተኛ ባለስልጣናትም በተመሳሳይ አካውንቶችን በመክፈት መልዕክቶችን ይቀርፃሉ፤ ምላሽም ይሰጣሉ፡፡ ይህ

በኛ ሀገር የፖለቲካ አመራር ዘንድ /ከጥቂት መሪዎች በስተቀር/ የተለመደ አይደለም፡፡ የመንግስት የስራ ኃላፊነትን ይዘው ያሉ አመራሮችም ሶሻል ሚዲያው ለተቋማቸው ራዕይ መሳካትና ለአጠቃላይ የፖለቲካ ስራችን ያለውን ፋይዳ ተረድቶ የሚመራበትን አቅጣጫ ከመንደፍና በየተቋሙ ያሉ ግንባር ቀደሞች የተልዕኳቸው አካል እንዲያደርጉት ከማስገንዘብ ይልቅ አሉታዊ ተፅኖዎቹን በመምዘዝ ጎጂ ነው የሚል ማደማደሚያ ላይ የመድረስ አዝማሚያዎች ይታያሉ፡፡

ሶሻል ሚዲያውን በተመለከተ ካለው የአመለካከት ችግር በተጨማሪ በአጠቃቀም በኩልም በአባሉም ሆነ በአመራሩ ላይ የክህሎት ችግር ይታያል። በዚህ ረገድ ሊጠቀስ የሚችለው አባሉ የሚከፍታቸውን አካውንቶች ደህንነት የመጠበቅ ጉዳይ ነው። ምንም እንኳን በግል ደረጃ የምናስተላልፋቸው መልዕክቶች የግላችን የአስተሳሰብ ውጤቶች ቢሆኑም እንደ አንድ ታሪካዊ ሃላፊነትን ተቀብሎ ሀገር የሚመራ ፓርቲ አባልነታችን መልዕክቶቻችንም ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ድርጅታችንን የሚመጥኑ መሆን እንዳለባቸው የታወቀ ነው። ከዚህ በመነሳት ሌሎች ግለሰቦች በአካውንቶቻቸው ላይ አስተያየት በመስጠትም ሆነ በቀጥታ በመለጠፍ ያልተገባ መልዕክት እንዳያስተላልፉባቸው በመስጋት ሶሻል ሚዲያውን ከመጠቀም የሚቆጠቡ አባላት አሉ። ሆኖም ቴክኖሎጂው ይህን አይነት ስጋቶችን መከላከል የሚቻልበትን አሰራርም አብሮ የዘረጋ በመሆኑ ስጋቱን በቀላሉ መቅረፍ ያስችላል።

## 7. በስኬቶች የታጀበው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመራችን የመልዕክቶቻችን ማዕከል ነው

ፖለቲካዊ አስተሳሰቡ ወይም የሚከተለው ርዕዮተ አለም ተቀባይነት እንዲኖረውና በህዝቡ ውስጥ እንዲሰርፅ የሚሻ የፖለቲካ ድርጅት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይህንኑ የማስተዋወቅና በትግበራ ሂደቱ ያሉትን የበጎ ስኬቶች መረጃ በፍጥነትና በስፋት የማሰራጨት ሃላፊነት አለበት፡፡ ይህን ማድረግ ያለመቻል ህብረተሰቡን ለሌላ ተቃራኒ አስተሳሰብ ተደራሽ እንደ ማድረግ ይቆጠራል። ሶሻል ሚዲያ ለህዝብ ግንኙነት ስራዎችና ለፖለቲካዊ ንቅናቄ ትልቅ አቅም መሆኑ የተረጋገጠው እ.አ.አ በ2008ቱ የአሜሪካ ምርጫ

ማይስፔስ፣ ዩቲዩብና ሌሎች ገፆችን ይጠቀም ነበር፡፡ በምርጫውም ኦባማ 70 ከመቶ የሚሆነውን የወጣቶች ድምፅ ማግኘት አስችሏቸዋል፡፡ በ2012ቱ ምርጫም ይህንኑ ደግመውታል፡፡ በኖርዌይና አውስትራሊያ እ.አ.አ በ2013 በተካሄዱ የምርጫ ቅስቀሳዎች ወቅት ሶሻል ሚዲያው በስፋት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በአፍሪካ በዚህ ረገድ የሚጠቀሰው እ.አ.አ በ2013 በኬንያ የተካሄደው ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ነው፡፡ ኡሁሩ ኬንያታ ወጣት መራጮችን በቅስቀሳቸው ለመድረስ የተጠቀሙት ሶሻል ሚዲያውን ነበር፡፡

አሁን ድርጅታችን በአመለካከትም ሆነ በክህሎት ያሉ ችግሮችን በመቅረፍ ሶሻል ሚዲያውን የህዝብ ግንኙነት ስራችን አንድ መሳሪያ አድርጎ መጠቀም ግድ ከሚለው ምዕራፍ ላይ ይገኛል። በመጀመሪያ ደረጃ የምንከተለውን መስመር፣ ስኬቶቻችንንና እቅዶቻችንን ለማስተዋወቅ ከተለምዶ የመገናኛ ብዙሃን በተጨማሪ አዲሱን ሚዲያ ብንጠቀም ስኬታማ የህዝብ ግንኙነት ስራ እንደምናከናውን ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል ፅንፈኛውና ኪራይ ሰብሳቢው ሃይል ያለ የሌለ ሃይሉን በማሰባሰብ የጀመርነውን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማደናቀፍ የሚረባረበው ይህን አዲስ ሚዲያ በመጠቀም ነው፡፡ ወቅታዊ የሀገራችን ሁኔታ በግልፅ የሚያሳየን በዘርፉ ያለብንን የክህሎትና የአመለካከት ችግር ቀርፈን ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ካልገባን ብዙውን ወጣት ሃይል ለፀረ ሰላም ሃይሎች ፍላጎት ማስፈፀሚያ አሳልፈን ልንሰጠው እንደምንችል ነው፡፡ ያም ሆኖ አሁንም ከሶሻል ሚዲያው የላቀ ውጤት ማግኘት የሚቻለው ከተለምዶ ሚዲያው ጋር አስተሳስሮ በጥምረት መስራት ሲቻል እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

ኢህአዴግ በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ፣ ዘላቂ ህዝባዊ አንድነትን የሚያረጋግጥ የሰላምና የዴሞክራሲ መሰረት የሆነ ህገ መንግስት በህዝቦች ተሳትፎ እንዲጸድቅና የህዝቦች የእኩልነት መብት ህገ መንግስታዊ ዋስትና እንዲያገኝ ግንባር ቀደም ሚናውን በመወጣት ሀገሪቱን ከመበታተን አደጋ በመታደግ በአለም በፈጣን እድገት ላይ ከሚገኙ 10 ሀገራት ተርታ ማሰለፍ የቻለ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅታችን ሃገራችን የምትመራባቸው ግልጽ ስትራቴጂዎች ባለቤት ነው፡፡ በእነዚህ መስመሮች አማካኝነት ባለፉት 12 ተከታታይ አመታት ህብረተሰቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ማድረግ የቻለ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት አስመዝግቧል፡፡ የድርጅታችን መስመሮችና ፖሊሲዎች በሃገራችን ህዝቡ የመሰከረላቸው ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስኬቶችን እያስመዘገቡ ይገኛሉ፡፡

ድርጅታችን ኢ.ህአዴግ በሃገራችን ዴሞክራሲዊ ስርአት እንዲገነባ ለማስቻል አምባገነናዊውን ስርአት በማስወገዱ ሂደት፣ በሽግግር መንግስት ምስረታ፣ በህገ መንግስት ማርቀቅና ማጽደቅ፣ ስልጣን በምርጫ ብቻ የሚያዝበት ስርዓት እንዲኖር በማድረግና በመሰል ወሳኝ ስኬቶች የመሪነቱን ሚና በአግባቡ የተወጣ ውጤታማ ድርጅት ነው፡፡ ኢ.ህአዴግ በሀገር ውስጥ ብቻም ሳይወሰን ከጎረቤት ሀገሮችና ሌሎች አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር መልካም ወዳጅነትና ትብብር ለመመስረት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያለውን መንግስታዊ ግንኙነት በመምራት ኢትዮጵያን ከጎረቤቶቿ ጋር በመሰረተ ልማት ለማስተሳሰር እየሰራ ነው፡፡ ይህም ከወዲሁ የጎረቤት ሀገሮችን ተቀባይነት አስገኝቶለታል፡፡ እነዚህ እስካሁን የተመዘገቡ ድሎች፣ አሁን በትግበራ ላይ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶችና የሀገሪቱ ራዕይ ፓርቲው በሶሻል ሚዲያ ለሚኖረን ስራ የማያልቁ የይዘት ምንጮች ናቸው፡፡ የድርጅቱን መሰረታዊ መርሆዎች ከእነዚህ ተጨባጭ ውጤቶች ጋር በማስተሳሰር መስራት ከተቻለ በርግጥም በማህበራዊ ድረ ገፁ ላይ የይዘት የበላይነትን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

## 8. የሶሻል ሚዲያ አጠቃቀማችን ድርጅታዊ ስነ ምግባርን የተከተለ ሊሆን ይገባዋል

በሶሻል ሚዲያ ምህዳሩ የልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰቦች የበላይነት ተረጋግጦ የማየት ራዕያችንን እውን በማድረግ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነን በሃሳብ ትግሉ የኢ.ህአዴግን አስተሳሰቦች የበላይነት ማረጋገጥ የሚችል የሶሻል ሚዲያ ሰራዊት የመገንባትና በርካታ ተጠቃሚዎችን ማሰባሰብ የሚችል የኢ.ህአዴግ ሶሻል ሚዲያ ስርዓት መዘርጋት አላማዎችን የማሳካት ስራ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ ነው። እነዚህን ቁልፍ አላማዎች መፈፀም ግን በራሱ ግብ ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም። ይልቁንም ራዕያችንን ለማሳካት የምንችለው በእቅድና አጀንዳ ላይ ተመስርተን የኢ.ህአዴግ መስመሮች፣ ፖሊሲዎች፣ ስኬቶችና እሴቶች በስፋት ማስተዋወቅና በተደራሾች ዘንድ የጋራ ግንዛቤ እንዲያዝባቸው ማድረግ ስንችል ነው። በዚሁ ሂደት የጽንፈኛ ተቃዋሚውን አፍራሽ እንቅስቃሴ ማጋለጥና መመከትም በሚዛኑ ትኩረት የምንሰጠው ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው በድርጅታችን ስምም ይሁን እንደ ግለሰብ የምናስተላልፋቸው መልዕክቶች በተቻለ መጠን የድርጅታችንን ስምና ክብር የሚመጥኑና የሚጠብቁ መሆን አለባቸው። ስለሆነም ሁልጊዜ የምንከተላቸው መርሆዎች አሉን። ከምንም በላይ በገፆቻችን የሚወጡ መረጃዎች በሙሉ ትክክለኛ መሆን አለባቸው። ከሌሎች የሚመጣን ማንኛውም ሃሳብ /የተሳሳተም ቢሆን/ ተገቢውን ክብር ሰጥተን እውነታውን ማሳወቅ አለብን። የሶሻል ሚዲያ አካውንቶቻችን አነጋጋሪ በሆኑ ዋና ዋና ሀገራዊና ድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የተደራጀና መልእክትን መሰረት ያደረገ የሃሳብ ትግል የሚደረግባቸው እንጂ የነፈሰውን አጀንዳ ሁሉ የሚያራግቡ መሆን የለባቸውም። የሚተላለፉ መልዕክቶችም ከድርጅታችን መስመሮችና ፖሊሲዎች ጋር የተጣጣሙ መሆን ይገባቸዋል። አካውንቶቻችን ሶሻል ሚዲያውን የሚጠቀሙ የድርጅታችን አባላትና ደጋፊዎች የሃሳብ ትግልና የመረጃ ልውውጥ የሚያደርጉባቸው አሳታፊ መድረክ መሆን ይገባቸዋል።

ድርጅታችንን በሶሻል ሚዲያ ውጤታማ ሊያደርጉት ከሚችሉት ስትራቴጅዎች አንዱ የሶሻል ሚዲያ ሰራዊት መገንባት ነው፡፡ በተለያዩ መስኮች የልማት ሰራዊት የመገንባት ልምዶች ያሉት በመሆኑ ይህንን ልምዱን በሶሻል ሚዲያው ተግባራዊ ማድረግ ይችላል፡፡ የድርጅታችን አባላትና ደጋፊዎች ግንባር ቀደም ሚና የሚጫወቱበት ሁኔታ በመፍጠር በሃሳብ ትግሉ የበላይነት ማረጋገጥ የስትራቴጅው ዋነኛ ትኩረት ነው፡፡ በተለይ በወጣቶች ላይ ትኩረት ያደረገ አቅጣጫ መከተል ያስፈልጋል፡፡ በሶሻል ሚዲያ አጠቃቀም ያሉብንን የግንዛቤና የክህሎት እጥረቶች በቀጣይነት በመፍታት የተቀራረበ ብቃት ላይ በማድረስ የድርጅታችን መስመሮች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች በሶሻል ሚዲያ ምህዳሩ የበላይነት እንዲኖራቸው ተግተን መስራት ይኖርብናል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በርካታ ቁጥር ያላቸው የሶሻል ሚዲያ ኔትወርኮች ቢኖሩም ከእነዚህ ውስጥ ብዙ ተጠቃሚዎች ያላቸውንና የድርጅታችንን አላማዎች ለማሳካት ወሳኝነት ባላቸው ላይ በማተኮር መንቀሳቀስ ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ፌስቡክ፣ ቲዊተርና እንደየሁኔታው ዩቲዩብና ብሎግም ቅድሚያ የምንሰጣቸው ይሆናሉ ማለት ነው።

## 9. የተደራጀ እንቅስቃሴ የማድረግ አስፈላጊነት

በተደራጀ ሁኔታ በሶሻል ሚዲያ የሚደረግ እንቅስቃሴ በግል አካውንት ከሚደረግ የሶሻል ሚዲያ ተሳትፎ እጅጉን የተለየ ነው፡፡ ማንኛውም ግለሰብ በሶሻል ሚዲያ የሚኖረው ተሳትፎ ግለሰቡ ለሶሻል ሚዲያው በሰጠው ትኩረትና ቁርጠኝነት ላይ የሚወሰን ሲሆን በተቋም ወይም አደረጃጀት ደረጃ የሚኖር ተሳትፎ ግን በተያዘለት አላማና ሊያሳካው በሚፈልገው ግብ ላይ የሚወሰን ነው፡፡ አንድ የግል አካውንት ያለው ግለሰብ አካውንቱን በፈለገው ጊዜ ሊጠቀምበት፣ ያሻውን ያክል ጊዜ ሊመድብለትና በመልዕክት አሰጣጡና አቀባበሉም ላይ በየጊዜው የሚቀያየር መልክ ሊያሲዘው ይችላል፡፡ ተቋማት የሚመሩት የሶሻል ሚዲያ ገፅ ግን ተገማች እና ወጥነት ያለው ሆኖ ጎብኝዎቹ በቋሚነት ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት የሚጠብቁት መሆን ይገባዋል፡፡ ስለሆነም ግለሰቦች ሲፈልጉ ብቻ የሚሰሩበትና መዳረሻው የማይታወቅ መሆን የለበትም፡፡ በመሆኑም ድርጅታችን በሶሻል ሚዲያ የሚያደርገው እንቅስቃሴ በእቅድና በእለት ተእለት ክትትልና ድጋፍ መመራት አለበት፡፡ ይህንን የመምራት ተልዕኮ የተሰጠው አካልም መኖር አለበት፡፡ በስሩ ተግባሮችን ተከፋፍለው የሚፈፅሙ ፈፃሚ አካላት፣ አጋሮችና እነዚህን የሚያስተሳስር አደረጃጀት ሊኖረው ይገባል ማለት ነው፡፡

እንደሌሎቹ የልማት፣ የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ተግባሮቻችን ሁሉ የኢህአዴግ ሶሻል ሚዲያ ሰራዊት ቁልፍ የድጋፍ አግባብ መሆን ያለበት የእለት ተዕለት ስራን ማዕከል አድርጎ በሚሰጥ ተልዕኮ ፈፃሚውን ሰራዊት የማብቃት አግባብ ነው፡፡ በየእለቱ በሚኖሩ ተልዕኮዎች አፈፃፀም ጥንካሬዎችና ጉድለቶች ላይ ተመስርቶ ሰራዊቱን የሚደግፍ አሰራር መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ መልካም ተሞክሮዎችን ለሁሉም ማዳረስ፣ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን ማበረታታትና እውቅና መስጠት እንደዚሁም አንፃራዊ ድክመት ያለባቸውን አደረጃጀቶችና ፈፃሚዎች በመለየት መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ ስራን ማዕከል አድርጎ የሚደረገው ድጋፍ በራሱ የማይሞላቸውን ክፍተቶችና በተለይም በመልዕክት ቀረፃና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ የሚኖሩ የአቅም ክፍተቶችን ደግሞ በተመረጡ የአቅም መገንቢያ ስልጠናዎች መሙላት ይገባል፡፡ በስራ ላይና ከስራ ውጭ የሚሰጡ የአጭርና መካከለኛ ጊዜ የስልጠና አይነቶችን በመለየት የሶሻል ሚዲያ ሰራዊቱን በማያቋርጥ መልኩ መደገፍ ያስፈልጋል፡፡

የመረጃ ልውውጥ ሌላው የድጋፍ አግባቡ መገለጫ ነው። መረጃ ከላይ ወደ ታች ብቻ ሳይሆን ከታችም ወደ ላይ መፍሰስ ይኖርበታል፡፡ በሶሻል ሚዲያ የሚደረግ እንቅስቃሴ መረጃ ላይ ጥገኛ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ በቂ መረጃ ያለውና ይህንንም በብቃት የሚያቀርብ ሃይል

የበላይነቱን ይይዛል፡፡ ስለሆነም በአንድ አደረጃጀት ወይም እርከን ያለ መረጃ ለሌሎች የሰራዊቱ አካሎች በአግባቡ በማድረስ ሁሉንም የሰራዊቱ አደረጃጀቶች በተቀራራቢ ደረጃ ላይ ማድረስ ይገባል፡፡ የአፈፃፀም ችግር ያለባቸው የሰራዊቱ አባላትም ተገቢ የሆነ ድጋፍ መስጠት የሚያስችል አሰራር መዘርጋትና በዚህም ወደ ተግባር መግባት ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን አባላትና ደጋፊዎች በተናጠል ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ የዘለለ አዋጋቢ ስራ ባይሰራም ከላይ እንዳየነው የሶሻል ሚዲያ ስትራቴጂ ከመቅረፅና የአሰራር መመሪያ ከማዘጋጀት ጀምሮ በተለያዩ አጋጣሚዎች የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ በኢህአዴግና በብሔራዊ ድርጅቶች ደረጃ የተከፈቱ አካውንቶችም አሉ፡፡(ለግንዛቤ እንዲረዳ የኢህአዴግና የየብሔራዊ ድርጅቶቹ እንዲሁም የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ኮሚቴ ይፋዊ የፌስቡክ አካውንቶች ስም ከታች ተመልክቷል፡፡) ሶሻል ሚዲያው የሚሰጣቸውን መልካም እድሎች አሟጦ ለመጠቀምና የሚያስከትላቸውን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለመቀነስ እንዲቻል ታዲያ አባላት በተለይም ምሁራን የከተማ አባላት ድርጅታዊ ስነ ምግባርን በተላበሰና የልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብን ልዕልና በሚያረጋግጥ መልኩ በምህዳሩ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ አለባቸው፡፡

| Organization | Facebook Address | |
|---|---|---|
| | Account Name | Username |
| EPRDF Council Sec. Office | EPRDF official | www.facebook.com/EPRD-Fofficial/ |
| OPDO CC Office | OPDO - Official | www.facebook.com/OPDO-Official-548492341951894/ |
| ANDM CC Office | ANDM CC office | www.facebook.com/AND-Moffice/ |
| TPLF CC Office | Tplfofficial1967 | www.facebook.com/Tplfofficial1967-1056328604419403 |
| SEPDM CC Office | Southern Ethiopian People's Democratic Movement - SEPDM | www.facebook.com/SEPD-MHQ/ |
| AA EPRDF Committee | Addis Ababa EPRDF Official | www.facebook.com/aaeprdf/ |